




# ሥነ ፍጥረት

(ሥነፍ ፩ኛ)

የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት
(የግቢ ጉባዔያት) ተማሪዎች መማሪያ
መጽሐፍ

አዘጋጆች፦ ቀሲስ ስንታየሁ አባተ
እና
ዲ/ን ብርሃኑ አድማስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች
ማ/መምሪያ በመንበረ ቅዱሳን
ትምህርት ክፍል
፲፱፻፺፯ ዓ.ም

© ማኅበረ ቅዱሳን 1996 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኤዲቶርያል ቦርድ ታርሞና ተስተክክሎ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ስልክ +251-111-24 61 82/83/84

E-mail:- mk.devt@yahoo.com
Website:- www.eotc-mkidusan.org



## "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ።።"

*መዝ.፲፰፥፩*

እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረበት ዋና ዓላማው ክብሩ አን ጂገለጥ ነው። ከዚህም የተነሣ ከተፈጠረው ፍጥረት የእግዚአብሔር ክብር የማይገለጥበት አምላክነቱ የማይታወቅበት የለም። ሁሉም የእግዚአብሔርን አምላክነት ይመሰክራሉ፤ ይናገራሉ። ለዚህም ነው ቅዱስ ዳዊት "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታውጣለች ሌሊትም ለሌሊት አውቀትን ትናገራለች።" መዝ.፲፰፥፩-፪ ቢል የተናገረው። ሰማይና ምድር የሚናገሩት ግን በሰው ቋንቋ አይደለም፤ ተፈጥሮአቸው ሰዋዊ አይደለምና። ጌታ በተሰቀሰበት ዕለት የፀሐይ መጨለም፣ የጨረቃም ደም መምሰል አምላክነቱን መናገር ነበር። ከዚህም (ከተዓምራት) ውጭ በሃይማኖት ለሚመለከታቸው የአምላክን ህልውና ይነግሩታል፤ ያሳዩታልም። ቅዱስ ጳውሎስም "የማይታየው ባሕርይ አርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን አያውቁ አንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ።" ሮሜ ፩፥፳-፳፩ ያለው በሥነ ፍጥረት እግዚአብሔርን ማወቅ የሚቻል መሆኑን ለመናገር ነው።

ሥነ ፍጥረት የእግዚአብሔርን ነገር የሚናገር የመጀመሪያ ሥራው አንጂ የመጨረሻ ሥራው አይደለም። ከሥነ ፍጥረት በኋላ ደግሞ በፈጠረው ፍጥረት አያደረ በሚሠራው ሥራ ለሰላው ፍጥረት ይገለጣል፤ ይታወቃል። ይህ መጽሐፍም አንዱ የእግዚአብሔር መገለጫ ሥራው ነው። በእርሱ ፈቃድ ተወጥኖ በፈቃዱ በፍጥረቱ ተፈጽሟልና። ይህንንም የሠራው መጽሐፉን በሚያነቡት ሁሉ አድሮ ለሰላው ለመገለጥ ነው። ከዚህ አንጻር መጽሐፉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስም ቢዘጋጀም ለምእመናን ሁሉ የሚሆንንና የሚሠራ ነው አንደመሆኑ መጠን ሁሉም ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ለሰላው የሚገልጥበት ወደሌሎች መጻሕፍትም የምንመራበት መሆን አለበት። ካለበለዚያ ክብሩን ሳያስታውሱ የሚገልጡት ከንቱነት፣ ፍጥረታት ከሰማይ፣ ከምድር፣ . . . አነሥነ ማለት ነው። ሰው ግን ክብሩን የሚነገር የሚገልጥ ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት በምግባር ቢኖር



የእግዚአብሔርን ክብር ይወርስ ዘንድ ያለው በመሆኑ ከሌሎች ፍጥረታት ይለያል።

ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ብቻ ላንወሰን ሌሎቹንም በመግዛትና በማንበብ ለሌሎችም (በተለይም ለወጣት ለባከያንና ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች) በመስጠት የእግዚአብሔርን ክብር ልንመ ሰክር በዚህም ጸጋ እግዚአብሔርን ልንወርስ ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን፤ አሜን።

*የማኅበረ ቅዱሳን ትምህርት ክፍል*



## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ..... i

### ምዕራፍ አንድ

፩. ሥነ ፍጥረት ..... 1
ሀ.፩ ትርጉም ..... 1
ሀ.፪ ህልውና እግዚአብሔር ..... 1
ሀ.፫ የሥነ ፍጥረት ዓላማ ..... 3
ሀ.፬ የሥነ ፍጥረት መገኛ ..... 7
ሀ. አምኃ አልቦ ኀበ ዖ፤ ካለመኖር ወደመኖር ..... 7
ለ. ግብር አምጣብር፤ ከተፈጠረው የተፈጠረ ..... 7
ሶ.፭ እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ያስገኘበት ሁኔታ ..... 8
ሀ. በሐልዮ ..... 8
ለ. በኃቢ /በመናገር/ ..... 8
ሐ. በገቢር /በሥራ/ ..... 9

### ምዕራፍ ሁለት

፪. አራቱ ባሕርያትና ጠባያቸው ..... 12
ሀ. መሬት ..... 12
ለ. ውኃ ..... 12
ሐ. ነፋስ ..... 12
መ. እሳት ..... 12

### ምዕራፍ ሦስት

፫. የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት ..... 17
ሀ. የነሳሣት መገኛ ..... 20

ሀ. እንዴት ተገኙ (How they come into existence) ..... 21
ሐ. የወደፊት ሁኔታ (Future of the universe) ..... 21
ይ.ጸ የዕለተ እሑድ ፍጥረታት ..... 25
ይ.ጸ.ሀ ትርጉም ..... 25
ይ.ጸ.ለ የእሑድ ሰዓተ ሌሊት ፍጥረታት ..... 25
ይ.ጸ.ሐ ከሀደተ ሳጥናኤል ..... 31
ይ.ጸ.መ የእሑድ ሰዓተ መዓልት ፍጥረታት ..... 32
ይ.ጸ.ሠ ማጠቃለያ ..... 37
ይ.ፀ የሰኞ ፍጥረት ..... 39
ይ.ፀ.ሀ ትርጉም ..... 39
ይ.ፀ.ለ የሰኞ ፍጥረት ..... 40
ይ.ፀ.ሐ የጠፈር ጥቅም ..... 41
ይ.ፀ የማክሰኞ ፍጥረታት ..... 42
ይ.ፀ.ሀ ትርጉም ..... 42
ይ.ፀ.ለ የማክሰኞ ፍጥረታት ..... 42
ይ.ፀ.ሐ የማክሰኞ ፍጥረታት ምሳሌነት ..... 43
ይ.ፁ የረቡዕ ፍጥረታት ..... 49
ይ.ፁ.ሀ ትርጉም ..... 49
ይ.ፁ.ለ የረቡዕ ፍጥረታት ..... 49
ይ.ፁ.ሐ መጋቢያነ ከዋክብት ..... 51
ይ.ፁ.መ የረቡዕ ፍጥረታት ምሳሌነት ..... 52
ይ.ፃ የሐሙስ ፍጥረታት ..... 53
ይ.ፃ.ሀ ትርጉም ..... 53
ይ.ፃ.ለ የሐሙስ ፍጥረታት ..... 54
ይ.ፃ.ሐ የሐሙስ ፍጥረታት ምሳሌነት ..... 54
ይ.ፄ የዕለተ ዓርብ ፍጥረታት ..... 57
ይ.ፄ.ሀ ትርጉም ..... 57
ይ.ፄ.ለ የእንስሳት የአራዊትና የእዕዋፍ ተፈጥሮ ..... 58
ይ.ፄ.ሐ የአሳም ተፈጥሮ ..... 60
ይ.ፄ.መ የሐዋን ተፈጥሮ ..... 64

**ምዕራፍ አራት**

፬. ቀዳሚት ሰንበት ..... 72
፬.ሀ ትርጉም ..... 72
፬.ለ የቀዳሚት ሰንበት ታሪክ ..... 72

**ምዕራፍ አምስት**

፭. ሣያው ዓለማት ..... 76
፭.ሀ. ዓለማተ አሳት ..... 76
፭.ለ. ዓለማተ ነፋስ ..... 76
፭.ሐ. ዓለማተ ማይ ..... 76
፭.መ. ዓለማተ መሬት ..... 76

**ምዕራፍ ስድስት**

፮. ሰውና ሥነ ፍጥረት ..... 80

**ምዕራፍ ሰባት**

፯. በሥነ ፍጥረት ትምህርት ለምን እናምናለን? ..... 83
፯.ሀ የሥነ ፍጥረት መጻሕፍት መለኮታዊ መጻሕፍት ስለሆኑ ..... 83
፯.ለ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስለሆኑ ..... 84
፯.ሐ ያለ ሥነ ፍጥረት ክርስትናን ማመን ስለማይቻል ..... 85
፯.መ የሥነ ፍጥረት ትምህርት ለክርስትና ትምህርት መሠረት ስለሆነ ..... 85



## መግቢያ

የሥነ ፍጥረት ታሪክ አበው ቅዱሳን፤ ሊታወጉት ቤተክርስቲያን ከአሥራው መጻሕፍት አውጥተው ጽፈው ያቆዩልን ነው። በውስጡ ከዕለተ እሑድ እስከ ቀዳሚት ሰንበት ድረስ ልዑል እግዚአብሔር ስለሃሊነቱ የፈጠራቸው የሃያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ታሪክ ተጽፏል። ከዚህም ቡተጨማሪ የፍጥረቱ ምሳሌነት ምን እንደሆነ ተገልጧል። በየርእሱና በየምዕራፉ መጨረሻ የምዘና ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪው ከትምህርቱ ምን ያህል ግንዛቤ እንደጨበጠ ለመገንዘብ ይረዱ ዘንድ የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም መምህሩ በተቻለው መጠን በየርእሱ መግቢያና መጨረሻ ላይ በተረበት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎቹ እንዲወያዩና መልስ እንዲሰጡ እንዲሁም እንዲጠይቁ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በዚህች አጭር የመማሪያ መጽሐፍ እንደባሕር የሰፋውን የፍጥረትን ታሪክ አካቶ ማቅረብ ባይቻልም ከአበው ሊቃውንት ቤተክርስቲያን ጥልቅና ምጡቅ የሆነ ትምህርት ለመረዳት፣ ልቡናን ለማትና ለማስፋት ያህል ከብዙ በጥቂቱ ለተማረው የሚያስፈልገው ንጥብ ቀርቧል። ትምህርቱን ሊያስተምር የተመረጠው መምህር በተማረው መመሪያ ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ የሥነ ፍጥረት መጻሕፍት በማንበብ፣ ሊቃውንቱን በመጠየቅ ዕውቀቱን ሊያሰፋና ለሚጠይቁት ሁሉ መልስ ለመስጠት እንዲቻለው መዘጋጀት ይጠበቅበታል።

ተማረውም እንደማንኛውም ሌሎች የቤተክርስቲያናችን ትምህርቶች ሥነ ፍጥረትን ለመማር የተጋ፣ የነቃ መሆን አለበት። አእላፍ ፍጥረታት ሥነ ፍጥረትን ለመማር የተጋ፣ የነቃ መሆን አለበት። አእላፍ ርዋኖም፥ አንአሳ ሙሴ ጸሊም እግዚአብሔርን ሰማወት፣ ለማምለክና ፈቃዱንም ለመፈጸም የቡቱት በሥነ ፍጥረት ተመራምረው ነው።



ቅዱሳት መጻሕፍትም "አሁንም እንስሳትን ጠይቅ ያስተምሩሀልና፣ የሰማይንም አዕዋፍ ጠይቅ ይነግሩሀልና፣ ወይም ለምድር ተናገር እርስዋም ታስተምርሃለች፣ የባሕርም ዓሣዎች ይነግሩሃል፣ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረጉ በማሰት ሥነ ፍጥረት እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ እንደሚመሩ ያስረዳሉ። ኢዮ.፲፪ ÷ ፯-፱።

መምህሩ የሥነ ፍጥረትን ታሪክ ከማስተማሩ አስቀድሞ ተማሪውም ከመማሩ በፊት ምሥጢረ ሥላሴን ማስተማርና መማር ያስፈልጋል። ይህ ሳይደረግ መጀመሪያ ወደ ሥነ ፍጥረት ታሪክ መግባት ግን እናቷን አታውቅ አያቷን ትናፍቅ የሚሉትን ዓይነት ይሆናል።

የሥነ ፍጥረትን ሂደት ተምረን ፈቃደ እግዚአብሔርን ፈጽመን ሰርስቱ ለመንግሥቱ ያብቃን፤ አሜን።

# ምዕራፍ አንድ

## ፩. ሥነ ፍጥረት

### ፩.፩ ትርጉም

ሥነ ፍጥረት የሚለው ቃል ሠነየ፣ ተሰነዐወ፣ እና ፍጥረት ከሚሉ ቃላት የተገኘ ነው። ትርጓሜውም፦ -

ሀ. የፍጥረት መፀደት፣ የበደ፣ ያመረ፣ የተዋበ ፍጥረት ማለት ነው።

"ወርአየ እግዚአብሔር ኵሉ ዘንብረ ከመ ጥቂ ሠናይ፣ እግዚአብሔርም ያደረገው የፈጠረው ያበጀው/ ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ።" ዘፍጥ.፩፥፴፩ እንዲል።

ሌ. የፍጥረት መስማማት፣ የተስማማ ፍጥረት ማለት ነው።

ፍጥረታት የተፈጠሩባቸው አራቱ ባሕርያት ኩሳት፣ ውኃ፣ መሬትና ነፋስ/ በባሕርያቸው የማይስማሙ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል ተስማምተው ስለሚኖሩ ነው።

"መአስተሰንዮሙ በበይናቲሆሙ እንዘ ዘዘዚአሁ ኃፀዘ ጠዛይዒሆሙ፣ የባሕርይ ጠባያቸው እየራሱ /የተሰ ያየ/ ሲሆን አርስ በርሳቸው አስማማቸው እንዲል ድጓሰን ዘቅዳስ ሮሐንስ።

### ፩.፪ ህልውና እግዚአብሔር

ህልውና፦ ሀለወ ከሚል የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አኗኗር፣ መኖር ማለት ነው። ህልውና እግዚአብሔር ሲልም የእግዚአብሔር አኗኗር፣ የእግዚአብሔር መኖር ማለት ነው።

እግዚአብሔር ለዘመኑ የጊዜ ቀመር አያቀመርለትም። በዘሁን ጊዜ ነበር በዘነገው ጊዜ ደግሞ አልነበረም አይባልም። እግዚአብሔር ከኅሳም (ከፍጥረት ሁሉ) አስቀድሞ መኖሩ



ይታወቃል እንጂ የኖረበት ዘመን አይቆጠርም። "እነሆ እግዚአብሔር ታላቅ ነው። አናውቀውምም። የዘመኑም ቁጥር አይመረመርም" ኢዮ ፴፮፥፳፮።

እግዚአብሔር ከዓለም በፊት እንደነበረው ሁሉ በመሰከረ ነበር። የዓለም አለመኖር ከእግዚአብሔር ክብር ሳይ የሚያሳድሰው (ያሳደሰው) ነገር የለም።

"እግዚአብሔር ከዓለም በፊት እስከ ዘለዓለም ድረስ በሦስትነቱ አለ። እግዚአብሔር በመለኮቱ እግዚአብሔር በመንግሥቱ አለ። ከንሳና ከጽባስ በፊት መላእክት ሳይፈጠሩ እግዚአብሔር በመንግሥቱ አለ። ሰማያት ሳይዘረጉ የየብስም ፊት ሳይታይ ሐመልማላት ሳይበቅሉ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ነበረ። ከፀሐይና ከጨረቃ ከከዋክብትም በፊት ከብርሃናትም መመላለስ በፊት እግዚአብሔር በመንግሥቱ ነበር . . ." ቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ኦቁዶ.ጵ፣ ቅዳሴ ዮሐንስ አፈወርቅ ከፅ. ፪.ገፀ።

"እግዚአብሔርስ ንጉሥ ውእቱ አምቅድመ ዓለም፤ እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው አንዲል። መዝ. ፸፫፥ ፲፪።

አንዳንድ የነገረ ሃይማኖት ሊቃውንት የእግዚአብሔርን ህልውና አስመልክተው ሲናገሩ "እግዚአብሔር ከጊዜ ውጪ ነው" ይላሉ። ይህም እግዚአብሔር ከመዓልትና ከሌሊት መፈራረት በፊት ጊዜና የጊዜ ቀመር ሳይፈጠር በነበሩ በልዕልናው መኖሩን የሚገልጥ አባባል ነው።

ይህ ሰዘመኑ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው እግዚአብሔር የአኗኗሩም ሁኔታ በበታ አይወሰንም። እግዚአብሔር በሚታ የውም ሆነ በማይታየው፣ በሚጻሰሰውም ሆነ በማይጻሰሰው ዓለም በሳይ ሰሰማይ፣ በታች በምድር፣ ከምድርም በታች እስከጥልቁ ጨለማ እስከ በርነርስ የሌለበት ቦታ የለም። እርሱ ምሉዕ በዙሪያዊ የሆነ አምላክ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር በዓለምም በዓለም ውጪም በሁሉ የመላ ነው። "ከመንፈስህ፣ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት አሸሽለሁ? ወደ ሰማያ. ብወጣ አንተ በዚያ ነህ። ወደ ሲዖልም ብወርድ በዚያ አለህ።



እንደንስር የንጋት ክንፍ ብወስድ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር በዚያ እጅህ ትመራኛለች። ቀኝህም ትይዘኛለች።" መዝ. ፻፴፰፥፮-፲።

መልመጃ ፩.፩

ሀ. እግዚአብሔር ከዓለም በፊት መኖሩ በምን ይታወቃል?

ለ. እግዚአብሔር የሌለበት ቦታ የለም ተብሏል። ለመሆኑ በሲዖል፣ ጋጢአት በሚሠራበት ሥፍራ ይኖራል ብላችሁ ታስባላችሁ? ተወ ያዩበት።

### ፩.፫ የሥነ-ፍጥረት ዓለማ

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሌፈጥር የኅሳ የተረዳ ዓለማ አለው። ይህም ዓለማ ትድስት ኑርበት ያንን ሊሞላ፣ ፍጥረቱ ክብር ሲሆኑት አይደለም። ከዓለም በፊትም እግዚአብሔር በሙሉ ክብር በመሉ ምሥጋና ነበርና።

ይህም "አምቅድመ አፍጥር ኵሉ ፍጥረተ ስብሐትየ ምስለየ ውእቱ፣ ፍጥረታትን ሁሉ ከመፍጠሬ በፊት ምሥጋናዬ ከእኔ ጋር ነበር ተብሎ በቀሌምንጦስ ተነግሯል።

ከፍጥረቱም በፊት በምሉዕ ምሥጋናው መሆኑን፦-

"አምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ሰቅዳሴ አሃ፣ ዘተጸርዐ ስብሐተ አብ፣ ወወልድ መመንፈስ ቅዱስ አሃ ምሉዕ ውእቱ፤ መላእክትን ሰምሥጋና ከመፍጠሩም በፊት የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምስጋናቸው የተቋረጠ አይደለም የሚሳ ነው እንጂ።" ቅዳሴ ዘሠለሱቱ ምእት ቁ. ፴፩።

ይህ ምሥጋናቸው ከሌላ አነል ወይም ፍጥር የተገኘ ሳይሆን ሥላሴን ባሕርያቸው ባሕርይቸውን ያመሰገንን ነበር።

"ሰብሐኩሃ ዘአምገዚሁ መውጽሌሁ አምዚአሃ. ምሉዕ ወፄአዎ ውእቱ ብዕለ ጸ.ገሥ፤ ከብር ከአርሱ የተገኘ ነው። ምሥጋና ውም ከአርሱ የተገኘ ነው። የጸ.ገሡም ብዕል ምሉዕና ፍጹም ነው። የሮሐንስ አፈወርቅ ቅዳሴ ቁ. ፲፫።



ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ሥጋዌው ከዓለም በፊት ምሉዕ የሆነ ክብር እንደነበረው ገልጧል።

"ወደእዜኒ አንተ አባ ሰብሐኔ በስብሐቴየ ዘሀሎ ምስሌከ አም ቅድመ ይትፈጠር ዓለም፣ አሁንም አንተ አባት ዓለም ሳይፈጠር ጠር ጀምሮ ከአንተ ጋር ባለ ጌትነቱ አክብረኝ ' ብሏል። ዮሐ. ፲፯፥፭።

እግዚአብሔር ዓለሙን የፈጠረበት ዓላማ፦ -

ሀ. ስሙን ቀድሰው /ከመስግነው/ ክብሩን መንግሥቱን እንዲወርሱ፣ ኤፌ. ፪፥፩።

ለ. የህልውናው /የመኖሩ/ መታወቂያ እንዲሆኑ መዝ.፻፫፤ ዕብ.፲፩፥፩፤ ሮሜ ፩፥፳ የሐዋ. ፲፬፥፲፯።

ሐ. ምግቡ ሥጋ፣ ምግቡ ነፍስ እንዲሆኑ፤

ምሳሌ፦ ምግብ ሥጋ፦ - አዝርዕቱ፣ አትክልቱ፣ ፍራፍሬው

ምግብ ነፍሱ፦ ከስንዴው፦ ቅዱስ ሥጋው ይዘጋጀበታል ከወይኑ፦ ክቡር ደሙ ይዘጋጀበታል

ዕጣኑ፦ መሥዋዕቱ ይታረገበታል

መ. መማሪያ ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ፣ መዝ.፻፰፥፩፣ ኢዮ. ፴፮፥፴፫፣ መዝ. ፵፯፥፮፣

ምሳሌ፦ - ምሥጢረ ሥላሴን፦ በፀሐይ

- ፀሐይ አንዲት ስትሆን ሦስት ነገሮች አሏት። እነር ሱም ክበብ፣ ብርሃን፣ ሙቀት ናቸው። ሦስት ፀሐይ ግን አትባልም።
- ሥላሴ በመለክት አንድ ሲሆኑ በአካል በስም በግብር ሦስት ናቸው።

❖ ምሥጢረ ሥጋዌን፦ በብርሃንና በጎይን መመሣሰር፦ በዓለም የመላው ብርሃን ከጎይን ብሌን ጋር ይዋሃዳል። ምልዓቱ ርቀቱ አይወሰንም። የጎይን ብሌን አትጠበውም። አደቆ ሬቁራትም። የጎይን ብሌንም ብርሃንን ተዋሕዶ የቅርከን፣ የሩቁን ታያለች። እንዲሁም አካላዊ ቃል ከምልዓቱ ሳይ ወሰን፣ ክብሩ ጌትነቱ ሳይቀነስ ሥጋ ሆነ። ሥጋም

በተዋሕዶ የቃልን ገንዘብ ገንዘቡ በማድረጉ የባሕርይ አምላክ ሆነ።

ቅ ምሥጢረ ትንሣኤ፦ በዘር ይቀር.ሃ፡-ፀ፩-፵፱፤ በፀሐይ መውጣትና መግባት፤

ዘር ይዘራል፣ ይበሰብሳል፣ ደግሞም ይበቅላል። የሰው ልጅም ይወሰዳል ይድጋል ይሞታል፤ በስተ መጨረሻም ነፍሱና ሥጋው ተዋሕደው ይነሣል።

ፀሐይ ጠዋት ትወጣለች። ቀኑን ሁሉ ስታበራ ውላ ማታ ትጠልቃለች። እንደጠሉቶች አትቀርም በሚቀጥለው ማለዳ ትወጣለች። ሰው ይወለዳል። የተፈቀደለትን ሥራ ሲፈጽም ይኖራል። ጊዜው ሲደርስ ወሐይ ዕድሜው በሞት ትጠል ቃለች። ሞቶ ፈርሶ በስብሶ ግን አይቀርም። በትንሣኤ ዘንባኤ በክብር ይነሣል።

እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ሲያስገኝ ያማከረው አካል፤ የረዳው ኃይል የለም።

"የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ ወይስ አማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ወይስ ከማን ጋር ተመካከረ? ወይስ ማን መከረውት ኢሳ.፵-፲፫ ሮሜ ፲፩፡-፴፬።

"ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ሰንኪ ያለ እርሱ አልሆነም።" ዮሐ. ፩ ፥ ፫።



## ሥሉስ ቅዱስ፦ የሥነ ፍጥረት ባለቤት




ሰዕል አንድ፦ ሥሉስ ቅዱስ



መልመጃ ፭፱

፩. የተፈጠራችሁበትን ዓላማ ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ ግለጡ? ይህንን ዓላማችሁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠበቅባችሁን ለመሙሉ ሀራችሁ ነገሩ።

፪. እግዚአብሔር ዓለሙን ከነመሳው ፍጥረቱ ባይፈጥር ኖሮ ምሥጋናም ክብሩ ምሉዕ ይሆናል ብላችሁ ታምናላችሁ? እስቲ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።

## ፭.፬ የሥነ-ፍጥረት መገኛ

መልመጃ ፭፪

፩. እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን በቃሉ ፈጠረ። አንዲት ሸክላ ሠሪ ደግሞ አንድ የከበረ ዕቃ ከሸክላ ሠራች። በማስገኘት ሂደት ላይ በሁሉቱ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን፣ የሚጸለሰ ውንና የማይጸለሰውን ዓለም (ፍጥረት) ያስገኘው የፈጠረው ከሁሉት ወገን ነው።

### ሀ. አምላክ አልቦ ገበ ቦ፣ ካለመኖር ወደ መኖር

እግዚአብሔር በሥልጣኑ፣ በልዕልናው ሲኖር ግሰ እርሱ ላዘጋጀው ዓላማ ፍጥረታትን ለመፍጠር አሰበ። በዚህም መሠረት በባሕርይው ባለች ሥልጣኑ ብርሃንን፣ መሬትን፣ አሳትን፣ ውቃን፣ ነፋስን፣ መላእክትና ጨለማን ፈጠረ። እነዚህ ፍጥረታት በእግዚአብሔር ሥልጣን የተገኙ ናቸው እንጂ ሌላ መገኛ የሆኑ ቸው ምክንያት የላቸውም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም "ዓለ ሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን" ብሏል። ዕብ.፲፩ ፥ ፫። ሮሜ. ፬ ፥ ፲፯።

### ለ. ፫ኅር እምንባር፣ ከተፈጠረው የተፈጠረ

እነዚህ ዳግም አራቱ ባሕርያት ሥጋ ከተባሉት ከመሬት፣ ከውኃ፣ ከንፋስና ከእሳት የተገኙ ናቸው።



**ሰምሳሉ፦** ምድር (መሬት) ዘርን የሚሰጥ ማርን፣ ቡቃያን በምድርም ላይ እንደወጡ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያ ፈራ ማፍን ታብቅል፡ ብሎ ባዘዘበት ሰዓት መሬት በእጅ የሚሰቀሙ፣ በማጭድ የሚታጨዱ፣ በመጥረቢያ የሚ ቆረጡ እዝርዕት፣ አትክልትና ዕፅዋትን አስገኘች። ዘፍ.፩+፲፩-፲፪

በዚሁ መሠረት ከባሕር ውኃ አደር ፍጥረታት፣ ከመሬት የብስ አደር እንስሳትና የሰው ልጅ ተፈጥረዋል። ዘፍ. ፩+፲፪-፳፮።

## ፭.፭ እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ያስገኘበት ሁኔታ

መልመጃ ፭፬

፩. እግዚአብሔር ይህን ዓለም አስገኝ ብላችሁ የምትገምቱበትን ሁኔታ አስቲ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አስረዱ።

እግዚአብሔር እምነበ አልቦ ያስገኛቸውንም ሆነ ከተ ፈጠሩት ላይ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ያስገኘበት መንገ አለው። ይኸውም በሦስት ወገን ነው።

### ሀ. በሐልዮ፦ ሐልዮ ማለት ማሰብ፣ ሐሳብ ማለት ነው። ይኸው ሲሠራው ሲፈጥረው የወደደውን ፍጥረት በአንደበቱ ቃል ሳይና ገር በኅሊናው ብቻ አስቦ በመፍቀድ በሥልጣኑ ያስገኛቸው ናቸው። እግዚአብሔር በሐልዮ ያስገኛቸው ፍጥረታት ሰባት ናቸው እነርሱም፦

- አራቱ ባሕርያተ ሥጋ
- ጨለማ
- ሰባቱ ሰማያትና
- መላእክት ናቸው

### ሐ. በነቢብ /በመናገር/፦ እግዚአብሔር በመናገር፣ ቃል በማሰማት ወይም በአንደበት ቃል በማዘዝ ብቻ የፈጠራቸው ፍጥረታት አሉ። እነርሱም በቁጥር አሥራ አራት ናቸው።

- ብርሃን
- ዐሰይ.

- ጠፈር
- ጨረቃ
- አዝርዕት
- ከዋክብት
- አትክልት
- ውኃ አደር የሆኑ እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ
- ዕፀዋት
- የብስ አደር የሆኑ እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ

ዘፍ. ፩÷፫፣ ፩÷፭፣ ፩÷፲፩፣ ፩÷፲፫-፲፭፣ ፩÷፳-፳፪፣ ፩÷፳፬፣

ሐ. **ፀጋውና ሽመራ፡-** እግዚአብሔር በሐልዮና በነቢብ ፍጥረታትን እንዳስገኘው ሁሉ በገቢርም ከሥራ ያስገኘው ፍጥረት አለ። ይኸ ውም አዳም ነው። በመጀመሪያ ሥላሴ ሰውን በመልካቸው ራሳ ቸውን አስመስለው ሰመፍጠር አንዲት የሆነች ፈቃዳቸውን ሳውን በመልካችን አንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ብለው ንለጡ። ዘፍ.፩÷፳፮። በዚህም መሠረት ሰውን ከምድር አፈር አበጀው ሠራው። በንቢር (በሥራ) ሰው የሚባለውን ፍጥረት ከምድር አፈር ፈጠረው። ዘፍ.፪÷፯።

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም "እጆችህ ሠሩኝ አበጁ ጁኝም" በማለት ሰው በእግዚአብሔር እጅ በንቢር መፈጠሩን ገል ጿል። መዝ. ፻፲፰÷፸፫።

ልዑል እግዚአብሔር በሐልዮ፣ በነቢብና በገቢር ሥነ-ፍጥ ረትን በማስገኘቱ በሁሉም መንገድ የወደደውን ነገር ማድረግ የሚቻለው መሆኑን እንረዳለን።

መመሪያ I. ለሚከተሉት ዐነገሮች ትክክል የሆነውን አውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ ሙ።

ፅ. የፍጥረት ሁሉ አስገኝ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
፪. እግዚአብሔር ሰዘመት ውሱንነት አለው።
፫. እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው ብሎ የተናገረው ነቢዩ ኢሳይያስ ነው።
፬. እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከፈጠረበት ዓላማ አንዱ ምድር ባዶ መሆኗን ስላየ ነው።
፭. ሰው የተፈጠረው ከፍጥረት ሁሉ በፊት ነው።



መመሪያ II. የሚከተሉትን ሐረጎች የ ሦን ሪፎ ከ ሳ ሪፎ ጋር አዛምድ (ሺ)።

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| ፩. አራቱ ባሕርያት | ሀ. ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት |
| ፪. ለዘለለም ሕይወት የተፈጠሩ | ለ. የእግዚአብሔር የህልውናው መገለጫዎች ናቸው። |
| ፫. ግብር አምንብር የተፈጠሩ | ሐ. ብርሃንና ሰው |
| ፬. ሥነ ፍጥረት | መ. መላእክትና ሰው |
| ፭. በሐልዮ የተገኙ ፍጥረታት | ሠ. የፍጥረት ሁሉ መገኛዎች ናቸው። |
| | ረ. ሰባቱ ሰማያት |

መመሪያ III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ (ጭ)።

፩. እግዚአብሔር ፍጥረታትን ያስገኘበት መንገድ ያልሆነው የትኛው ነው?
ሀ. በሐልዮ ለ. በመናገር
ሐ. በሥራ መ. መልስ አልተሰጠም

፪. ቀድሞ የተፈጠረው ፍጥረት የትኛው ነው?
ሀ. መላእክት ለ. ውኃ
ሐ. አትክልትና አዝርዕት መ. እንስሳት

፫. እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረበት ዓላማ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. የመኖሩ መታወቂያ እንዲሆኑ
ለ. መማሪያ ማስተማሪያ እንዲሆኑ
ሐ. ምግብ ሥጋ፣ ምግበ ነፍስ እንዲሆኑ
መ. ሁሉም



፬. "ከመንፈስህ ወዴት አሄዳለሁ?" የሚለው ጥቅስ የሚገኘው የት ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ኢሳ. ፮÷፩-፬ | ሐ. መዝ. ፻፴፰÷፮-፯ |
| ለ. ምሳ. ፩÷፮ | መ. ጻን. ፮÷፬ |

፭. ለምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ የሆነው የትኛው ነው?

| | |
|---|---|
| ሀ. ጨረቃ | ሐ. አዝርዕት፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ |
| ለ. ፀሐይ | መ. ውኃ፣ ሰማይ፣ ምድር |

መመሪያ IV. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አብራርተህ መልስ ስጥ (ጭ)።

፩. ሥነ ፍጥረት ማለት ምን ማለት ነው?
፪. "እግዚአብሔር ታላቅ ነው አናውቀውምም።" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህስ አባባል ምንን የሚገልጥ ይመስላችኋል?
፫. የአንተ መፈጠር ለእግዚአብሔር ምን ጎይነት ጥቅም ይኖረዋል?



# ምዕራፍ ሁለት

## ፪. አራቱ ባሕርያትና ጠባያቸው

አራቱ ባሕርያት የሚባሉት መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና እሳት ናቸው። እነዚህ አራት ነገሮች ባሕርያት የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸ ዋል። ባሕርይ ማለትም የነገር ዅሉ ሥር፣ መገኛ፣ መሠረት ማለት ነው። መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና እሳት የፍጥረት መገኛዎች በመሆና ቸው አራቱ ባሕርያት ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ አራቱ ባሕርያት የፈጣሪው የሆነ መለያ ጠባይ አላቸው።

አራቱ ባሕርያት እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ጠባያትን ሰለ ቸው። ይኸውም ለምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር በሥ ለት በህልውና፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ አንድ ሲሆን በስም፣ በአ ካል፣ በግብር ሦስት ነው።

ሀ. **መሬት**፡- አፈር፣ ትቢያ ማለ ነው። መሬት ጥሩ ከዘሩን ባትሰሥ ጽብር ትባል ነበር። ሞቃ ማለት ነው። ለፍጥረቱ ሁሉ ማደሪያ ትሆን ዘንድ በመሰጠቷ የሚሞ ምድር ተብላለች።

መሬት ሦስት ጠባይ አላት። እነዚህም ይዙበትን (ደረቱ መሆን)፣ ጽሉምነት (ጨለማንት)፣ ቀረርንት (መቀዝቀዝ) ናቸው

ሰ. **ውኃ**፡ - ከአራቱ ባሕርያት አንዱ የሆነው ውኃ ሦስት ጠባይትን አሉት። እነርሱም ብሩህነት (ብርሃን)፣ ርጠብነት (መርጠብ) ቀሪርንት ናቸው።

ሐ. **ነፋስ**፡- የነፋስ ጠባይትም ርጠብነት፣ ሙቁይነት (መሞቀ)፣ ጽሉም ነት ናቸው።

መ. **እሳት**፡- የእሳት ጠባይትም ሙቁይነት፣ ብሩህነትና ያልብነት ናቸው።

እነዚህ ባሕርያት ተጣምረውና ሰመሳሰላቸ ነቸው። ነፋስ መራ ትን ያጠበርቃሉ፣ ያለነሃቀሉ። መሬት ደግሞ ነፋስን ያገናዝባሉ። ውኃ እሳትን ሲያጠፋው እሳት ደግሞ ውኃን ያደርቅባል። እንዱ ለእንዱ ተቃራኒ ነው። ነገር ግን ከዓለ ከተዘረዘረው ጠባያቸው ውስጥ በእንዱ ይታረቃሉ።

**ሰውነታቸው**፦ ውኃ፣ ነፋስና መሬት ሲሟሉ አሳት፦ ከነፋስ ውውይነትን፣ ከውኃ ብሩህነትን፣ ከመሬት ይዙነትን ወስዶ ያስታርቃ ቸዋል።

በሰላ በኩልም ነፋልና መሬት ጥለኞች ናቸው። ነገር ግን ውኃ ከነፋስ ርጡብነትን፣ ከመሬት ቂሬርነትን ወስዶ ያስማማቸዋል። በዚህ ዓይነት ሂደት እስከ ፍጻሜ ዓለም ድረስ ተስማምተው ይኖራሉ።

አራቱ ባሕርያት በእግዚአብሔር ባሕርይ አራት ጠባያት አንጻሉ ያስረዳሉ።

**መሬት**፦ የእግዚአብሔርን ባሰጠግነት ያስረዳል። መሬት ሰለው ልጅ ሕይወት መሠረታዊ ፍላጎት የተባሉትን ምግብ፣ መጠለያና ልብስ ታስባሻለች። እንደዚሁ ሁሉ ልውል እግዚአብሔር የግያበድሩት ባሰጠጋ፣ ለሁሉ የሚበታ፣ የማያልት ሀብት ያለው፣ ምግበ ሥጋን ምግበ ነፍስን ለፍጥሬቱ ሁሉ የሚሰጥ አምላክ ነው። መዝ. ፻፵፭፥፮።

እንዲህም መሬት ታጋሽ ናት። ቢያርሷት፣ ቢቆፍሯት ቢገርፏት ለምን አትልም። ጻድቁንም ኀጥኡንም ሁሉን እንደየጠ ባዩና እንደ የምግባሩ ችላ ትናራለች። እግዚአብሔርም ታጋሽና ቻይ ነው። የፍጥረቱን ሁሉ ክፋት ኃጢአት ችሎ ታግሶ ይኖ ራል። ኃይል ሳለው እንደሌለው ሆኖ ይታገሳል። አያየ አንጻባየ ሆኖ አያውቀ አንጻላውቀ ሆኖ ያልፋል። "ኃያል ወመከተወሥሥ አንዲል። መዝ. ፯፥፲፫።

**ውኃ**፦ - የልውል እግዚአብሔርን ርኀራኄውንና ቸርነቱን ይገልጣል። ውኃ ያደፈውን ያጎሣል ያጠራል። የተጠማውን ያረካል። እግዚአብሔርም ሰው በኃጢአት ምክንያት ሕጉን ተላልፎ ሲኖር በኋላ ተጸጽቶ ንሰሐ ቢገባ በርኀራኄው በቸርነቱ ኩነ ጢአቱ፣ ክርኩሰቱ ያነጣዋል፣ ያጠራዋል። ዮሐ. ፫፥፴፮።

**ነፋስ**፦ የእግዚአብሔርን ፈቃሪነት ፈራጅነት ያሳያል። ነፋስ ፍሬን ከገሰባ ይለያል። እግዚአብሔርም በጻድቅ ፈራጅነቱ ጻድቃንን ከኃጥኣን፣ ኃጥኣንን ከጻድቃን ይለያል። ለይቶ ለለያንጻንፋ ከኃጥኣን፣ ኃጥኣንን ከጻድቃን ይለያል። ለይቶ ለለያንጻንፋ ዋጋውን እንደሥራው ይከፍለዋል። ኀጥኣን ኃጢአት



ሠርተው ባስቆጡት ጊዜ ጻድቃንን አብሮ አያጠፋቸውም። በፈራጅነቱ ለጻድቃን ፈርዶ ያድናቸዋል። ይህም ኖኅን በዘመኑ ከነበሩ ኀጥኣን፣ ሎጥንም ከሰዶምና ከገሞራ ኀጥኣን ለይቶ እንዳዳናቸው ማለት ነው። በዕለተ ምጽአትም እረኛ በጎችን ከፍየሎች እንዲለያቸው እግዚአብሔርም በፈታሒነቱ ጻድቃንን ከኀጥኣን ለይቶ የማታልፍ መንግሥቱን አውርሶ የዘላለም ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ማቴ.፳፭፤፴፫፤ ማቴ.ጽሩ፥፴፪፤ ዘፍ. ፯፥፩-፳፬፤ ፲፱፥፲፪-፳፮።

**አሳት**፦ አሳት የእግዚአብሔርን ክሣሊነቱን /ሁሉን ቻይነቱን/ ያስ ረዳል። አሳት ሲቀጣጠል ባሕር፣ ገሜል ካልከሰከሰው በቀር ርጥቡን፣ ደረቁን ያቃጥላል። እግዚአብሔርም ቸርነቱና ርኀራኄው ካልከሰከሰው በቀር ሁሉንም ሳጥፋ ቢል ይችላል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያቃጥል አሳት ነውና። ዘዳ.፬፡፳፬። ሲሠራው ወድዶ፣ ፈቃዱ ሆኖ እግዚአብሔርን ከመሥራት ከመፈጸም የሚያገደው ነገር የለም። "አስመ አልቦ ነገር ዘይሰእኖ ለእግዚአብሔር፣ ለእግዚአብሔር የሚሳ ነው ነገር የለም" ሉቃ.፩፥፴፯። "ወለአመቦ ዘፈቀድኦ ንግበር አልቦ ዘይክልእነ እምነሱ ፍጥረት። ወኢያእምረነ ሕሊና ጥባቢሆሙ ለመላእክት፣ ለመሥራት ብንወድ ክፍጥረት ወገን የሚከለክለን የለም። የመላእክት የሕሊናቸው ጥበብ አያውቀንም" ያለው ቀሌምንጦስ።



## መመሪያ I. ለሚከተሉት ዐነገሮች ትክክል የሆነውን አውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት ብለህ ጻፍ (ፊ)።

ሰ. አራቱ ባሕርያት የሚባሉት ነፋስ፣ ነባቢነት፣ ለባዊነትና ሕያዊነት ናቸው።

፪. ውኃ የልውል እግዚአብሔርን ርኀራኄውንና ቸርነቱን ይገልጣል።

ሮ. እግዚአብሔር በመሰኮት በሀልውና በሥልጣን በአንዝህ አንድ ሲሆን በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ነው።

## መመሪያ II. በ"ሦ ረድፍ ያሉትን ቃላት ከ"ሰ ረድፍ ካሉት ቃላት ጋር አዛምድ።

| ሀ | ቤ |
|---|---|
| ፩. መሬት | ሀ. ብሩህነት |
| ፪. ነፋስ | ለ. ቂሬርነት |
| ፫. አሳት | ሐ. ውውይነት |
| ፬. ውኃ | መ. ይዙነት |

## መመሪያ III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ (ጭ)።

፩ ንክክል የሆነው ነው '

ሀ ነፋስ መሬትን ይጠርገዋል፣ ይሰነጥቀዋል

ለ. ውኃ አሳትን ሲያጠፋው አሳት ደግሞ ውኃን ያደርቀዋል

ሐ. መሬት ነፋስን ይገድበዋል

መ. ሀ ሳም

፪. "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" የሚለው የሚገኘው የት ነው?

ሀ. ሉቃ.፩፥፴፯ ለ. መዝ.፩፥፩ ሐ. መክ. ፻፪፥፩ መ. ዮሐ. ፩፥፬

ሮ. የእግዚአብሔርን ባሰጠግነት የሚያስረዳው

ሀ ውኃ ለ. መሬት ሐ. ነፋስ መ. አሳት



፬. "ለመሥራት ብንወድ ክፍጥረት ወገን የሚከለክለን የለም። የመላእክት የሕሊናቸው ጥበብ አያውቀንም" ያለው

ሀ. ጻደቡቆርስ ለ. አትናቴዎስ

ሐ. ቀሌምንጦስ መ. ፊልክሰዩስ

## መመሪያ IV. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጠር ያለህ መልስ ጠ።

፩. አራቱ ባሕርያት አሥራው ፍጥረታት ይባላሉ። ለምን?

፪. አራቱ ባሕርያት የተባሉትን ሁለት ሁለቱን አስታርቋቸው።

- መሬትና ነፋስ፣ አሳትና ውኃ ቢጣሉ እንዴት ይታረቃሉ?

፫. አራቱ ባሕርያት ከነገረ እግዚአብሔር አንጻር ያላቸውን ምሳሌነት ግለጽ።

፬. ሕዝን ሆነህ ትፈጥን የነበረው፣ ውጣት ሆነህ ደግሞ በቀላሉ የምትናደደው ለምን የተነሣ ይመስልሃል?

# ምዕራፍ ሦስት

## ፪. የስድስቱ ቀናት ፍጥረታት

መልመጃ ፪.፩

ፋ. ተማሪዎች ፍጥረታት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ የተፈጠሩ ይመስላ ችኋል?

፪. በቀለም ትምህርታችሁ ዓለም በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት ዕድሜ እንዳላት ተምራችኋል። በሃይማኖት ትምህርት ስታዩት ይህ ትምህርት ምን ያህል ተቀባይነት አለው?

፫. ዓለም በአዝጋሚ ለውጥ ሳለመገኘቷ አስቲ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቡና ተወያዩበት

እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ያስገኘው በስድስት ቀናት ውስጥ ነው። ይህም በአንድ ቀን ለመፍጠር አቅም አጥቶ አይደለም። እርሱ ባወቀ ሁሉን በሥርዓትና በአግባቡ ሰማይሪን ብሎ አንጂ። ደግሞም ፈቃዱና ጊዜውም ስለሆነ ፍጥረታትን በስድስት ቀናት ውስጥ አከናወነ።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር መላውን ሥነ ፍጥረት በአንዲት ቀን ፈጠረ፤ ነገር ግን ነቢዩ ሙሴ የረዥሟ ፍጥረትን ታሪክ ሲጽፍ ስድስት ቀናትን የዘረዘረበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ጥበብ፣ አስደናቂ ዝግጅቱንና ሥነ ሥርዓቱን ለማሳየት ነው ይላሉ። ይህ ግን ትክክል አይደለም።

ሙሴ የፍጥረትን ታሪክ የጻፈው መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ያለውን የተደረገውን ነገር በትክክል ገለጠለት እንጂ ግራ ሊያጋባ የሚችል ነገር አይገልጥም። በተጨማሪም ይህ አባባል እግዚአብሔር ፍጥረቱን በአንድ ቀን ፈጥሮ ሳለ ሙሴ ስድስት ቀን ከፋፍሎ ለማስረዳት ለማሰየት ስድስት ቀን ቆጠረ ማለት ሙሴ ከእግዚአብሔር ካገኘው ዕውቀት በተጨማሪ የራሱን ሥጋዊ አስተሳሰብና አቀራረብ ተጠቅሟል ያሰኛል። ይህ ከሆነ ደግሞ ተቀባይነት አይኖረውም።



ሌሎች ወገኖች ደግሞ እግዚአብሔር የፍጥረትን ንጥረ ነገሮች ከፈጠረ በኋላ በሚቀጥሉት ቀናት ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ አደረገ ይላሉ። ይህም ሸክላ ሠሪ መጀመሪያ መደብ ሠርታ፣ ሸክላውን ፈጭታ አቡክታ በስተመጨረሻ የወደደችውን ዓይነት ዕቃ እንደምት ሠራ ማለት ነው። ይህም ስህተት ነው። እግዚአብሔር በየዕለቱ የወደደውን ፍጥረት በሐሳቡ፣ በነቢብና በገቢር ይሁን ብሎ ከመፍጠሩና በፈጠረበት ዕለት ሥርዓት እንዲይዙ ከማደረጉ ውጪ ሌላ ውጣ ውረድ አልነበረበትም። በባሕርዩ ባለች ሥልጣን የወደደውን ፈጠረ። የተፈጠረውም ፍጥረት ብቃትና ሥርዓት ያለው ፍጥረት ነው። "አስመሙ ውኆቱ ይቢ ወከኑ፣ ወውኆቱ አዘዘ ወተፈጥሩ ወአቀምሙ ለዓለም ወሰዓሰመ ዓለም ትእዛዘ ወሀለመ ወኢኀለፉ፣ አሉ ይፈጠሩ ብሏልና ሆኑ እነርሱም ተፈጥረዋልና ለሰለዓለሙ አጸናቸው ሥርዓት ሠራላቸው መሰን ወሰነላቸው። ከሠራላቸው ሥርዓት አልወጡም ከወሰንላቸውም መሰን አላለፉም።" መዝ.፻፵፰፥፭። ትርጓሜውን ተመልከት።

ሦስተኛም ሥነ-ፍጥረት እንደተፈጠሩባቸው የተጠቀሱት ስድስት ዕለታት ቀናት ሳይሆኑ በብዙ ሺህ ዘመን የሚቆጠሩ ዓመታት ናቸው የሚሉም አሉ። ከእነዚህም አንዳንዶቹ "ቀን" የሚለው ቃል ሃያ አራት ሰዓት ብቻ አለመሆኑን ለማስረዳት የቀንን ትርጉም በተለያየ መንገድ ያቀርባሉ። ለምሳሌ "እግዚአብሔር አምላክ ሰማይና ምድርን ባደረገ ቀን በተፈጠሩ ጊዜ የሰማይና የምድር ልደት ይህ ነው" በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሰው "ቀን" ጊዜ" የሚያሳዩት አንድን ቀን ሃያ አራት ሰዓታት ስፍር ያለውን ዕለት ሳይሆን በመቶና በሺህ ለሚቆጠሩ ዓመቶች የተሰጠ ቃል ሊሆን ይችላል ባዮች ናቸው።

በመሠረቱ ይህ አባባል መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። በዘፍጥረት ፩፥፩ ላይ የተጠቀሰው "ቀን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በመቶና በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን የሚያሳይ ሳይሆን እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን የፈጠረበትን የመጀመሪያይቱን ቀን የሚያመለክት ነው። የሚሄ ቁጥሮች ሁሉ በምድር ላይ ገና አልነበረም ሲል ሰማይና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት እንዳች የተፈጠረ ፍጥረት አለመኖሩን ያሳያል።



"ቀን የተባለው ብዙ ዓመታትን እንጂ አንድን ዕለት አያሳይም" ማለት በመጀመሪያ እግዚአብሔር ፍጥረቱን የፈጠረው በሂደት እያ ፈፈ ነው ያሰኛል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰ ባተኛው ቀን ፈጸመ። በሰባተኛውም ቂን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ ካሰው ቃለ እግዚአብሔር ጋር አይስማማም። ቀን የሚለው ብዙ ዓመ ታትን የሚያሳይ ከሆነ እግዚአብሔር ዐረፈበት የተባለው ሰባተኛው "ቀን" የትኛው ነው? በሁሉተኛ ደረጃም ዓለም በአዝጋሚ ሂደት ተገኘች ወደሚለው ፍልስፍና ያመራል። ዘፍ.፪÷፪።

ሙሴ በጻፈው የፍጥረት ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ስድስት ዕለታት እኩል መዓልትና ሌሊት ያላቸው ሃያ አራት ሰዓታት የሚቆ ጠርላቸው ናቸው። ይህንንም ለመረዳት በኦሪት ዘጸአት ፴፥፲፮ ላይ የተጠቀሰውን መመልከት በቂ ነው። "ሳዝዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ባሕርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛውም ቀን ዐርፎአልና።" ከዚህ በተጨማሪም እግዚአብሔር በአምላክነቱ ቀን ያዘጋጀውን /ያሰበውን/ ፍጥረት ከፈጠረ በኋላ መልኩም መሆኑን ግለት የበቃ፣ ብቃት ያለው ፍጥረት መሆኑን እንዳየ ከተገለጠ በኋላ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንደኛ ቀን፣ ሁለተኛ ቀን፣ . . . በሚለው ውስጥ ቀን የተባለው ዕለት ሃያ አራት ሰዓታት ያሉት መሆኑን ያስ ረዳል። እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ከፋፍሎ በሉልን፣ በነቢብና በገቢር ካሰመሮር ወደመሮር ሥነ ፍጥረትን ማስገኘቱ ከሃሊነቱን ያስ ረዳል። ከዚህ ውጪ ግን በመቶና በሺህ በሚቆጠሩ ዓመታት ልዩነት ፍጥረታትን ፈጠረ ማለቱ የትኛውንም የእግዚአብሔርን ጠባይ የማይ ገልጥ ከመሆኑም በላይ ሁሉን ቻይነቱን የሚነክ ነው።

ከዚህ፣ በተጨማሪ በአሁኑ ዘመን ስለ ዓለማት ጥንትና መገኛ እንዲሁም ስለወደፊቱ ዕጣ ፈንታቸው የሚያጠኑ ፈላስፎች ብዙ ናቸው። በዚህ መስክ ስፍና ጥልቅ ጥናት የሚያካሂዱት ኮስሞ ሎጂስቶች (Cosmologists) ሲባሉ ሳይንሱ ደግሞ ኮስሞሎጂ (cosmology) ይባላል።

ይህ ሳይንስ ብዙ ዕድገት ካሳዩትና በየጊዜው አዳዲስ ግኝቶችን ከሚያሳውቁት የምርምር ውጤቶች አንዱ እንደሆነ ይታመናል። ይህም ትናንት ሰለዓለም ጥንትና ሁኔታ ስለወደፊት ሁኔታም ሲነገር



የነበረውን በአዲስ ግኝት እየሻረ አዲሱን ወደ አርኒነት /በጥናትና ምር ምር/ አስኪሚቀይር ድረስ እውነት ነው ብሎ የሚያቆለምጥ መሆኑን ያስረዳል። ለአብነት ያህል በ፳ኛው ክፍለ ዘመን የሚታወቀው የአልበርት አንስታይን (A.Enstien) ሐሳብ (model) እንኳ ሳይቀር ጊዜውን ጠብቆ ወድቋል። በጊዜው ያለው የምርምር ውጤትም ተቀባይነቱ በሌላ አዲስ ግኝት (New Scientifical Discovery) እስካልተተካ ድረስ የመቀበል ሳይንሳዊ ግዴታ ስላለበት ብቻ ነው። ይህም የቀደመውን መሠረት አድርገው አዲስ ምርምር በማድረጋቸው ይታወቃል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚያመለክቱት በሳይንሱ ዓለም "እርግጥ" (Always true) ሆኖ የሚኖር ነገር በጣም አነስተኛ መሆኑን ነው። በዚህ መሠረት ከሥነ ፍጥረት ጋር ያለውን ነገር ለመረዳት በዚህ ዘመን ተቀባይነት አግኝቶ በትምህርት የሚሰጠውን አንድ ሞዴል ወይንም የቀመር ትንታኔ እንመለከትና በሥነ ፍጥረት ትምህርት እንመዝንዋለን።

**ፕሩብል ሕግ (Hubble's law)**

ይህ ሕግ የሚጠራው ምርምሩን ባገኘው ፈላስፋ ስም ነው። የፈላስፋው ሐሳብ በሚል ልንመለከተው እንችላለን። ሹብል አያንዳ ንዱ ዓለም (Planet) ከተገኘበት መሐል ወደ ጻር ያለማቋረጥ በመፃዝ ይናራል፣ አንዱ ከሌላው ሁልጊዜም ይርቃል። ለምሳሌ መሬትን አንደ መሐል ብንቆጥራት ሁሉም ፕላኔቶች ከመሬት በመራቅ ላይ ናቸው የሚል አመለካከት (ሕግነት) አለው።

በዚህ ሐሳቡ መሠረት ሁሉም ዓለማት፣ ከዋክብትና ጨረሮች (all planets, stars and radiations) ከመሊያቸውም በሬት አንድ ላይ በትንሽ ኳስ ቅርጽ በትልቅ እፍግታ (with big density) የነበሩበት ጊዜ ነበር ይላል። ከዚህ በመነሣትም ለዓለማት ጥንት (origin) እንዴት እንደተ ገኙና ወደፊት ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ያለውን አመለካከት እንደ ሚከተለው እንመለከታለን።

ሀ. **የኳስነት መንጭ**:- ሹብል የሁሉም ነገር መኖና ከጥንታዊ (የመጀ መሪያ) አካታዊ ኳስ መሰል ነገር (Primordial fire ball) ነው ይላል። እንደ እርሱ ሐሳብ ይህ የመጀመሪያ (Existing from the


beginning) አሳታዊ ኪስ ሁሉንም ቁስ (all matter) ማንኛውንም ጨረር፣ ከፍተኛ መጥተና በትልቅ አፍንታ ብዙ ጉልበት (Energy) ነበረው። ሁሉም ዓለማት፣ ከዋክብትና ሌሉችም ነገሮች በዚህ ውስጥ ታምቀው በአንድነት ነበሩ ይላል።

ለ. **እንዴት ተገኙ (How they come in to existence)**

አሁን በምናውቅበት ቅርጽና መልክ፣ ሁኔቴና ይዘት እን ዴት ተገኙ? ለሚለው ደግሞ ምክንያቱ ፍንዳታ (Explosion) ነው ይላል። ይሄንንም ፍንዳታ ቢግ ባንግ (Big-Bang) ይለዋል። ድንገተኛ ሆኖ አጀማ ታላቅ በሆነ ድምጽ የፈነዳ ግለት ነው። በዚህ ቢግ ባንግ ዓለማት (Planets)፣ ከዋክብት (Galaxy) እና ሌሉ ችም ተገኙ ይላል። ከዚህ በኋላ በተከሄደው አገጋሚ ለውጥ (Evolution) ሁኔታዎች እየተሰየመ፣ ሕይወት ያላቸው ነገር ችንም እስከ ማስገኘት ደረሱ ይላል። በዚህ መንገድ ስለ አያን ዳንዱ ነገር ግኙት ሲተርክ ሁሉም ነገር ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል ብሎ ያምናል። ስለሰውም መነሻ ሲናገር ሰው ከዋክብት ሲገኙ ከሚፈጠረው አመድ የተገኘ ፍጡር (from ashes of star formation) ነው ይላል።

ሐ. **የወደፊት ሁኔታ (future of the universe)**

ስለወደፊቱ ሲናገር ደግሞ ሦስት መላምቶችን ያስቀምጣል። አዝዚም በስበት (gravity) እና አፍንታ (density) መሠረት እንደሚሆኑ ይናገራል። ይህንንም የመጀመሪያውን ፍንዳታ (the Big Bang) መነሻ አድርጉ በጠታ - ጊዜ (Space- time) ሰንጠረዥ ያስረዳል።






የዓለምን የወደፊት ሁኔታ ከላይ በተቀመጠው በታ-ጊዜ (Space-time) ከርብ (curvature) መሠረት ሦስት ሁኔቶች ይኖራቸዋል በማለት ግምታቸውን ያቀርባሉ። ትንታኔውን እንደሚከተለው እናቀር በዋለን።

ፅ. የሰንጠረዡ የኩርባው (the curvature) በቁጥር አንድ እንደተመለ ከተው አሉታዊ (-ve) ከሆነ የዓለማት መስፋፋት (Expansion of the universe) የሚቴተል፣ ከፍተኛና ፍጻሜ የሌለው (opened infinite) ይሆናል ይላሉ።

ፀ. በቁጥር ሁለት እንደተመለከተው ዜሮ (Zero) ከሆነ ደግሞ ዓለም (Universe) ጠፍጣፋና ፍጻሜ የሌለው (flat and infinite) ይሆናል ይላሉ።

ተ. በቁጥር ሦስት እንደተመለከተው አዎንታዊ (+ve) ከሆነ ደግሞ ዓለም ዝግና ውስን (closed and finite) ይሆናል። መስፋፋቱም ያቆምና እንደገና ወደ አንድ ኪስ መሰል ቅርጽ ተቀይራ ሌላ ቢግ ባንግ (Big Bang) ይገጥመዋል ይላሉ።

የዓለም ዝግና ክፍት መሆን የሚወሰነው በአፍንታ ጥምር ነው በማለት ሌሉች ሦስት መላምቶችንም ያቀርባል። ይህ ለው ራሱን የቻለ ቀመር አለው፣ ብዙ ትንታኔዎችም አሉት። ከሥነ ፍጥረት አንጻር ግን በዚሁ አንወሰንና ትንታኔዎቹን ወደ መመዘን እንሂዳለን።

ከላይ የተመለከትናቸውን ሳይንሳዊ ትንታኔዎች አውነት ነው ብሎ የተቀበለ ክርስትናንስ መቀበል ይችላልን? አስኪ በጥያቄ አንመርምራቸው።

- Big Bang (ቢግ ባንግ) ፍንዳታ ከመነሄዱ በፊት የነበረው አላ ታዊ ኪስ መሰል (Primordial fire ball)) ከየት ተገኘ አሰንጂ ውስ ምንድን ነው? ለሚሉት የነገሮች ጥንት ጥያቄ ይህም ሆነ ሌሉቶ ሳይንሰች መልስ አላቸውን?

ሀ. Big Bang (ታላቁ ፍንዳታ) ሲከሄድ ማን ነበር? ስፈላስፎቹ አስረጻ ቸው ማን ነው? ምክንያቱም አንደ አነርሱ ሐሳብ ከታላቁ ፍንዳታ



(Big Bang) አንድ ቢሊዮን ዓመታት በኋላ ደመናዎች ተገኙ፣ ከ፱ ቢሊዮን ዓመታት በኋላ ደግሞ መሬትና መሰል ዓለማት (Planets) ተገኙ። ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ ደግሞ ቀስ በቀስ በአዝ ጋሚ ለውጥ (Evolution) ሕይወት ያላቸው ነገሮች ተገኙ ስለ ሚሉ ከ፱ ቢሊዮን ዓመታት በፊት ያለውን ማን አየ? መሆኑንስ በምን ያስረግጣሉ?

ለ. በቤተ-ሙከራ (in the laboratory) ተገንዘብነው ካሉ ደግሞ ሁኔታ ውን በዚሁ በቤተ-ሙከራ ሠርተው ማሳየት ለምን አልቻሉም?

ለመሆኑ ከላይ ያየናቸው ነገሮች የተረጋገጡ (proved) መሆናቸውን ማሳየት የሚቻለው ማን ነው? ይሆናል ከሚል ሐሳብ በቀር እምና ከመቀበል በቀር በምን አርግጠኞች ነን? በአጭር ቃል በየትኛውም የአዝ ጋሚ ለውጥ (Evolution) ሂደትና የክሳሞሎጂ (Cosmology) ምርምር መላምቶችና አስተያየቶችን መሠረት ያደረገ እምነት አንጂ ማስረገጫ (Proved principlcs) ማቅረብ አይቻልም።

ይልቁንም ሕይወት ስላላቸው ነገሮች የሚያጠናው የሳይ ንስ ክፍል ሥነ ሕይወት (Biology) የሚለውን ነገር መመልከቱ ግልጽ ሊያደርግልን ስለሚችል እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለ ከተዋለን።

## ጥንተ ሕይወት (Origin of life) በሥነ ሕይወት

ብዙ የሥነ ሕይወት ሊቃውንት ሕይወት ያለው ነገር እንዴት ጀመረ? ለሚለው ጥያቄ ጥልቅ ምርምር በማካሄድ የተቻሉ ቸውን ሁሉ ተፈላስፈዋል። ነገር ግን ከመላምት (Hypothesis) አለ ፋም። ጄሊያን ሳቱን /Julian Sutton/ የተባሰ የሥነ ሕይወት ሊቅ በጻፈው የሥነ ሕይወት (Biology) መጽሐፍ ገጽ ፬፪ ላይ ጥሪት (ታሪክ) አልባ ከመሆን ባለጥራዝ ነጠቅ ተሪት (ታሪክ) ባለቤት መሆን ይሻላል፣ ባዶ አእምሮ /ችውቀት አልባ/ ከመሆንም የሚሠራ መላምት ይሻላል። Asketehy story is better than no story at all, working hypothesis is better than an empty mind." በማለት አስክሁን ያለውን የሥነ ሕይወት ምርምር ስለጥንተ ሕይወት /Origin of life/



ባዶ ከመሆን ወይም ምንም ካለመናገር የተሻለ መላምት እንደሆነ አስተምጠንታል። ይህንም ያለኸው ምን እንደሆነ ሲገልጽ የዚህ ምር ምር ሰዎች ሕይወትን ከአዝ ጋሚ ለውጥ መጣ ያለኛቸው የራይቦኒ ውክ ሊክ አሲድን /RNA/ በቤተ-ሙከራ /Labratory/ ማባዛት መቻ ላቸው ቢሆንም በዚሁ በቤተ ሙከራ (RNA) ከዚህ መባዛት /Replic-ation/ ሕይወት ያለውን ነገር ማስገኘት አልተቻለም። ይህ ሁሉ እንደ ሚደረግ የሚታሰበው ደግሞ በምድር ላይ ሆኖ ሳለ ሕይወት ከመ ሬት ውጭ ልትገኝ እትችልምን? ለሚለው ጥያቄ ምንም ዓይነት ሐሳብ /Idea/ ወይንም መልስ መስጠት የሚችል አለመኖሩ በአንርሱ በተማራማሪዎቹ ዘንድ አስክሁን ያለው ሁሉ ከመላምት /Hypothesis/ ወይንም ግምት የማያልፍ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። አኒሁ ለው ስለዚህ አሁን ስላለው የሥነ ሕይወት አዝ ጋሚ ለውጥ /Biological Evolution/ ሲናገሩም ምንም ዓይነት ሕይወት ሳይኖር ምን ተደርጉ ሕይወት መጣ? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠውን መላምታዊ ትንታኔ መናገር የተቻለው ቀድመን ሲሆን ይችላል በሚል ሕሊናችንን ስላላመንነው ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ።

ስለዚህ በየትኛውም የምርምር ዘርፍ የምንመለከታቸው አስተሳሰቦች እንኳን በራሳቸው "ሃይማኖት" ናቸው። ሃይማኖት ተብለው የማይጠሩት ግን ስለ ሁለት ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። እነዚህም የመጀመሪያው ሐሳቡ ከሃይማኖት መጻሕፍት የተቀዳ ባለመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሐሳቡ አቀራረብ በተመክራን መነሻ አድርጎ የሚቀርብ የላይንስ ሐሳብን ሥርዓት /Principle of labratorical Science/ የተከተለ በመሆኑ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ በዚህ መንገድ ለመምጣቱ ማንም ማን እስክሁን እርግጥ የሆነ ማስረጃ የለውም። ይህም የፈጣሪን ሥራ ራሱ ካለገለ ጠው በቀር ሊደርስበት የሚችል ፍጡር እንደሌለ ያረጋግጥልናል። እንኳን ፍጡር ፈጣሪውን ሊያውቅ ቀርቶ የለው የሥራ ውጤት የሆነው ኮምፒውተርም /Com-puter/ ሠሪውን ሊያውቅ አልቻለም። ከኮምፒውተር የምንወስደው ሁሉ በሰላ ሰው የተሠሄነ (Load) የተደረገ እንጂ ከራሱ ከቁስ አካሉ የሚገኝ እንዳልሆነ ሁሉ የፈጣሪ ሥራም ሊታወቅ የሚችለው ፈጣሪ ለፍጡሩ አውቀት ሲሰጥ ብቻ ነው።

ከዚህ ቀጥሎን እግዚአብሔር በስድስቱ ዕለታት የፈጠራቸውን ፍጥረታት በቅደም ተከተልና በዝርዝር እንመለከታለን።

## ፪.፩ የዕለተ አሑድ ፍጥረታት

### ፪.፩.፩ ትርጉም፦

አሑድ የሚለው የዕለት ስም አሐደ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። አሐደ ማለትም አንድ አደረገ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። አሑድ ማለትም አንድ፣ አንደኛ፣ መጀመሪያ ማለት ነው። የዕለታት አንደኛ መጀመሪያ አሑድ ናት። እግዚአብሔር ከብሩ አንዲገለጽና አንዲመለክን ፍጥረትን መፍጠር የጀመረበት ዕለት ዕለተ አሑድ ትባላለች። የመጀመሪያዋ ዕለት ማለት ነው። ዮሐ.፩.፩ ፬ ÷ ፲፭።

### ፪.፩.፪ የአሑድ ሰዓተ ሌሊት ፍጥረታት

እግዚአብሔር በዕለተ አሑድ በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት አራቱ ባሕርያት የተባሉትን መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስ፣ እሳትን ፈጠረ። የፈጠራቸውም ከምንም ተነሥቶ (ካለመኖር) በሐልዮ በማህዝ ብቻ ነው። "የሌለውንም አንዳለ አድርጎ በሚጠራ . . . ተባሉ አንደተነገረው ካለመኖር መኖርን አስገኘ። ሮሜ.፬÷፲፯። አዝዘ አራቱ ባሕርያት ሲፈጠሩ ዛሬ በዓለም መልተው አንዳሉ ምልዓት ስፍሐት አልነበራቸውም። አስቀ ድሞ ጥቂት መሬት፣ ጥቂት ውኃ፣ ጥቂት ነፋስና ጥቂት እሳትን ፈጠረ። ከፈጠራቸው በኋላ "ከአድማስ እስከ አድማስ መሉ" ብሎ በሐልዮ (በአርምሞ) ቢያዘቸው በከሃሊነቱ ጸኑ። በዚሁ ሰዓት አምስተኛ ፍጥረት ጨለማን ፈጠረ። ". . . ምድርም ባዶ ነበረች። አንጻችም አልነበረባትም ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር።" በዛ. ፩÷፪።

ጨለማ አይዳሰስም። በጨለማ ውስጥ ያለ አይታወቅም። አይመረመርም። ይህም የእግዚአብሔር ባሕርይ መለኩዙ የማይመረመር የማይደረስበት መሆኑን ያሳያል። "መሰወሪያውን ጨለማ አደረጎ" መዝ. ፲፯÷፲፩።



ከሁለተኛው ሰዓተ ሌሊት እስከ ዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት አሳት ዋዕዩን /ሙቀቱን/ ማቃጠሉን/ ትቶ ብርሃኑን ነሥቶ /ወስዶ/ ሰባቱን ሰማያት ፈጠራቸው። ሰባቱ ሰማያት የሚባሉትም ራማ፣ ኤረርና ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ናቸው።

- **ሰማይ ውዱድ**፦ ኪሩቤል የተሸከሙት የሥላሴ ዙፋን ነው።
- **መንበረ ስብሐት**፦ - ይህች ሰማይ አሠራሯ አሬት ማዕዘን ቅርፅ ያላት ናት። መጠኗም ከላር እስከ ላር የማይደርስ መጠነኛና ይህችን የምንኖርባትን ዓለም ያህል። ሥላሴ ለቅዱሳን በፈለጉት መልክ የሚታዩባት፣ የሚገለጡት በዚህች ሰማይ ሆነው ነው። ዘፍ. ፴፰÷፲፪-፲፮፣ ኢሳ.፮÷፩።

እግዚአብሔር መንበረ ስብሐትን ፈጥሮ ሲያበቃ በሰዓተ የሌሳት መጋረጃ ጋረጳት፣ በሰባት የሌሳት አጥር አጠራት።

- **ጽርሐ አርያም**፦ ከሰማያት ሁሉ በላይ የሆነች ሰማይ ናት። መጠኗ ኗን ጻሬን ከፍጡራን ወገን የሚያውቅ የለም። እግዚአብሔር ጽርሐ አርያምን የፈጠራት ከአሳት ብርሃኑን ጨምቆ፣ ብርሃኑን አጥርቶ ብፋሀ አድርጎ ነው።
- **አድር፣ ራማ፣ ኤረር** - እነዚህ ሦስቱ ሰማያት ዓለመ መላእክት፣ የመላእክት ከተሞች ይባላሉ። ብርሃናውያን ሰማያት ሲሆኑ ከአድ ማስ እስከ አድማስ የተዘረጉ ናቸው። የአድር ወሰን ከሰማይ ውዱድ ወሰን፣ የራማ ወሰን ከአድር ወሰን፣ የኤረር ወሰን ከራማ ወሰን ጋር የተጋጠመ ነው። ሦስቱም በሰባት የሌሳት መጋረጃ የተ ጋረዱ፣ በሌሳት አጥር የታጠሩ፣ ወርቫችውና ቁመታቸው ትክክል የሆኑ ናቸው።
- **ኢየሩሳሌም ሰማያዊት**፦ - አንደ ቤተመቅደስ አራት ማዕዘን ያሳት ናት። ፲፪ በሮች አሏት። ምሰሶዎቿ፣ ክዳኗ፣ መርገፏ ሁሳንተናዋ ብርሃናዊ ነው። የአመዜታችን ምሳሌ የሆንችውና ክብርህን የተቀ ረጸችው ታቦት ዘለር የምትገኘው በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ነው።

በዘጠነኛው ሰዓተ ሌሊት መላእክትን ካለመኖር ወደ መኖር አስገኘ። የመላእክት ተፈጥሮአቸው አምኃ አልቦ ካለመኖር ነው።



አንዳንድ መጻሕፍት (መዝ.፻፫ ÷ ፬፣ ዕብ.፩÷ ፯፣ ድርሳነ ሚካኤል ዘገዳር) መላእክት ከአሳትና ከነፋስ አንደተፈጠሩ ይናገራሉ። ይሁን አንጂ የቆድሮስ ደሴት ኤጲስ ቆጳስ የነበረው ኤጲ ፋንኾስ አክሊግሮስ በተባለው መጽሐፉ "ሰባበሰ ተፈጥሮ አምነፋስ ወነድ አሞቱ ወአማሰኑ ከማነ፤ ከነፋስና ከአሳትስ ተፈጥረው ቢሆን አንደኛ ታማሚ መዋች በሆኑ ነበር ብሏል። መጻሕፍት መላእክት ከነፋስና ከአሳት ተፈጠሩ ማለታቸው ግን ግብራቸውን ሲያመለክቱ ነው። አሳት ረቂት ነው። መላእክትም ረቂቃን ናቸው። ነፋስ ፈጣን ነው። መላእክትም ለተልዕኮ ይፋጠናሉ። ነፋስ፣ አሳት ደጻም ያነ ፈቃድ (ፈቃድ ደጻሚዎች) ናቸው። መላእ ክትም የፈጣሪያቸውን ፈቃድ ይፈጽማሉ። የተፈጠሩት መላእክት መቶ ነገድ ናቸው።

ቢኒኛው ሰዓተ ሌሊት ኢዮርን ከአራት ከፈላት። ከመቶው ነገደ መላእክትም አርባውን ወስዶ አሥሩን ኢጋዕዝት፣ አሥሩን ኪሩቤል፣ አሥሩን ሱራፌል፣ አሥሩን ኃይላት ብሎ ሰየማ ቸው። ኢጋዕዝትን በኢዮር በላይኛው ከተማ፣ ኪሩቤልን በሁ ለተኛው የኢዮር ከተማ፣ ሱራፌልን በሦስተኛው የኢዮር ከተማ፣ ኃይላትን በአራተኛው የኢዮር ከተማ አሰፈራቸው።

ለኢጋዕዝት ሳጥናኤልን፣ ለኪሩቤል ኪሩብን፣ ለሱራፌል ሱራፌን ሰጋይላት ቅዱስ ሚካኤልን አለቃ አድርጎ ሾመላቸው።

ነገደ ኪሩቤል ከወገባቸው በላይ አራት ራስ፣ አራት ገጽ ያላቸ ውና ገጾቻውም ገጸ ሰብእ (የሰው ፊት)፣ ገጸ አንበሳ (የአንበሳ ፊት) የማመስለሉ ዋቸው። ዓይናቸው አንደ ነባር ቆዳ ሻርንተር ጉርና አንደ መስተዋት ልመጥ ነው። አገልግሎታቸው በተሳው ስት አምሳል መንበረ ሥሉስ ቅዱስን መሸከም ነው።

ነገደ ሱራፌል በዲያቆናት አምሳል ለጸሎት የሚተጉ፣ የሚያቀጉ የምስጋና መላእክት ናቸው። ገጾቸው ገጸ ንስር፣ ገጸ አንበሳ ነው። አያንዳንዱ ሱራፊ ስድስት ስድስት ክንፎች አሉት። አገዚአብሔርን ሲያመሰግኑም በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ቁመው በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን፣ በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ። ሁሉቱን ክንፋቸውን ቀኝና ግራ ይዘረጋሉ። ኢሳ.፮÷፪።



በአሥራ አንደኛው ሰዓተ ሌሊት ከቀሩት ስስድሳው ነገደ መላእክት ሠላሳውን ነገድ ከፈለ። የከፈላቸውንም፦

- አሥሩን ነገድ አርባብ
- አሥሩን ነገድ መናብርት
- አሥሩን ነገድ ሥልጣናት ብሎ ሰየማቸው። በዚሁ ሰዓት ራማ የተባለችውን ሰማይ ከሦስት ከተማ በመክፈል አርባ ብን በላይኛው፣ መናብርትን በሁለተኛው፣ ሥልጣናትን በሦስተ ኛው ከተማ አሰፈራቸው። ወዲያውም ለአርባብ ቅዱስ ገብር ኤልን፣ ለመናብርት ቅዱስ ሩፋኤልን ለሥልጣናትም ቅዱስ ሱርያ ልን አለቃ አድርጎ ሾመላቸው።

አርባብ፣ መናብርትና ሥልጣናት በተሾመበት ከተማ የሚፈጽሙት የሥራ ድርሻ አላቸው። አርባብ በሥላሴ ፊት በአ ፋሪ በአስተናጋጅ አምሳል የሚቆሙ ናቸው። "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" እንዳለ የአርባብ አለቃ የሆነው ቅዱስ ገብርኤል። ሉቃ.፩÷፲፱። መናብርት ደግሞ በጋሻ ጃግሬ አም ሳል ያገለግላሉ። አዋጅ ነጋሪዎችና መላእክትን በየጊዜው ለጸሎት ሰምስጋና የሚያተጉት ደግሞ ሥልጣናት ናቸው።

በአሥራ ሁለተኛው ሰዓተ ሌሊት የተቀሩትን ሠላሳውን ነገደ መላእክት በኢረር አሰፈራቸው። መኒንንት የተባሉትን አሥሩን ነገድ በላይኛው ከተማ፣ ሊቃናት የተባሉትን አሥሩን ነገድ በሁለተኛው የኢረር ከተማ እንዲሁም መላእክተ የተባሉትን አሥሩን ነገድ በኢረር የመጨረሻው ከተማ አኖራቸው። ወዲያውም ሰመኒንንት ሰጳኳሌልን፣ ለቢሊቃናት ሰላታኤልን፣ ሰመላእክት አናንኤልን አለቃ አድርጎ ሾመ።

እግዚአብሔር በሦስቱ ሰማያት ያሰፈራቸው መላእክት ፈጣሪያቸው ካሠፈራቸው ሀገር አይወጡም። አይናወጹም። እግዚአብሔር ለተልዕከ ሲጠራቸው ግን ወደ ላይ እስከ ጽርሐ አርያም ወደታች እስከ በርባሮስ ድረስ ከመቅጽበት ወርደው ተልዕ ኳቸውን ይፈጽማሉ።

እግዚአብሔር በባሕርይ ሥልጣኑ አራቱን ባሕርያት፣ ጨለማንና ሰማያትን ከፈጠረ በኋላ መላእክትን ፈጠረ። መላእክትን አስቀድሞ ፈጥሮ በኋላ ሌሎችን ያስገኘው ሰማያትን ሲፈጥር ሲዘረጋ እኛም አብረን ፈጠርን ተራዳነው እንዳይሉ ነው። ሳጥናኤል እንኳን ከዚህ ሁሉ በኋላ ተፈጥሮ ይህንን ሁሉ የፈጠርሁ እኔ ነኝ ብሎ ተነሥቷል። ይህን የመሰለውን ከንቱ ሕሊና ሊያርቅ ሊያስወግድ መላእክትን ወደኋላ ፈጠራቸው።





ስዕል ሁለት፡- እግዚአብሔርና ሥነ ፍጥረቱ
(እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ ለራ አከሆም እጀን መለከ ሮ ነዉር በፍይጠዉ)



## ፫.፪.፫ ክህደተ ሳጥናኤል

ሳጥናኤል አጋዕዝት ሰቱባሉት ነገደ መላእክት አለቃ ሁኖ የተሾመ መልአክ ነበር። አለቃ በመሆኑም አቋቋሙ ከሌሎች መላእክት በቅድምና ነበር። ሌሎቹ መላእክት ከእርሱ በታች ነበሩ።

ሥላሴ መላእክትን ፈጥረው በየቦታቸው ካደራጇቸው በኋላ ድምፅ ሳያሰሟቸው በረቂት ባሕርያቸው ተሰወሯቸው። መሠወራቸውም መላእክት ከእግዚአብሔር ባገኙት ዕውቀት ተመራምረው ፈጣሪያቸውን እንዲያውቁ ሰማድረግ ነውና መላእክቱ በቦታቸው ሆነው እርስ በርሳቸው እኛ ምንድን ነን? ከየትስ መጣንየ? ማንስ ፈጠረንየ ብለው ይጠያየቁ ጀመር። በቦታ ከሁሉም በላይ የሆነው ሳጥናኤል መላእክት እንዲህ ብለው ሲጠያየቁ ከማንኛውም አክል ‹እኔ ፈጠርኋችሁ› ብሎ መልስ የሰጠ እንዳለሰ ባየ ጊዜ ‹ፈጣሪ ያችሁማ እኔ ነኝ አለ። ብረት ከብረት፣ እንጨት ከእንጨት ሲላበት አሳትን እንዲያስገኝ አእምሮው እርስ በርሱ ተፋጭቶ ክፋትን ከህደትን ጸንሶ ወለደ። ‹ዓመፃ ወጽኦት እመፃግቡቲሃ፤ ዓመፃ ከመዝገቧ ወጣች› እንደተባለው። ሄዘ. ፮፩፡፪።

ይህቺ የዓመፅ ቃል ከመዝገቧ ከዲያብሎስ ልቡና መንጭታ በቃሉ በተገለጠች ጊዜ መላእክት ከሦስት ወገን ተከፈሉ ሦስቱም ወገን፡ -

ሀ. ፈጣሪያችን ነው ብለው የሰገዱለት

ሌ ሀልዎተ እግዚአብሔርን ሳይመራመሩ ቀርተው ‹ያለ እርስ ፈጠር ኪችሁ ያለ አምላክ የለም ፈጥሮን ይሆን? አይሆንም› ብለው የተጠራጠሩ

ሐ. በቦታ ከበላያችን በመሆኑ ፈጠርኋችሁ የሚለን ከሆነ መች እኛ ከበታቾችን ያሉትን ፈጠርናቸውና? ፈጣሪ ነኝ ካልህ ደግሞ ፈጣሪ በፍጡሩ ይታወቃልና ፈጥረህ አሳየን በማለት የተከራከሩት ናቸው።



ፈጥረህ አሳየን ያሉትን መላእክት ለማሳመን ሲላ ፍጥረት አፈጥራለሁ ብሎ አጁን ወደ አሳት ከተተው። ቢፈጀው ‹ዋይ› ብሎ ጮኸ። ይህን የእግዚአብሔርን ትዕግሥት እንደ አላዋቂነት በመቁጠር የውጪውን ብቻ የሚያውቅ (አፍአዊ) አምላክ ቢሆን ኖር ነው እንጂ የውስጡን ልቡና ያሰበውን የሚያውቅ ቢሆን ኖር እሳቱ የፈደህ ምን ስትሠራ ነው? ብሎ በጠየቀኝ ነበር ብሎ አሰበ። ይህንኑ ከህደቱን በማሸናነት እንዲያውም አምላክ የጋቢናን የነቢቡን እንጂ የሐልዮውን አያውቀውም በማለት ደመደመ። ሥላሴም የተሰወራቸውና የሚሠወራቸው ነገር እንደሌለ ይረዳ ዘንድ ይህን ክፋት ያሰበበትን ልቡናውን በእርምም በሐልዮ እንዲቃጠል አደረጉት። ‹ዋይ› ብሎ ጮኸ ፈወሱት። በዚህ ሁሉ ግን ሲያምን አልወደደም። ሲያውቅ ክሷልና።

‹አበሃ ሉሐሰት፣ የሐሰት አባቷ› የተባለው ሳጥናኤል በመላእክት መከክል በዘራው ክህደት፣ ባመጣው መለያየት በሦስቱ ዓለመ መላእክት ታላቅ ሽብር ሆነ። አረጋጊ መልአክ ብሥራት የሆነው ቅዱስ ገብርኤል በመላእክት ዘንድ ሽብር ሁከት በሆነ ጊዜ ‹ፈጣሪያችንን ፈጥሮ ስለማይጥሰን አስከናንሃው፣ አስኪንሳጥልን ድረስ ባለንበት እንጽና› ብሎ አረጋግቷቸዋል።

## ፫.፭.፬ የሰዉድ ሰዓታ መላእክት ፍጥረት

አሑድ በቀዳማይ ሰዓተ መላእክት (ሚት በ፤ዐዐ ሰዓት) እግዚአብሔር ‹ባጨሰማው መከክል ብርሃን ይሁን› ብሎ ቢያዝ ብርሃን በስተምሥራቅ በኩል ተፈጠረ። ይኸውም ብርሃን የተገኘው ከአራቱ ባሕርያት መከክል እንዱ ከሆነው አእሳት ነው። ያቺን አሳት ብርሃን ታስንኝ ዘንድ ባዘዘት ጊዜ (ቢያዝዛት) ብርሃንን አስገኘች።

ብርሃን በሆነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አንድ ክንፉን ወደ አር ያም ዘርግቶ (በአብና በመልድ ላይ ረበ) አንድ ክንፉን ወደ ምድር ዘርግቶ ሰመላእክት ታያቸው። በዚህም ብርሃን በሦስቱ ሰማያት በዓለመ መላእክት ያሉት መላእክት እርስ በርሳቸው ተያዩ። በብርሃኑም ዕውቀት ተገልጠላቸው ፈጣሪያቸውን አወቁት። አየሰ ዱሳትም ‹ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አምላሩ እግዚአብሔር ምስጋኑ

በሰማይና በምድር የመሳ ነው ብለው አመሰገኑት። ክዩትም ከእግዚአብሔር ግርማ የተነሣ መላእክቱ እንደ ሻሽ ተነጠፉ፤ እንደ ቅጠልም ረገፉ።

እግዚአብሔርና መላእክቱ ሲነጋገሩ ሳጥናኤል ሰምቶ ዳነ ገጠ። ሐሳቡ ከንቱ ስለሆነበትም እጅጉን አፈረ። "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮክብ ሆይ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ እንዴት አስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ? አንተም በልብህ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ። ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ። በሰሜንም ጸርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከደመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲዖል ወደ ጥልቅ ትወርዳለህ እንደተባለው ሆነ። ኢሳ.፲፬፥፲፪-፲፭።

ሥላሴ እስከ ኤሎድ ቀዳማይ ሰዓተ መዓልት ድረስ ያሉትን ፍጥረታት አራቱን ባሕርያት፣ ሰባቱን ሰማያትና መላእክትን የፈጠሩት በሐልዮ ወይም በእርምኖ ነው። ብርሃንን ግን የፈጠሩት በነቢብ (በመናገር) ይሁን በማለት ነው። ከኤሎድ ቀዳማይ ሰዓተ መዓልት በፊት ያሉትን በሐልዮ በእርምኖም የፈጠሩት የሚሰማ የሚያዳምጥ ፍጥረት ስለሌለ ነው። ይህም ነገርን የሚሰማ፣ የሚያዳምጥና የሚከታተል ሳይኖር መናገር እንደማይገባ ያስረዳል። ብርሃንን "ይሁን" ብለው በነቢብ በመናገር የፈጠሩት የሚሰሙ የሚያዳምጡ መላእክት ስለነበሩ ነው።

ሥላሴ በሐልዮም በነቢብም መፍጠራቸው በሁሉም ሥራ መሥራት እንዲቻላቸውና በሐልዮም በነቢብም የሚደረገውን እንደሚያውቁት ያጠይቃል።

እግዚአብሔር ጨለማውን አስቀድሞ ብርሃንን በሰተኋላ የፈጠረው ጨለማ የዘለዓለም ዓለም ምሳሌ ስለሆነ ነው። ይህች ዓለም በጨለማ መመሰሏም ሕሊናን የሚያደነዝዝ፣ ልቡናን የሚያናውዝ ኃጢአት ይሠራባታል። የዲያብሎስ ፈቃድ ይፈጸምባታልና ነው። የወዲያኛዋ ዓለም ግን ብርሃናዊ ሥራ (ስብሐተ እግዚአብሔር) ብቻ ስለሚቀርብባት፣ ኃጢአት ስለማይሠራባት ይልቁንም የእግዚአብሔር ብርሃን ስለማበራባት በብርሃን ትመሰላለች።



ጨለማ የአረት፣ ብርሃን የወንጌል ምሳሌ ነው። ቀድሞ ሳአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በአረት ጨለማ ነበር። ዛሬ ግን በወንጌል ጽድቅ የምንሠራበት ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብ ብርሃን ወጥቶልናል።

"በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ አገርም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው አንጂለ። ሊሊፎ፤ ሮሜ ፲፫፥፲፪፤ ፩ጴጥ.፪፥፱።

ጨለማ ያለማወቅ /የአለማዋቂነት/፣ ብርሃን የአውቀት ምሳሌ ነው። በሰላ በኩልም አስቀድሞ ብርሃንን ፈጥሮ በኋላ ጨለማን ቢፈጥር ናሮ ኋላ የተነሡ መናፍቃን ደት አምላክ ብርሃን ነን ቢፈጥር ክፉው አምላክ ደግሞ በላዩ ሳይ ጨለማን ፈጠረበት አንጻይሉ አስቀድሞ ጨለማን በኋላም ብርሃንን አሰኘ።

በሁለተኛው ሰዓተ መዓልት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጽርሐ አርያምን፣ ሰማይ ውዱድን፣ መንበረ ስብሐትን መሠረቷን ሁለንተናዋን ተብቡ አክበራት ንጽሕት ብርሀት አደረጋት። በዚሁ ሰዓት በምስጋና ቃል እንደ ነገድጓድ የሚነጉዱ፣ በክብር በንጽሕና እንደ መብረቅ የሚበርቁ እንደ አላት የሚነዱ መላእክትን አሰፈረባቸው።

በሦስተኛው ሰዓተ መዓልት አዮርን ከቀባት ቀደሳት በኋላ ቀደም ሲል በወሰጣ አስፍራቸው የነበሩትን መላእክት ቀባቸው።

❖ *ቀባቸው*፦ ማለትም ከዝንጋኤ የራቁ፣ ባለአእምሮ የሆኑ እውቀት ያላቸው ይዋሂን፣ ትዕግሥትን ገንዘብ እንዲያደርጉ ለዘለዓለም የማይጥፍ የማያቋርጥ፣ እንደ ወራጅ ውኃ የሚወርድ ምስጋና አፍ ልቆ ሰጣቸው ማለት ነው። ሕማም፣ ሞት፣ ድካም፣ ዕረፍት የሌለባቸው አደረጋቸው ማለት ነው። መላእክት ሳይቀቡ አእምሮ (ዕውቀትን) እንደሌላቸው ሕማናት ነበሩ።

- በሦስተኛው ሰዓተ መዓልት ኢጋዘነትን፣
- በአራተኛው ሰዓተ መዓልት ኪሩቤልን፣
- በአምስተኛው ሰዓተ መዓልት ሱራፌልን፣



- በስድስተኛው ሰዓተ መዓልት ኃይላትን ቀባቸው።

ራማ የቆባሰችው ዓለመ መላእክት በሰባተኛው ሰዓተ መዓልት ሁለንተናዋ ተቀባ። ከዚያም፦

- በሰባተኛው ሰዓተ መዓልት አርባብን፣
- በስምንተኛው ሰዓተ መዓልት መናብርትን፣
- በዘጠነኛው ሰዓተ መዓልት ሥልጣናትን ቀባቸው።

በዐሥረኛው ሰዓተ መዓልት ኤረርን ሁለንተናዋን ቀባት ቀደሳት።

- በዚሁ ሰዓተ መዓልት መኢንንትን፣
- በአሥራ አንደኛው ሰዓተ መዓልት ሊቃናትን፣
- በአሥራ ሁለተኛው ሰዓተ መዓልት መላእክትን ቀባቸው።

በዚሁ በአሥራ ሁለተኛው ሰዓተ መዓልት መላእክት የተባሉትን ነገድ ከቀባ በኋላ ኪየሩሳሌም ሰማያዊትንና ቅውስጧ ያሉትን ታቦት ዘደርጋ፣ አሥራ ሀጫሉ ፪ር፻፵፬ ምሰሶዎቿን ቀባ፣ አነጻ፣ ቀደሰ።

ልዑል እግዚአብሔር በየሰማያቱ ያሉትን መላእክት ሲቀባቸው፦

- የብርሃን መንፍጸፊያ አንፍኖር፣
- የብርሃን ዝናር አስታጥቆ፣
- ማኅተመ መስቀል የሆነ የብርሃን መስቀል አስይዞ፣
- የብርሃን ጫማ አጫምቶአቸው፣
- የብርሃን አክሊል ደፍቶላቸው፣
- የብርሃን ዘውድ አቀናጅቷቸው፣
- የብርሃን መነጽር (መስተዋት) አድርጎላቸው ነው። ይህም ምሳሌ ነው።

❖ *መንፍጸፊያ*፦ የእግዚአብሔር ፍጥረት፣ ፍጡራን መሆናቸውን /እኛ ደሆኑ/ አንዲያውቁ ነው። መንፍጸፊያን ከአካል በላይ አንዲኖሩ ጸፉት ከእነርሱ በላይ እግዚአብሔር መኖሩን አንዲያውቁ ነው።



❖ *ዝናር*፦ - ተገባሮች ናችሁ፣ ተገቢነታችሁን ዕወቁ ሲል ነው።

ጌታውን የሚያገለግል አገልጋይ ወገቡን ታጥቆ ተገቢ ነቱን አውቆ ሰተልዕኮ እንዲፋጠን እነርሱም የብርሃን ዝናር ታጥቀው ያገለግሉታል። "ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን። እናንተም ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ. . ." እንዲል። ሉቃ ፲፪÷፴፭-፴፰

❖ *ጫማ*፦ ሰተልዕኮ መውረድ መውጣት መላክ አለባችሁ፣ እንዳለ ባችሁ ዕወቁ ሲል ነው።

❖ *ማኅተመ መስቀል ያለበት የብርሃን ዘንግ በእጅ*፦ ሠራዊቶች ናችሁ ሠራዊቶቼ መሆናችሁን ዕወቁ ሲል ነው።

"ወገባችሁን ታጥቃችሁ ጫማችሁን በእግራችሁ በትራችሁ ንም በእጃችሁ አድርጋችሁ. . ." እንዲል። ዘጸ.፲፪÷፲፩፣ ኤፌ.፮÷፲፭።

❖ *የብርሃን አክሊል*፦ የብርሃን ዘውድ የጸጋ ክብር፣ የጸጋ መንግሥት እንማግችኋለሁ። ሲል ነው።

❖ *የብርሃን መነጽር /መስተዋት/*፦ አኔን ማየት በወደዳችሁ ቀን ያለ ምክንያት ልታቋኝ አይቻላችሁም ሲል ነው።

ሁሉንም ቀብቶ ከመጋበሩ በክብር በልዕልና በደባቤ መላእክት ተቀመጠ። ወዲያውም ከነገደ ኪሩቤል ገጸ ሰብእና ገጸ አንበሳ ያላቸውን፣ ከነገደ ሱራፌል ገጸ ንስርና ገጸ ላህም ያላቸውን ወስዶ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት በላይ ከሰማይ ውዱድ በታች በአራቱ ማዕዘን በምሥራቅ በምዕራብ፣ በሰሜን በደቡብ አቆማቸው። ያቆማቸውም ጀርባቸውን ወደ ውስጥ፣ ፊታቸውን ወደ ውጪ አድርጎ ነው። በመሆኑም ገጽ ሰገጽ አይተያዩም። ዓይናቸው እንደ ነብር ሰምድ (ቆዳ) ዥንጉርጉር ነው። ከአገር እስከ ራሳቸው እንደ መስተዋት ስድ (ልሙጥ) ነው።

ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ የሚባሉትን ከሩቋኤል ሠራዊት አለራቱ ሲታናት መርጦ በመንበረ ስብሐት ዙሪያ አቆማቸው። አክሊሉም ጻዝዮን የሚባል አሳታዊ የሆነ የዕንቁ አክሊል የደፉ፣ የብርሃን

ካባ ላንቃ የለበሱ፣ የብርሃን መሲቀል የያዙ ናቸው። አገልግሎታቸውም ያለማቋረጥ የሥላሴን መንበር ማጠን ነው። ሲያጥኑም መል ካም መዓዛ ያለው መብረቅ ነጋድጓድና ብልጭልጭታ ከማዕጠንታቸው ያወጣል። "በዙፋኑ ዙሪያም ሃያ አራት ዙፋኖች ነበሩ። በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሃያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር። ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል' አንጺል። ራእይ ፬፡፬።

ካህናተ ሰማይ በአገልግሎታቸው ወቅት በማዕጠንታቸው የሚያጥኑት ምድራዊውን ዕጣን ሳይሆን የሰማዕታትን ገድል፣ የጸድ ቃንን ጸሎት፣ የበጎ ፈዳጊ ሰምኾን መልክም

- ግብራቸውን
- ፍቅራቸውን
- ትሕትናቸውን
- ንጽሕናቸውን ነው። ራኢይ፪፡፰። ባጠኑ ጊዜም የማዕጠንታቸው ጢስ አርያምን ይሸፍናታል።

መላእክት ረቂቃን መንፈሳውያን እንደ መሆናቸው ሥጋዊ ምግብ አይመገቡም። ምግባቸው መጠጣቸው ረቂት የሆነ የፈጣሪ ያቸው ፍቅርና ምስጋና ነው። መላእክት የወንድና የሴት መለያ የላቸውም። ሁሉም እሳታውያን መንፈሳውያን ረቂቃን ናቸው። የመሳ እክት መጠናቸው አርኪያቸው አገልግሎታቸው ሰየብዕ ነው። ክንፋ ቸው አንድ አገር የሚያክል፣ ራሳቸው ተራራ የሚያክል፣ መላ ሰውነ ታቸው በዓይን የተሸለመ፣ ስድስት ክንፍ ያላቸው አሉ። መጠናቸውን ግን ከሥላሴ በቀር የሚያውቀው የለም።

**ዲ.ፎ.ሯ ግጠቃለያ**

እግዚአብሔር በዕለተ አሑድ፡-

- በአሥራ ሁለቱ ሰዓተ ሌሊት
- በአሥራ ሁለቱ ሰዓተ መዓልት ስምንት ፍጥረት ፈጠረ። እነዚህም፡-
  - አለት
  - ጨለማ
  - ውኃ
  - ሰባቱ ሰማያት



- ነፋስ
- መላእክት
- መሬት
- ብርሃን ናቸው።

ልዑል እግዚአብሔር በዕለተ አሑድ በሃያ አራቱ ሰዓታት ሥራ ሠርቶባቸዋል። ይህም በኋላ ዘመን የሚነሡ ቅዱሳን ወጻጽፎ በሃያ አራቱ ሰዓታት ውስጥ ሳያቋርጡ የሚያመሰግኑት መሆኑን ያሳያል።

እግዚአብሔር ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት ያስገኘው እምኀበ አልቦ ኀበ ዖ (ከሰመኖር ወደ መኖር) እና ግብር እምግብር ከተፈጠረው ፍጥ ረት በመፍጠር ነው።

- እግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረትን በሐልዮ በነቢብና በገቢር አስገኝ ፈጠረ።
- ጨለማውን ሌሊት፣ ብርሃኑን ደግሞ መዓልት አለው። ሁለቱን አንድ ላይ "ዕለት" ብሎ ሰየመው።

"እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት አለው ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ቀን አንጺል። ዘፍ. ፩፡፩።

ጨለማ የአሪት፣ ብርሃን የወንጌል ምሳሌ ነው። ሁለቱን አንድ አድ ርጎ ዕለት አንጻላቸው ሁለቱም (ኦሪትም ወንጌልም) ሕግ በመባል አንድ ናቸውና። ሮሜ ፲፫ ÷ ፲፪። በሌላ በኩልም ሌሊት የትስብእት (የሥጋ)፣ መዓልት የመለኮት ምሳሌ ነው። ሁለቱን አንድ አድርጎ ዕለት አንጻላቸው ትስብእትና መለኮት በተዋሕዶ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ የመሆናቸው ምሳሌ ነው።

**መልመጃ ፪.፭**

፩. ተማሪዎች፡- ሙሉ እግዚአብሔር አንድ ሰማይ ብቻ እንደፈ ጠረ አድርጎ ". . . እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" በማ ለት ጽፏል። በሥነ ፍጥረት መጻሕፍት ደግሞ ሰባት ሰማያት እንደተፈጠሩ ተገልጧል። የሁለቱን ትምህርት አስቱ ተወያይ ታችሁ አስማሙት።



፪. ሳጥናኤል ወደ ሲያል የተጣለው መቼ ነው? አስከሪያስ የት ቆየ?

፫. አሑድ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት በነቢብ የተፈጠረው ብርሃን ምን ዓይነት ብርሃን ነው?

፬. ሳጥናኤል "እኔ ፈጣሪ ነኝ" በማለት በኩደበት ወቅት ያመኑት፣ የተ ጠራጠሩትና ፈጣሪያቸውን ሳይመረምሩ የቀሩት መላእክት ምን ሆኑ? ዛሬስ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ነው ያሉት? ሊቃውንቱን ጠይቃችሁ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት።

፭. በነገደ ኪሩቤልና በነገደ ሱራፌል መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው? የሁለቱ ነገደ መላእክት አገልግሎታቸውስ ምንድን ነው?

፮. እግዚአብሔር በየትኛው ሰማይ እንዲያኖራችሁ ትሻላችሁ? ለምን?

፯. ሳጥናኤል በዓለመ መላእክት እንደተኾመ እንተም በሰው ልጆች ላይ ብትኾም ምን ሊሰማህ እንደሚችል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

## ፫.፪ የሰኞ ፍጥረት

**ዲ.፪.፩ ትርጉም**- ሁለተኛይቱ ዕለት በግእዝ ሰኑይ (ሠኑይ) እና በአግርኛ ደግሞ ሰኞ ትባላለች። ሰኑይ የሚለው ቃል ሰኞ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን መሰነይ ሁለት ማድረግን፣ ሁለት መሆንን ያመለክታል፤ ሰኑይ ሁለተኛ ዕለት ማለት ነው።

"ወእምድኅረ ሰኑይ መዋዕል ወጽአ እግዚእ ኢየሱስ እምሀየ ውሉረ ገሊላ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ቀናትም በኋላ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ እንጺል። ዮሐ. ፪÷፶ ፫።

በሌላ በኩል ደግሞ ሠኑይ ሠነየ ካለው ግሥ ሲወጣ አማረ፣ ተዋበ፣ በመልክ በጌጥ ደስ አሰኘ የሚል ትርጉም ይይዛል።

"ወርእየ እግዚአብሔር ኵሉ ዘገብረ ከመ ጥዋ ሠናይ፤ እግዚአብሔር የሠራውን ፍጥረት ሁሉ ያመረ እንደ ሆነ አየ እንጺል። ዘፍ. ፩÷፴፩።



ዕለቲቱ ለፍጥረታት ሁለተኛ ቀን ስለሆነች ዕለተ ሰኑይ ስትባል የተፈጠረባትን ፍጥረት መልክምነት ለመግለጥ ደግሞ ዕለተ ሠኑይ ተብላለች።

**ዲ.፪.፪ የሰኞ ፍጥረት**

**መልመጃ ፫.፫**

፩. የምትመለከቱት ሰማይ ጥርት ያለ ነጭ ቢሆን በሰው ልጅ ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

፪. ስለምታዩት ሰማይስ ጥቅም አስቲ ለመምህራችሁ አስረዱ።

እግዚአብሔር ሰኛ ዕለት በመጀመሪያው ሰዓተ ሌሊት ጠፈርን ፈጠረ። ጠፈር ማለትም ሰማይ፣ የምድር ባጥ ማለት ነው። "ወገብረ ጠፈረ ወለመፎ ለውሃቱ ጠፈር ሰማየ፣ እግዚአብሔር ጠፈርን ሠራ፣ ይህንም ጠፈር ሰማይ ብሎ ጠራው እንጺል። ዘፍ. ፩÷፮።

ጠፈር ከመፈጠሩ በፊት ከምድር አስከ ኡረር ድረስ ውኃ መልቶ ነበር። ሰኛ በአንደኛው ሰዓተ ሌሊት እግዚአብሔር ግዙውንና በውኃ መካከል ይለይ ዘንድ ጠፈር ይሁን ብሎ ቢያዝ በዓለም መልቶ የነበረው ውኃ ከአራት ተከፈለ። እነዚህም.

ሀ. የምናየው ሰማይ (ጠፈር) (ሥዕለ ማይ)፣
ለ. ከጠፈር በላይ የተለቀለው ሐናስ፣
ሐ. ለምድር ምንጣፍ የሆነው ውኃና
መ. በምድር ዙሪያ የተጠመጠመው ውኃ ናቸው።

እግዚአብሔር በወሰነላቸው ቦታ የተለበለቡት ሰኛ በመጀመሪ ያው ሰዓተ መዓልት (ወንግህ) እግዚአብሔር "ለይትጋብ ማይ ውስተ ምዕላጲሁ፣ ውኃ በየቦታው ይሰብሰብ ብሎ ባዘዘው ጊዜ ነው። ዘፍ. ፩÷፱።

ጠፈር ሁለት ሺህ በሮች አሏት። የአሳት ንብን፣ መድረክ፣ መቃን ተሠርቶላታል። የውኃ ለንቃም ተገዥውላታል። በአያንዳንዱ በር ጀምሮ ሰይፍ የያዙ ሁለት ሁለት መላእክት አቆሙ። አዘርአም ወደ ታች እንዲወርዱ ወደላይም እንዲወጡ ያልተፈቀደላቸው እንዲደው ርጓ እንዳይወጡ የሚጠብቁ ናቸው።

አግዚአብሔር ከጠፈር በላይ ያወጣው ውኃ (ሐናስ የተባለው) ጠፈርን እንዳይጫነው ባቢል የሚባል ነፋስ ወደ ላይ አውጥቶ ሐኖስን አሸክመው። ባቢልም የረጋ ነፋስ ነው። ጠፈርን ከታች ባቢል የተባ ሰውን የረጋ ነፋስ ከመከከል ሐኖስን ከላይ አድርጎ ሁሉን በየቦታ ቸው አጸናቸው። ቀባቸው። አንጽቶም አከበራቸው። ሐኖስ የተባለው ውኃ ከላይ ሆኖ ጠፈርን ባያቀዘቅዝው ኖሮ የፀሐይ ትኩሳት ይሰብረው ይበሳው ነበር። ድስት ውኃ ሳይጨመርበት ከእሳት ቢጣድ እሳት ሲበዛበት ሲሰበር፣ ሊበላ ሲሰነጠቅ እንደሚችለው ዓይነት ማለት ነው።

የጠፈር መልኩ የበዛ ነጭ፣ የበዛም ቀይ አይደለም። ነጭ ቢሆን ኖሮ እያንጸባረቀ የሰውን ዓይን በጎዳ ነበር። ቀይም ቢሆን ኖሮ ለዓይን በከበደና መደብዘዝን ባስከተለ ነበር። ነገር ግን ለሰው ልጅ ዓይን በሚመች መልኩ የቢጫና የአረንጓዴ ቅልቅል አስመስሎታል።

ጠፈር ቅርጹም እንደ ጠረጴዛ ዝርግ ሳይሆን ጎበጥ ያለ ነው። የጠፈር ቅጥሯ ከሐናስ፣ የሐናስም ቅጥር ከኤረር ቅጥሯ የተጋመ መና የታተመ ነው።

ሰኞ ዕለት ምድር እንደ አይብና እንደ አትት ከውኃ ጋር ተቀ ላቅላ ነበር። ልዑል አግዚአብሔር በጥበቡ አይብ ከአትት ተለይቶ እንዲረጋ ውኃውን በውስጥ እንደ አትት አደጠራ ተራራ፣ ኮረብታ ድንጋይ የምታስገኝ አደረጋት። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ አግዝፎ አወፍሮ በውኃ ላይ እንደ መርከብ ዘርግቶ ምድርን አጸናት። ከላይ ወደታችም ውኃ፣ አሳት፣ ነፋስ በስተመጨ ረሻም በርባሮስን አደረገ። ከተመውም። በርባሮስም በብረት እንኳን እንደማይውቀር ድንጋይ የጸና፣ እልፍ አእላፍ ፀሐይ ቢያበሩበት ጨለ ማውን መግፈፍ የማይቻላቸው የኀጥአን ማስፈሪያ ሥፍራ ነው።

### ይ.ደ.ይ የጠፈር ጥቅም

ጠፈር የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል።

ሀ. ለዕሐይ፣ ለክዋክብትና ለጨረቃ መመላለሻ፣ ማጎሪደር ይሆን ዘንድ፣

ደ. ከዕሐይ፣ ከክዋክብትና ከጨረቃ የሚወጣውን ብርሃን ንጠብ ባለ ቅርሹ ወደ ላይ ሳይነካ ወሰና ገትቶ እንዲይዝ፣



ሸ. ዋዕየ ፀሐይን /ሙቀት መፋጀት/ እንዲያቀዘቅዝ፣

፱. ሰው ጠፈርን /ሰማይን/ እያየ ሰማያዊ ርስቱን ተስፋ እንዲያደርግ ነው።

## ይ.ደ የማክሰኞ ፍጥረታት

### ይ.ደ.ሀ ታርኩም

ሦስተኛይቱ ዕለት ዕለተ ሠሉስ ትባላለች። ዕለተ ሠሉስ ማለትም ሦስተኛ ቀን ማለት ነው። ሦስተኛ መባሏም አግዚአብ ሔር ፍጥረት መፍጠር ከጀመረባት ከዕለተ አሑድ ጀምሮ ስለሚ ቆጠር ነው። ይህች ዕለት በአማርኛ ማግሰኞ ትባላለች። ይህም የሰኞ ማግሰት እንደማለት ያለ ነው።

### ይ.ደ.ይ ሥነ-ፍጥረታት

መልመጃ ይ.፭

፩. ተመሪዎች በአካባቢያችሁ ወዳለው ደን ወይም ሜዳ ከመምህራችሁ ጋር ወጥታችሁ የምታገኙዋቸውን ዕፀዋት አዝርዕትና አትክ ልት ተመልከቱ።

ሀ. የምታዩአቸውን ዕፀዋት፣ አትክልትና አዝርዕት በተሰያዩ ክፍ ሎች አስቲ ከፈሏቸው?

ሐ. ዕፀዋቱ አትክልቱና አዝርዕቱ ከአቲ ተነጋገሩ።

ሲሆን እንደሚችል አስቲ ንገሩ። ሚምታችሁንም ከመምህራ ችሁ ጋር ተወያዩ።

ምድር ሰኞ መፃልት ከውኃ እንደተለየች ከአራቱ አቅጣጫ በነፈሰባት ነፋስ ረግታ ጸናች። አጅግም ሳትረጥብ፣ አጅግም ሳትደ ርቅ አኗኗሯ አርዓ ለሰለስት። ከዚህ ውጪ አንድም ፍጥረት አል ነበረባትም።

ማግሰኞ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ልዑል አግዚአብሔር ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ተብቅል ብሎ ቢያዝ መራት ነባሔኒ፣ አዝርዕትን፣ ዕፀዋትን አስገኙት። በዚ.ፍ.ረ.ፀ.



ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልት ከአራቱ ባሕርያት ከመ ሬት፣ ከውኃ፣ ከነፋስና ከእሳት ተፈጠሩ። ይህም በግብራቸው ይታወቃል።

- ከእሳት በመፈጠራቸው አርስ በርሳቸው ሲሰነቋቋቸው /Friction/ እሳት ይወጣቸዋል፣
- ከውኃ በመፈጠራቸው ሲቆርጡዋቸው እንደ ደም፥ እንደ ወተት እንደ ውኃ ያለ ነገር ይወጣቸዋል።
- ከነፋስ በመፈጠራቸው በነፋስ ያድጋሉ።
- ከአራር በመፈጠራቸው ቆርጠው ሲጥሏቸው ፈርሰው በስብሰው አፈር ይሆናሉ።

ከዚህ ፈተጨማሪም ብዝናብ ይበቅላሉ፣ በነፋስ ያድጋሉ፣ በፀሐይ ይበስላሉ፣ ከመሬት ምግባቸውን ያገኛሉ።

### ይ.ደ.ይ የማግሰኞ ፍጥረታት ምሳሌነት

ከዕፀዋት ከአዝርዕትና ከአትክልት በሥራቸው፣ በሳና ቸው፣ በሚፈቸው ፍሬ የሚያደሩ አሉ።

- በሥራቸው የሚደፈሩ፦
  - በሚስታቸው /በባላቸው፣ በልጆቻቸው የሚጠቀሙ ሰዎች፣
  - በጌታ ትምህርት አምነው ክርስቶስን በነፍሮ ያሉ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።
- በሳናቸው የሚያደሩ፦
  - በሠራተኞቻቸው፣ በረዳቶቻቸው የሚጠቀሙ ሰዎች፣
  - በሐዋርያት ስብከት ያመኑ ሰዎች፣
  - ከጌታ ጎን በወጣ ውኃ /ማየ ገቢ/ ተጠምቀው በመስቀሉ የጸኑ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።
- በሜፋቸው የሚያደሩ፦
  - ጥረው ግረው ራሳቸውን የሚረዱ ሰዎች፣
  - ባሉሎች ሰሞሆራን ተማህርት ያመኑ ሰዎች፣
  - የጌታችንን ሞቱን፣ ትንሣኤውን አምነው በመስቀሉ የጸኑ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።



ዕፀዋት አዝርዕትና አትክልት ፍሬያቸውን በሥራቸው፣ በሳና ቸው የሚሠውሩ፣ በሜፋቸው አፍርተው አዕዋፍ የሚበሱባቸው አሎ። ፍሬአቸውን በሥራቸው፣ በሳናቸው የሚሸፍኑ፣ የሚከድኑ በዚህ ዓለም ምግባር፣ ትሩፋት ሠርተው እኛስ አልሠራንም፣ አላደረግንም በማለት ከውዳሴ ከንቱ ድነው ዋጋቸውን በመንግሥተ ሰማያት የሚያ ገኙ ምእመናን አምሳል ናቸው። እነዚህም ገበመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና፣ የተባለላቸው ናቸው። ማቴ. ፭፥፫።

ፍሬያቸውን በሜፋቸው አፍርተው አዕዋፍ በልተዋቸው፣ ጠላት ሰቅሚቸው የሚቀሩት በዚህ ዓለም ሲኖሩ ይደልን፣ ይሰሙ ልን፣ በማለት ምግባር ትሩፋት ሠርተው ዋጋቸውን የሚያጡ ሰዎች ምሳሌ ናቸው። ማቴ. ፭፥፭-፲፱።

ከመሬት ወይንና መርዝ፣ እሬትና ሙዝ ተገኙተዋል። ከአን ዲት ምድር በዕለተ ሠሉስ ቢገኙም በጣዕም ይለያያሉ። እነዚህ ከአን ዲት ምድር በቅለው በጣዕምና በምረት የተለያዩ እንደሆኑ ሁሉ ሰም ችም ከአንድ አዳም ተወልደው በሃይማኖትና በክህደት፣ በበጎነትና በክፋት ቀቀቧይተው ይኖራሉ። እንደ ወይን እንደ ሙዝ መልክም ጣዕም ያላቸውና መርዝነት የሌላቸው አትክልት፣ ዕፀዋትና አዝርዕት የጻድቃን፣ መርዝነት ያላቸውና መራራ የሆኑት እንደ እሬት የመሰሉ ሶት ዳግሞ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው።

ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልት እስከ ዓለም ፍጻሜ ደረስ ጣዕ ማቸውን ፍሬያቸውን ሳይቀይሩ ይኖራሉ። ጻድቃንና ኃጥአንም ዘራቸ ውን አይለዩም። የተወለዱበትን ቤተሰብ ግብር፣ አምነት ይዘው ስለ ሚያድጉ ይመስሏቸዋል። ማቴ.፯ ÷ ፲፮፣ ሉቃ. ፮ ÷፵፫-፵ ፭።

ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልት፦

- በክረምት ደርቀው በበጋ የሚለመልሙ አሉ። ለምሳሌ በለስ፣ ወይንና እንዶድ የመሰሉት በክረምት ቅጠላቸውን አራግፈው፣ በበጋ ይለመልማሉ። አነዚህም በዚህ ዓለም ተረክበው ታርክው መከራውን በደስታ፣ በጸጋ ተቀብለው በወዲያኛው ዓለም የሚጠ ቀሙ ሰዎች ምሳሌ ነው። ይህ ዓለም በክረምት መመሰሉም ከረምት ላዩ ታቹ ውኃ ነው። ድጡ አያበስድም ነርው ይከብዳል።

የዘሠችም ዓለም ኑሮ በመከራና በችግር የተሞላ ነውና፡፡ የወዲያ ኛው ዓለምም በበጋ መመሰሉ በጋ አዝመራው የሚደርስበት ከጎተራ የሚከተትበት፣ ገበሬው ድክመሙን ዋጋ የሚያፍስበት ነው፡፡ የወዲያኛው ዓለምም በዚህ ዓለም በሃይማኖት እንተው፣ ምግባር ትሩፋት የሠሩት ሰዎች ዋጋቸውን የሚቀበሉበት ወደ መንግሥተ አግዚአብሔር የሚሸጋገሩበት ስለሆነ ነው፡፡

❖ ክረምት ለምልመው በበጋ የሚደርቁ አሉ፡፡ ለምሳሌ አበቦች፡፡ እን ዚህ ደግሞ በዚህ ዓለም በልተው ጠጥተው፣ ፍርድ አጉድለው፣ ደሃ በድለው ሃይማኖታቸውን ምግባራቸውን በማጉደላቸው በወዲ ያኛው ዓለም የሚጎዱ ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡ ሶቃ.፲፮÷፲፱-፴፩፡፡

❖ ክረምትና በጋ የማይለመልሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ የበረሃ ቁልቋል፡፡ ክረምትና በጋ የማይለመልሙ የዕለተ ሠሉስ ፍጥረታት በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም የማይጠቀሙ ሰዎች ምሳሌ ናቸው፡፡ በዚህ ዓለም የሰው ገንዘብ ሰርቀው፣ ሰው ገድለው መላ ዘመና ቸውን በስደት፣ በፍርሃት በወንጌ ቤት የሚኖሩ ንሴሉ ሳይሸከም ዘመናቸውን በኃጢአት የሚጨርሱና በወዲያኛው ዓለም ከገሃነም አሳት ተጥለው የዲያብሎስን የግብር ልጆች ሆነው የሚሰቃዩ አሉ፡፡

❖ ክረምትና በጋ የሚለመልሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ዝግባ፣ ወይራ የመ ሳሰሉት፡፡ ክረምትና በጋ የሚለመልሙ ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክ ልት በዚህ ዓለም መልካም ሥራ ሠርተው፣ በጉልቻው ሁሉ ተደ ስተው በወዲያኛው ዓለምም የሚጠቀሙ የጻድቃን ምሳሌ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አብርሃም፣ ዳዊት የመሳሰሉት፡፡

ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልት፡-

❖ አበባ የሌላቸው ፍሬ ያላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሾላ
ሃይማኖት ሳይኖራቸው ምግባር ያላቸው

❖ አበባ ያላቸው፣ ፍሬ የሌላቸው አሉ፡፡ ምሳሌ፡- የደጋ ቁልቋል
ሃይማኖት ያላቸው ምግባር የሌላቸው

❖ አበቦ፣ ፍሬ የሌላቸው፣ ለምሳሌ፡- ቅንጭብ
ሃይማኖትም ምግባርም የሌላቸው

❖ አበባም ፍሬም ያላቸው ለምሳሌ ወይን፣ ሰሚ. . .



ሃይማኖትም ምግባርም አስተባብረው የያዙ የጻድቃን ምሳሌ ናቸው፡፡

ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልት፡-

❖ በግንቦት በሰኔ ተዘርተው የክረምቱን ዝናብ ተቋቁመው የሚበቅ ሱና ሰፍሬ የሚደርሱ አሉ፡፡ እንደዚህ ሁሉ ብዙ መከራና ስቃይ ተቋ ቁመው በሃይማኖት በምግባር ጸንተው ለክብር የሚበቁ የሚጸኑ ቅዱሳን አሉ፡፡ ምሳሌ፡- ኢዮብ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣

❖ በክረምት መውጫ ተዘርተው በጥቂት ዝናብ በቅለው ለፍሬ የሚ በቁ ዕፀዋት አዝርዕትና አትክልት አሉ፡፡ በጥቂት ምግባር፣ ትሩ ፋት፣ አንድ ቀን መከራ በመቀበል የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወርሱ ምእመናን አሉ፡፡ ለምሳሌ በላኤ ሰብኣ፣ ጥጦስ፡፡

ዕፀዋት፣ አዝርዕት፣ አትክልት፡-

ታላቅ፣ መካከለኛ ጥቃቅን ፍሬ ያፈራሉ፡፡ እነዚህም ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው በኃልግሳነት፣ በውጣትነትና በሕፃንነቱ ዘመን ለሠራ ቸው ትሩፋት ምሳሌ ናቸው፡፡

የዕለተ ሠሉስን ፍጥረት ያስገኘች ምድር በሦስት ነገር ጸንታ ትኖራለች፡፡ እነርሱም ድንጋይ፣ የዕፀዋት ሥር፣ ውኃ ናቸው፡፡ በነዚ ህም ምድር ሰውን ትመስላለች፡፡ ሰው ጸንቶ የሚኖረው (የሚንቀሳቀ ሰው) እንደ ድንጋይ በአጥንት፣ እንደ ሥር በጅማት፣ እንደ ውኃ በደም አማክይነት ነው፡፡


ምድር በድንጋይ፣ በሥርና በውኃ በመጽናቷም ለእመቤታችን ምሳሌዋ ናት፡፡ እመቤታችን ለአዳምና ሰልጆቹ ሁሉ ምግበ ሥጋ ምግበ ነፍስ የሆነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደ ችው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ጸንታ ነው፡፡ ምድሪቱ በሦስቱ ጸንታ እንደምትኖረው ሁሉ እመቤታችንም ከስሰሙተ ድንግልና ከዘርዐ ብእሲ፣ ርታ በድንግልና በንጽሕና ጸንታ ትኖራለች፡፡

ዕፀዋት፣ አዝርዕትና አትክልትን ያስገኘች ምድር መርገም ያል ወደቀባት፣ ገበረ ያልጋረባት፣ ማረሻ ያልዘረባት፣ ዘር ያልወደቀባት ናት፡፡ አግዚአብሔር ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ዑቃን . . . ታብቅል ብሎ ቢያዝዛት በቃሉ ሥልጣን ሁሉን በየወገኑ አስገኝች፡፡



**መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልማደ አንስት ሳያገኛት፣ አዳማዊ ርግማን ሳይተላለፍባት ዘርዐ ብእሲ ሳይወድቅባት የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን የብሥራት ቃል ለምታ በእምነት ተቀብላ ዕፀ ሕይወት፣ ፍሬ ሕይወት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አስገኝተልን፡፡**

ምድር ሦስት ስሞች አሏት፡፡ ከውኃ ሳትሰይ ጸብር ትባላለች፡፡ ጭቃ ማለት ነው፡፡ ከውኃ ከተለየች በኋላ ምድር ተብላለች፡፡ ማኅደር ማለት ነው፡፡ ደርቃ ከተፍታታች በኋላ መሬት ተብላለች፡፡ አፈር ትዚያ ማለት ነው፡፡





ሰዓል ሦስት፡- ዕፀዎችን፣ አዝርዕትንና አትክልትን የሚያብይ

## ይ.፬ የረቡዕ ፍጥረታት

### ይ.፬.፩ ትርጉም፦

ረቡዕ የሚለው ቃል ራብዕ ካለው የግእዝ ቃል የተ ገኘ ነው። ራብዕ ማለትም አራተኛ ማለት ነው። ረቡዕ ሲልም አራተኛዋን ዕለት ሲያመለክት ነው። አራተኛነቷም ለዕለተ እሑድ ነው።

### ይ.፬.፪ የረቡዕ ፍጥረታት

መልመጃ ይ.፭

፩. በአካባቢያችሁ ያሉ ብርሃን ሰፍል የሆኑ አካላትን ዘርዝሩ።

፪. በቀን፣ በሌሊት ተፈጥሮአዊ ብርሃን የሚሰጡ ሰማያዊ አካላት የሆኑትን ታውቃላላችሁ? ስሰተፈጥሮአቸው ምን የምታውቁት ነገር አለ? እስቲ ለመምህራችሁ ንገሩት።

፫. በተፈጥሮአዊ ብርሃን ሰፍል አካላትና በሰው ልጆች መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

ከእሑድ እስከ ረቡዕ ድረስ ከጠፈር በታች በምድር ጨለማ መልቶ ነበር። ልዑል እግዚአብሔር በዕለተ ረቡዕ የቀዳማይ በዓተ ሌሊት አሳትን ከኮረብ፣ ነፋስን ከአዜብ አምጥቶ የፀሐይን ሰሌዳ ፈጠረ። ውኃን ከናሄብ፣ ነፋስን ከአዜብ አምጥቶ የጨረቃንና የከዋክብትን ሰሌዳ ፈጠረ። "በሰማይ ጠፈር ብርሃን ይሁን ብሎ በቃሉ በማዘዝ ሦስቱን ፍጥረታት ፀሐይን፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠራቸው። ዘፍ. ፩÷፲፬።

፬ሐይ ከእሳትና ከነፋስ በመፈጠሯ ትምቃለች፣ ትሄዳለች። ፀሐይ በመዓልት (በቀን) ብርሃኗን ትሰጥ ዘንድ የተፈጠረች በመ ሆኗ በተፈጠረችበት ዕለት በምዕራብ ገብታ በሰሜን ዞራ በምሥ ራቅ ወጥታ መዓልቱን ገዛች። ስታበራ ዋለች። በዚህ ዓይነት ዑደት እስከ ኀልፈተ ዓለም ጸንታ ትኖራለች።

ጨረቃና ከዋክብት የተፈጠሩት ከነፋስና ከውኃ ነው። ከነፋ አንደ መፈጠራቸው ይዟዳሉ፤ ከውኃ እንደ መፈጠራቸው ደግሞ ይቀዘቅዛሉ። በዕለተ እሑድ ካለመናር ከስገኘው (ከፈጠረው) ብርሃን



የሰንዴ ፍሬ ያህል ወስዶ ያንን ከሰባት ከፈለ። ሁሉን እጅ ብርሃን ሰጨረቃ ቀባት። አንዱን እጅ ከዋክብትን ቀባ። ከዋክብትን ሲቀባም ሁሉንም እስተካከሉ በአንድ ዓይነት መጠን አይደለም። ነገር ግን እርሱ እንደ ወደደ መጠን አላልቆ ነው እንጂ። አንዱን እጅ ለውኖችና ለደመናት ሰጠ። ሦስቱን እጅ ለፀሐይ አደረገ። ጨረቃንና ከዋክብ ትን በሌሊት እንዲያበሩ አሠለጠናቸው።

፬ሐይ በቀንና በሌሊት ብታበራ ከመቀትዋ የተነሣ ፍጥረት ሁሉ ይቃጠል ነበር። ይህ እንዳይሆን በመዓልት ብቻ እንድት ሠለጥን አደረጋት። ጌታ ፀሐይን በቀን ያሠለጠነው ሰው፣ እንስ ሳት፣ አዕዋፍ በብርሃኗ ተመሰልሰለው ምግባቸውን እንዲፈልጉበት፣ በሙቀቷ ተግባራቸውን እንዲፈጽሙበት ነው።

ጨረቃም በመዓልትና በሌሊት ብታበራ ከቅዝቃዜዋ የተነሣ ለው ሁሉ በብርድ በተከማተረ፣ ባረረ ነበር። ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት በሚሰጡት ብርሃን አራዊት ተሠማርተው ምግባቸውን ይፈልጉበታል።

"ጨረቃን ለጊዜዎች አደረገ፣ ፀሐይም መግቢያውን ያውቃል። ጨለማ ታደርጋለህ ሴሊትም ይሆናል። በእርስዋም የዱር አራዊት ሁሉ ይወጡባታል። የአንበሳ ግልገሎች ለመንጠቅ ይጮሃሉ። ከእግዚአብሔርም ምግባቸውን ይሻሉ። ፀሐይ ስትወጣ ይሰበሰባሉ። በየዋሻቸውም ይተኛሉ። ሰው ወደ ተግባሩ እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው ይወጣል" እንዲል። መዝ. ያር÷፲፱-፳፬።

፬ሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት በመፈራረቃቸው በመውጣትና ወር ዓመት. . . እየተባሰ ዓለመና ጊዜው እስኪያልፍ ድረስ የዓለም ጊዜ ይቆጠርባቸዋል።

የጨረቃ ብርሃን መመላትና መጥደል ያገኘዋል። ለአሥራ አሬት ቀናት በመሉ ብርሃን ትቀያለች። ከአሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ አንድ አንድ ነገሩስ ብርሃን ትቀንሳለች። በስተመጨረሻ ሳአንድ ቀን ትጠፋለች። ጠፍታ ባደረች ቀን ራሷን ከፀሐይ አጋር ሥር ትቀብራለች። መጋቢ ብርሃን መልእክ እግዚአብሔር ከፀሐይ



ብርሃንን አያመጣ ይሥልባታል። በዚህ ብርሃን ማብራት ትጀምራለች። በዚህም ሥርዓት ጸንታ ትኖራለች።

### ይ.፬.፫ መጋብያነ ከዋክብት

ከክዋክብት መካከል ዕለትን፣ ወርን፣ ወቅትን የሚመ ግቡ፣ የሚመሩ ከዋክብት ተሹመዋል። እነዚህም፦

- መገብተ ዕለት፦
  - ሰባት ናቸው።
  - ሸምሸ፣ ቀመር፣ መሪሀ፣ መሸተሪሀ፣ ዙሐል፣ አጣርድ፣ ናርድ ይባላሉ። ሰባቱ መገብተ ዕለታት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉትን ዕለታት ይመግባሉ።
- መገብተ አውራህ
  - አሥራ ሁለት ናቸው።
  - አሥራ ሁለቱን የዓመቱን ወራት ተከፍለው የሚመግቡ፣ የሚመሩ ናቸው። ስማቸውም፦ አልሐመል፣ አልሰውር፣ አልጀመዛ፣ አልሸርጣን፣ አልአሳድ፣ አልሰንቡላህ፣ አልሚዛን፣ አልአቅረብ፣ አልቀውስ፣ አልዛዲፍ፣ አልዶሙ፣ አልሀት ይባላል።
- መገብተ አዝማን
  - አራት ናቸው።
  - አራቱን ወቅቶች፦ ፀደይ፣ ክረምት፣ መፀውና በጋ (ሐጋይ) የተባሉትን ተከፋፍለው የሚመሩ የሚመግቡ ሊቃነ ከዋክብት ናቸው። እነርሱም ናርኬል፣ ብርክኤል፣ ምልኤል፣ ሕል መልሚኤክ፣ ናቸው።

- ዘመነ ፀደይን ከመጋቢት ኛ፮ - ሰኔ ኛ፩ ከጸንሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው፣ የሚመግበው ምልኤል ነው።
- ዘመነ ክረምትን ከሰኔ ኛ፮ - መስከረም ኛ፩ ከጸንሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው፣ የሚመግበው ሕልመልሚኤክ ነው።
- ዘመነ መፀውን ከመስከረም ኛ፮ - ታኅሣስ ኛ፩ ከጸንሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው፣ የሚመግበው ብርክኤል ነው።



- ዘመነ ሐጋይን ከታኅሳስ ኛ፮ - መጋቢት ኛ፩ ከጸንሜ አንድ ቀን በመውሰድ የሚመራው የሚመግበው ናርኬል ነው።

### ይ.፬.፬ የረቡዕ ፍጥረታት ምሳሌነት

፬ሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለዓለም ብርሃናቸውን ከመስጠታቸውና ዘመናትን ከማፈራረቃቸውም በተጨማሪ ምሳሌነትም አላቸው። ይኸውም፦

**፬ሐይ፦**

- የጸድቃን ምሳሌ ናት። ፀሐይ በብርሃኗ ጸንታ እንድትኖር ጸድቃንም በቀናች ሃይማኖት፣ በበጎ ምግባር ጸንተው ይኖራሉ።
- ለኅጥአንም ምሳሌ ትሆናለች። በብርሃኗ ጸንታ እንድትኖር ኀጥአንም በኃጢአታቸው በከፉ ሥራቸው ጸንተው ይኖራሉ።

**ጨረቃ፦**

- የኀጥአን ምሳሌ ናት። በመሉ ብርሃን ተፈጥራ ብርሃኗ ጥቂት በጥቂት እየቀነሰ ፍጹም ትጠፋለች። ኃጥአንም ምንም እንኳን ኀጹሐን ሆነው ቢፈጠሩም በዓይን ኣምሮት፣ በልቡና ምኞት ተይዘው ዕለት ዕለት ሕገ እግዚአብሔርን ሲያፈርሱ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ጨምረው ሲሠሩ ክፍጹም ሞተ ነፍስ ይደርሳሉ።
- የተነሣሀያን /ንስሐ የሚገቡ ሰዎች/ ምሳሌም ትሆናለች። ጨረቃ መሉ የነበረችው ስትንደል፣ የጎደለችው ስትሞላ ትናራለች። ተነሣሀያንም ኃጢአት ሠርተው ከክብር ሲያንሱ፣ ንስሐ ገብተው ከፈጣሪያቸው በመታረቅ ያጡትን ጸጋና በረከት ሲያገኙ በእንደዚህ ዓይነት ንፃ ዘመናቸውን ይጨር ሳሉ። ጸድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃልና፣ ይነሣማል እንዲል። ምሳሌ ፳፬÷፲፮።

፬ሐይ ጨረቃ የመምህራን ምሳሌ ናቸው። እነዚህ ሲፈጠሩ ሰሌዳቸው የተፈጠረው ከእሳትና ከውኃ ነው። እሳት የማቃጠል፣ ውኃ የመቀዝቀዝ ጠባይ አላቸው። መምህራንም ተማሪዎቻቸው እንማርም ሲሉ፣ በተማሩት ሳይጠቀሙ ሲቀሩ ከህደት ሲበዛ፣ ኃጢአት ሲሰፋ እየተናደዱ፣ ብመታን ሳችሁ ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ› ባሰው ቃል ደግሞ እየታገሱ በመሳ ዘመናቸው ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ያስተምራሉ። ሉቃ. ፭፩÷፲፮።

፬ሐይ ጨረቃ ከዋክብት በብርሃን መጠን ይበላሰ ጣሉ። ቅዱሳንም በክብር ይበላለጣሉ። ማቴ.፲፫÷፰፤ ፩ቆሮ. ፲፭÷፵-፵፩።

በሰላ በኩልም ፬ሐይ የጻድቃን፣ ፬ሐይ የሠለጠነችበት መዓልት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። በቀን ሙሉ ብርሃን፣ ሙሉ ደስታ ይገኛልና። ጻድቃንም በአባታቸው መንግሥት በመንግሥተ ሰማያት ፬ሐይ በቀን እንደምታበራ በክብር ያበራሉ።

ጨረቃ በሴሊት ሥልጣን አላት። ጨረቃ የኃጥአን፣ ሴሊት፣ የጎሃነመ አሳት ምሳሌ ናት። በሴሊት ብዙ ጨለማ አለ። በሴሊት መከራ ይጸናልና። ኀጥአንም ሴሊት ምሳሌዎ በሆነችው በጎሃነመ አሳት ድቅድቅ ጨለማ ይውጣቸዋል። በማይጠፋ አሳት በማያንቀላፋ ትል መከራው ይፈራረቅባቸዋል።

መልመጃ ፫፯

፩. የረቡዕ ፍጥረታት ጥቅምና ምሳሌነት ምንድን ነው?
፪. የረቡዕ ፍጥረታት መገኛዎች ምንና ምን ናቸው?
፫. የአንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ በብርሃን መጠን መበለጥ ምንን ያሳያል?

## ፫.፭ የሐሙስ ፍጥረታት

### ፫.፭.፩ ትርጓሜ፡-

ሐሙስ የሚለው የዕለት ስም ሐመስ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው። አምስተኛ ማለት ነው። አምስተኛውም እግዚአብሔር ፍጥረታትን መፍጠር ስጀመረበት ሰዕሰተ አሑድ ነው።



### ፫.፭.፪ የሐሙስ ፍጥረታት

እግዚአብሔር ሐመስ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ‘ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኙ› ብሎ በማዘዝ ሦስት ዓይነት ፍጥረታትን ፈጠረ። ዘፍ.፩÷፳። በዕለተ ሐመስ የተፈጠሩት ሦስቱ ፍጥረታት ዘመደ እንስሳ የሚባሉት ዓሣዎች፣ ዘመደ አራዊት የሚባሉት ዓዘ፣ ጉማሬ፣ እንቁራሪት፣ ዘመደ አዕዋፍ የሚባሉት ደግሞ ጻዝኙዎች ናቸው።

በዕለተ ሐመስ የተፈጠሩት ፍጥረታት ተፈጥሮአቸው ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ /መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና አሳት/ ነው። አካላቸው ሥጋና ደም፣ አጽምና ጅማት ሲሆን በደመ ነፍስ ይንቀሳቀሳሉ። የደመ ነፍስ አውቱት አላቸው። ደመ ነፍስ ማለትም በደም ነፍስነት፣ ኃይልነት የሚንቀሳቀሱ፣ የደም ነፍስ ያላቸው፣ ደማቸው ሲቆም አንቅስቃሴያቸውም የሚቆም ማለት ነው።

የሐመስ ፍጥረታት በአካሂዳቸው፣ በአኗኗራቸው አንጻር በሦስት ይከፈላሉ። በአካሂዳቸው በልብ የሚሳቡ፣ በአግር የሚሽከረከሩ /የሚሄዱ/፣ በከንፍ የሚበሩ ይባላሉ። በአኗኗራቸውም አንጻር በባሕር ውስጥ ተፈጥረው በረው ወደ የብስ፣ ወደ ደረቁ መሬት የወጡ፣ በዚያው በተፈጠሩበት በባሕር ውስጥ የቀሩ፣ ወጣ ገባ አያሉ ማለት ከባሕር ወደ የብስ፣ ከየብስ ወደ ባሕር ወጣ ገባ አያሉ የሚኖሩ ይባላሉ። ከእነዚህም ፍጥረታት የሚበሉና የማይበሉ፣ ሰለው የሚገዙና የማይገዙም አሉ።

### ፫.፭.፫ የሐሙስ ፍጥረታት ምሳሌነት

በባሕር ውስጥ የሚኖሩት፡-

- በእግዚአብሔር አምነው በስመ ተጠምቀው በዚያው ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች፣



- በሕገ እግዚአብሔር ጸንተው በትጻር ተወስነው በሀብተ በንብረታቸው መልክም ሥራ እየሠሩ ዓመራት በኵራት አውጥተው፣ በዓሳትን አክብረው የሚኖሩ የሕጋውያን፣
- ሀገራችንን፣ ግብራችንን አንተውም ብለው ሲሠርቁ፣ ሲቀሙ፣ ሲምሱና ሲገዙዙ የሚኖሩ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው።

ወጣ ገባ አያሉ የሚኖሩት፡-

- አንድ ጊዜ ወደ ዓለም አንድ ጊዜ ወደ ገጻም ሲመላለሱ የሚኖሩ ‘መነኩሳት›፣
- አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት፣ አንድ ጊዜ ወደ ክህደት የሚወላውሉ ሰዎች፣
- በቅድስና ከአሥሩ ማዕረጋት ከደረሱ በኋላ ተመልሰው ‘አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር . . . በደለችንን ይቅር በለን› አያሉ የሚጸልዩ የሚኖሩና የተነሣሀያን /የተጸጸቾች/ ምሳሌ ናቸው።

አሥሩ ማዕረጋት የሚባሉትም፡-

### የገጽሐ ሥጋ ማዕረግ

፩. ጽማዌ፡- እርጋታን ገንዘብ ማድረግ የሚችሉበትና የቅዱሳን መለኮክትን ግብራቸውን (መውጣት መውረዳቸውን) ሰማየት የሚበቁበት ማዕረግ ነው።
፪. ልባዌ፡- ምሥጢራትን የማወቅ ማዕረግ ነው።
፫. ጣዕመ ዝማሬ፡- እንደ መላእክት የማመሰገን ማዕረግ ነው።

### የገጽሐ ነፍስ ማዕረግ

፩. አንብረ፡- መከራ መስቀልን አሸንፎ የማልቀስ ማዕረግ ነው።
፪. ኦሪኔ፡- ሥጋን ለነፍስ የማስገዛት ማዕረግ ነው።
፫. ፍቅር፡- ኃጥኣ ጻድቅ ሳይሉ ሁሉን የመውድድ ማዕረግ ነው።
፬. ሐሰት፡- እንደ እግረ ፬ሐይ ካለቡት ሁሉ የመድረስ ማዕረግ ነው።



### የገጽሐ ልቡና ማዕረግ

፩. ንጻሬ መላእክት፡- ቅዱሳን መላእክትን ሬት ሰፊት የማየት ማዕረግ ነው።
፪. ተሠጥዎ፡- በብርሃን ተመስጠ ራእያትን የማየት ማዕረግ ነው።
፫. ኅሪን አሳት፡- የመለወርና ለነጽርተ ሥሉስ ቅዱስ የመድረስ ማዕረግ ናቸው።

### በባሕር ተፈጥረው በረው ወደ የብስ የሄዱት፡-

ከዘመድ አዝማድ ተሰይተው ርቀው ከበረሃ ወድቀው ድምፀ አራዊቱን ጸብአ አጋንንቱን ግርማ ሌሊቱን ታግሰው የሚኖሩ የመናንያን ምሳሌ ናቸው።

### በልብ የሚሳቡ፡-

- የመንግሥት ምሳሌ፡- እነዚያ በልብ (በደረት) ተበበው ሥራቸውን፣ ፈቃዳቸውን እንዲፈጽሙ መንግሥትም በልቡ ያሰበውን ይሠራል ይፈጽማል።
- በሰላ በኩልም የሕጋውያን /በትጻር የተወሰኑ/ ሰዎች ምሳሌ ናቸው።

### በእግር የሚሽከረከሩ፡-

‘ያላችሁን ትታችሁ ተከተሉኝ› ባለው ቃል መሠረት ሁሉን ትተው ከሌት ከወንድ ርቀው ድንግልናቸውን ጠብቀው ከት ሩፋት ወደ ትሩፋት እየተሸጋገሩ የሚኖሩ መናንያን ምሳሌ።

### በክንፉ የሚበሩት፡-

ሥጋችሁን አንጂ ነፍሳችሁን ለመግደል የማይችሉትን አት ፍሩ ባለው አምላካዊ ቃል ተመርተው ሳይፈሩ ዓላውያን ነገ ሥታት ካሉበት ንጡተው ሃይማኖታቸውን በመመስከር ሰማዕ ትነታቸውን የሚፈጽሙ ሰማዕታት ምሳሌ ናቸው።

ሰው የሚበላቸውና ለሰው የሚገዙት፡-

ለእግዚአብሔርና ለሰው በፍትር በትሕትና የሚገዙ፣ የእግዚአብ ሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ የጻድቃን ምሳሌ ናቸው።

ሰው የማይበላቸውና ሰለው የማይዝተ፦
ለእግዚአብሔርና ለሰው የማይገዙ፣ አንገዛም እንታዘዝም ብለው በትዕቢት በዓመፅ የሚኖሩ የኃጥአን ምሳሌ ናቸው።

እግዚአብሔር ከአንድ ባሕር ሦስት ወገን የሆኑ ፍጥረታትን ፈጠረ። ከአንድ ማኖ ገበ ሦስቱ ትውልድ። ትውልደ ያፈት፣ ትውልደ ካም ይጠመቁ ዘንድ መሰጠቱን ያሳያል። ከዚህም በተጨማሪ ልጅነት በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ለመሰጠቷም ምሳሌ ነው።

መልመጃ ፪፮

፩. ሦስቱ የሐመስ ፍጥረታት አንድ በሚሆኑባቸውና በሚለያዩባቸው ነጥቦች ላይ ተወያዩ።

፪. የሐመስ ፍጥረታት "የደመ ነፍስ ሕይወት አላቸው" ሲባል ምን ማለት ነው?

፫. ሦስት ወገን ፍጥረታትን ያስገኘው ባሕር የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነች ተገልጧል። እንዴት?

፬. የሐመስ ፍጥረታት ቢጠፉ በአናንተ ላይ የሚያስከትለው ተዕዕና አለ?

፭. ከአሥሩ ማዕረጋት ለመድረስ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ካለባችሁ አሁኑ አስቀድማችሁ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ በዙፍ ውስጥ ተወያይቡትና በየራሳችሁ ፊጽሙት።

## ፫፯ የዕለተ ዓርብ ፍጥረታት

ፎቶ፩ ትርጉም፦ ዓርብ፦ ዓርቦ ካለው ገሥ ሲወጣ ተካተተ፣ ተከተተ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ዓርብ ማለትም መከተቻ ማለት ነው። ይኸውም ስድስተኛይቱ ዕለት (ዕለተ ዓርብ) የፍጥረታት መከተቻ፣ መፈጸሚያ፣ ማብቂያ መሆኑን ያመለክታል። ከዕለተ አሑድ እስከ ሐመስ ላሉት ዕለታት በተሰጠው የስያሜ አባባር ቢተየል ናር ዓርብ ባለው ፊንታ ሰዱስ ስድስተኛ ቀን በተባለ ነበር።



### ፎቶ፩ የእንስሳት፣ የአራዊትና የአዕዋፍ ተፈጥሮ

ዕለተ ዓርብ በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት ልውል እግዚአብሔር ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ እንስሳት ንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ ብሎ አዘዘ። ዘፍ.፩ ፡፳ ፪። በቃሉም መሠረት ወዲያውኑ ሦስት ዓይነት ፍጥረታት ተፈጠሩ። ዘፍ.፩ ፡፳ ፪።

ሦስቱ ፍጥረታት፦

- እንስሳት፦ ሣር ነጭተው፣ ውኃ ተነንጭተው የሚኖሩ፣
- አራዊት፦ ሥጋ በጭቀው ደም ተነንጭተው ውኃ ጠጥተው የሚኖሩ፣
- አዕዋፍ፦ የዛፍ፣ የአህል ፍሬ ለትመው፣ ሥጋ በልተው፣ ውኃ ጠጥተው የሚኖሩ ናቸው።

የዕለተ ዓርብ ፍጥረታት የደመ ነፍስ ሕይወት፣ የደመ ነፍስ አውቶት ያላቸው ከአራቱ ባሕርያት ሥጋ የተፈጠሩ በልብ የሚባቡ፣ በአንር የሚሸከረከሩና በክንፍ የሚበሩ ናቸው። ሁሉ ንም የፈጠራቸው ሴትና ወንድ አድርጎቸው ነው።

በዕለተ ሐሙስና በዕለተ ዓርብ የተፈጠሩት ፍጥረታት "እንስሳት" በመባል አንድ ቢሆኑም በአኗኗራቸውና በማብራቸው ይለ ያያሉ። የሐመስ ፍጥረታት ከባሕር ተለይተው በየብስ /በም ድር/ መኖር አይችሉም። የዕሉይ መቀት ሲንካቸው ይሞታሉ። የዓርብ ፍጥረታትም ከምድር ተለይተው በባሕር ውስጥ መኖር አይች ሱም። የባሕር ውርጭ፣ ቅዝቃዜ ይገድሳቸዋል።

የዓርብ ፍጥረታት /እንስሳት፣ አራዊትና አዕዋፍ/ በሁለት ይከፈላሉ።

፩. የቤት

፪. የበረሃ (የዱር)

፩. የቤት

ሀ. የቤት እንስሳት ሰው ለእርሻ፣ ለመንቀሳቀሻ፣ ለምግብነት የሚጠ ቀምባቸው ለማዳ እንስሳት ናቸው።

ምሳሌ፦ ላም፣ በሬ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ፍየል፣ በግ. . . ወዘተ ናቸው።



ለ. የቤት አራዊት፦ ቤት በመጠበቅ፣ አውሬ በመከላከል ሰለው ጥቅም የሚሰጡ ናቸው።

ምሳሌ፦ ውሻ፣ ድመት።

ሐ. የቤት አዕዋፍ፦ በቤት ታሣ ተጠልለው፣ በጓሮ ዛፍ ተንጠላጥለው የሚኖሩ ናቸው።

ምሳሌ፦ ዶሮ፣ ርግብ፣ ድንቢጥ ሌሎችም

፪. የበረሃ (የዱር)

ሀ. የበረሃ እንስሳት፦ ሰው ሲያዩ የሚሸሹ፣ በዱር በበረሃ የሚኖሩ ናቸው።

ምሳሌ፦ አጋዘን፣ ፈቆ፣ ሚዳቋ፣ ጎሽ፣ ዝሆን፣ ዋልያ የመሳ ሰሉት ናቸው።

ለ. የበረሃ አራዊት፦ የሰው ጠላቶች፣ ሰው በቀጥታ የማይገሰገል ባቸው ናቸው።

ምሳሌ፦ ነብር፣ አንበሳ፣ ጅብ፣ ቀበሮ . . . ወዘተ

ሐ. የበረሃ አዕዋፍ፦ በዋሻ በፍርክታ ተሸጉጠው በዱር በዛፍ ሰፍ ረው በተራራ ተጠግተው የሚያድሩ ናቸው።

ምሳሌ፦ ጉጉት፣ ኀልገል አንሥ፣ አርኩም . . . ወዘተ

በሰላ በኩልም እንስሳተ ዓርብና አዕዋፌ ዓርብ የሚበሉት ንጹሐን፣ የማይበሉት ርኩሳን ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ርኩሳን መባላቸውም ስለማይበሉ ነው እንጂ በባሕርያቸው ሲፈጠሩ ርኩ ሳን ሆነው አልተፈጠሩም። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብ ሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ "ያ መልካም እንደሆነ አዮ ተብ ሏል። ዘፍ. ፩፡፴፩-፴፪።

፩. ንጹሐን (የሚበሉ) እንስሳት፦

የቤት ወይም የበረሃ እንስሳት ሆነው ሰው ወተታቸውን አልቦ፣ ሥጋቸውን አርዶ የሚመገባቸው፣ ቆዳቸውን አልፍቶ አለበልሶ የሚጠቀምባቸው ናቸው።

ምሳሌ፦ ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ ሰስ፣ ሚዳቋ፣ አጋዘን፣ ድከላ. . .



፪. ርኩሳን (የማይበሉ) እንስሳት፦

ሰው ወተታቸውን አልቦ፣ ሥጋቸውን አርዶ የማይመገባ ቸው የቤትና የበረሃ እንስሳት ርኩሳን፣ የማይበሉ ይባላሉ።

ምሳሌ፦ ፈረስ፣ በቅሎ፣ አህያ፣ ግመል፣ ጥንቸል፣ አሳማ . . . ሌሎችም

ሀ. ንጹሐን አዕዋፍ፦

የሰው ልጅ በቤት አርብቶ፣ ከዱር አድኖ፣ ይዞ አርዶ የሚመ ገባቸው ናቸው። ምሳሌ፦ ዶሮ፣ ቆቅ፣ ጅግራ. . . የመሳሰሉት

፪. ርኩሳን አዕዋፍ፦

ሰው በቤቱ አርብቶ፣ ከዱር አድኖ የማይበላቸው ናቸው። ምሳሌ፦ ጭላት፣ ገጹ፣ አርኩም፣ ጉጉት. . .

ዘመደ አራዊት /ነብር፣ አንበሳ፣ አነር፣ ጉሬዛና የመሳሰ ሉት/ ወተታቸው ባይጠጣም፣ ሥጋቸው ባይበላም ቆዳቸው ግን ሰፍቶ ለስልሶ ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል።

መልመጃ ፫፯

፩. የሐመስና የዓርብ ፍጥረታት ልዩነታቸውና አንድነታቸው ምን እንደሆነ ግለጡ።

፪. የዓርብ ፍጥረታት በስንት ይከፈላሉ? ዘርዝሩ።

፫. ግመልና አሳማ ኮርኮሳን ወይም ኮማይበሉት እንስሳት ወገን የተ መደቡት ምን ስለሆነ ነው?

፬. "በምግብ ራስን ለመቻል" በሚል መመሪያ መሠረት የማይበሉ እንስሳትንና አራዊትን ግለጡ ብትባሉ ምን ታደርጋላችሁ?

### ፎቶ፫ የአዳም ተፈጥሮ

መልመጃ ፫፱

፩. ተማሪዎች ስለተፈጥሮአችሁ ታውቃላችሁ? እርስ በርሳችሁ ተወያዩ።

፪. በክፍላችሁ ውስጥ ካሉትና በተውልድ ሥፍራ፣ በቋንቋ የሚለ ያዩ ተማሪዎችን ተፈጥሮ ስለጣችሁ ጋር እስተያዩት። በሥነ ተፈ ጥሮ ተለያይተናል ኢንድ ከሆናችሁ አንዱት አንድ አንድ ሆናችሁ አብሮ ከመሥህራችሁ ጋር ተነጋገሩ።

ዓርብ በመጀመሪያው ሰዓተ መንፈት /በንግህ/ ልውል እግዚአብሔር አዳምን ፈጠረው። አስክሁን የተፈጠሩት ፍጥረታት በሐልዮና በንቢብ የተፈጠሩ ሲሆን እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው በገቢር በእጆቹ በማበጃጀት ነው።

እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ፈቃዱ ስለሆነ ጊዜው በደረሰ ወቅት "ንግበር ሰብእ በአርአያነ፣ ወበአምሳሊነ፤ ሰውን በመልክ ችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" አለ። ዘፍ.፩÷፳፮ ይህንንም ብሎ፦

- ከአሳት፣ ከነፋስ፣ ከውኃ፣ ከመሬት አንዋደው አዋርቀው ሰይቀው አንደ አሸት ፈልፍሰው፣ አንደ ዘንግ መልምሰው፣
- ሦስት ግብራት /ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነት/ ያሳት ነፍስ አምኀበ አልቦ /ከለመኖር/ አምጥተው አንድ ላይ አዋ ሕደው በአርአያቸውና በምሳሌያቸው ፈጠሩት።

ይህም ማለት ግዙፍ አካል ሥጋን ከአራቱ ባሕርይዎት ከፍሉ አንናኝቶ፣ በሥጋ አለበልሰ፣ በደም አርሶ፣ በጅማት አያይዞ በአጥንት አጽንቶ፣ ረቂቅ አካል ያላት ነፍስን ካለመኖር አስገኝቶ አውቀት፣ ቃል፣ ሕይወት ሰጥቶ ሥጋንና ነፍስን አዋሕዶ ፈጠረው ማለት ነው። አዳም ሲፈጠር በአካሉ ሥጋውና በአካሉ ነፍሱ መካከል መቀዳደም የለበትም፣ አልነበረበትም። ይህ ቢኖርበት ኖሮ ሥላሴ ንግበር ሥጋ፣ ወንግበር ነፍሱ ባሉ ነበር።

እግዚአብሔር ሰውን ፈጥሮ ሲያበቃም የሕይወትንም አስትን ፋስ እፍ አለበት። በዚህም በደመ ነፍስ ሕያዋን ከሆኑ እንስሳት ለየው። ከብርን፣ ልጅነትን ሰጠው። በዚህም ሰው ሕያው ፍጥረት ሆነ። ዘፍ.፩÷፳፮።

ሥላሴ አዳምን በአርአያቸው፣ በምሳሌያቸው ፈጠሩት ሲባ ልም መሠሰሰሳላቸው።

ሀ. <u>በመልክ ነው</u>።

- ሥላሴ በኅይሉ የሚታይ በአጅ የሚዳሰስ ግዙፍ አካል ባይኖራ ቸውም በሰው ላይ ያለ መልክ ነገር ግን ረቂቅ የሆነ መልክ አላ ቸው። መዝ.፴፪÷፮፤ ሰቆ.፫÷፩፤ ኢሳ.፵፰÷፲፫፤ ሄዘ.፩።



ለ. <u>በእንድነት በሦስትነት ነው</u>።

- ሥላሴ ፡ ለባዘ.ያን፣ ነባብያን፣ ሕያዋን ናቸው። ይሁን እንጂ አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም።
- አዳምም አንድ ሰው ሲሆን ለባዊ፣ ነባቢ፣ ሕያው ነው።

ሐ. <u>በሕያውነት ነው</u>።

- ሥላሴ። ሞት የለባቸውም። ለዘለዓለም ሕያዋን ናቸው።
- አዳም (ሰው) በሞት ፈርሶ፣ በስብሰ መቅረት የለበትም። "ወብነ ነፍስ እንተ ኢትመውት በህላዌሃ፣ ውስተ ነፍስትክ ርቱዕክ ትሰመይ አርአያ እግዚአብሔር፣ በሕያውነቷ የማትሞት ነፍስ አለችን። በነፍስህ አርአያ እግዚአብሔር ትባላለሀ እንዳሉ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው።

መ. <u>በፍጥረት ነው</u>።

- ሥላሴ ሁሉን ይገዛሉ።
- አዳምም ሁሉን ይገዛ ዘንድ ከእግዚአብሔር ተሰጥቶታል።

እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው በሠላሳ ዓመት ጎልማሳ መጠን ነው። ቋመናው እንደ ሰብኢ ረዓይት ሳይረዝም እንደ ድንክ ሳያጥር መካከለኛ ሆኖ መልክ መልኳም ሰው ነበር። አዳም ማለትም ያማረ ማለት ነው።

እግዚአብሔር አዳምን "ሰብኦ አለው። ሰብኢ ሳብዕ ካለው ቃል ሲገኝ ሰባት ነገር ያለው ማለት ነው። ይኸውም አራቱ ባሕ ርያተ ሥጋና ሦስቱ ግብራተ ነፍስ ናቸው።

ቀደም ሲል የፈጠራቸውን ፍጥረታት በሠርክ (ቡዶዓማይ ሰዓተ ሌሊት) ፈጥሮ አዳምን በነግህ ፈጠረው። ሠርክን ጨለማ ይሰተሰዋል። እንስሳትን፣ አራዊትንና አዕዋፍን ጨለማ በሚከተ ሰው ሠርክ መፍጠሩ።

- ጽሰ-ማነ አእምሮ /እውቀት የሌላችሁ ናችሁ/፣
- መዋቲ ናችሁ፣
- በምድር በስብሳችሁ፣ ፈርሳችሁ ትቀራላችሁ ሲል ነው። ነግህን ብርሃን ይዘተሰዋል። አዳምን ብዙህ አእምሮ ያለህ ነኽብን ብርሃን ይዘተሰዋል። በምግባር ብትጎዳ ብርህ መሃሳሥተ ሰማያት ትጠብትሃለች ቢለው ነው።



ሥላሴ አዳምን ሲፈጥሩት ድካም፣ እንቅልፍ፣ መንቃት የሚሰማማው አድርገው ውታል። ድካም እንቅልፍ የሥጋ፣ መን ቃት፣ መትጋት የነፍስ ግብር ነው። ከዚያም በተጨማሪ ሌሱቹን ፍጥረታት /እንስሳት አራዊትና አዕዋፍ/ አስንንብሰ፣ አዳምን ደግሞ አቅንቶ ፈጥሮታል። አዳም ገዝር፣ አናንቶ ተገዝር፣ አዳም ትንሣኤ አለው አናንቶ ግን የላችሁም ሲል ነው። በተጨማሪም አዳ ምን መቆም፣ መቀመጥ፣ መተኛት፣ መነሣት እንዲችል አድርገ ውታል።

- በመቆሙ ሰማያዊነቱን፣
- በመቀመጡ ምድራዊነቱ፣
- በመተኛቱ መሞቱን፣
- በመነሣቱ ትንሣኤውን ያሳያል።

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ካከናወነ በኋላ አዳምን ሃያ ሁሰቱኖ አድርጎ ፈጠረው። ይህም፦

፩. ደግ አባት የወለደው ልጁን ኩሱ ከመጻሩ በፊት ለኑሮ የሚ ያስፈልገውን ሁሉ እንዲያሟላለት ጌታ እግዚአብሔርም አስ ቀድሞ የሚኖርበትን ዓለም፣ የሚበላውን የሚጠጣውን የሚገዛውን የሚነዳውን ሁሉ ፈጥሮ አዳምን አከገኘ፣

፪. ዐሠርቱ ቃሳተ አሪት፣ ስድስቱ ቃሳተ ወንጌል፣ አምስቱ አዕ ማደ ምሥጢር /ሃያ አንድ ይሆናሉ/ እነዚህን የሚፈጽሙ ጻድቃን ሲበዙ፣ ሲመሱ ዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲፈርድ የመምጣቱ ምሳሌ ነው።

ሥላሴ አዳምን ማዕከለ ምድር ቀራንዮ ኤልዳ በተባለች ቦታ ከፈጠሩት በኋላ አርባ ቀን በመላእክት አስጠበቁት። በዝህ አርባ ቀናት ውስጥ መላእክት አየጠበቁት አየተራዱት አውቀቱ ሲሰፋሰት ሃይማኖቱ ሲጸናለት በአርባኛው ቀን መላእክት፦

- የብርሃን ልብስ አጎናጽፈው
- የብርሃን ዘውድ አቀዳጅተው
- የብርሃን በትር አስይዘው



- በብርሃን ሠረገላ አስቀምጠው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘፈጠሮ ለአዳም አያሉ በዕሰቱ ዓርብ በሦስት ሰዓት ወደ ገነት አገቡት። መጽ.ኩፋ. ፬÷፩።

መ. <u>ሃይማኖቱ የጸናለት</u>።

- ሌሱቹን ፍጥረታትና ራሱን በመመርመር፣
- ራሱን በራሱ እንዳላነገኝ ሌሱችም ፍጡራን እንደሱ ሁሉ ራሳ ቸውን በራሳቸው እንዳላነገኙ በመረዳት ነው። ፈጣሪውንም አውቆ ሰገደለት፣ ተገዛለት ፈራው። እግዚአብሔርም ፍጥ ሬቱን ለአዳም አስገዛለት። ለአዳም ያልተገዙለት ፍጥረታት ሥላእኩት፣ ለማያት፣ ብርሃንና ጨለማ እንዲሁም ጠፈር ናቸው።

<u>መልመጃ ፫.፮</u>

፩. እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን አንፍጠር በማ ለት አዳምን እንደፈጠረው መጻሕፍት ያስረዳሉ። ሰው እግዚአብ ሔርን እንዴት እንደሚመስሰው ከሌቃውንት ቤተክርስቲያን ጠይ ቅ።

፪. አያንዳንዳችሁ መቼ ተፈጠራችሁ?

፫. ሰው ከእንስሳት፣ ከአዕዋፍና ከአራዊት የሚለይባቸውን ነገሮች በዝ ርዝር አስረዱ።

፬. አዳም ኤልዳ በተባለች ምድር ተፈጥሮ ሃይማኖቱ ከጸናለት በኋላ በአርባኛው ቀን በመላእክት ታጅቦ በታላት ክብር ወደ ገነት ገባ። ይህ ነገር ምንን ያስረዳናል?

፭. አንተ የተፈጠርከው ለምን እንደሆነ አስበህ ታውቃለህ? ካለብህስ የተፈጠርከለትን ዓላማ ምን ያህል ፈጽመሃል?

<u>ዮ.፮.፬ የሔዋን ተፈጥሮ</u>

እግዚአብሔር እንስሳት አራዊትንና አዕዋፍን የፈጠረው አዳም ብቻ ነው። ነጠላ ፍጥረት ሆኖ የተፈጠረው ከቀ ረጻት እንደሚያስረዳነው። አዳምን ብቸኝነት ተመል ምንት "ሰከ ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" የምት መቸውን ረጻት እንፍጠርለት" አለ። ዘፍ. ፪÷፲፰።

በዚህም ውሳኔ መሠረት ረዳት ይፈጥርለት ዘንድ በ፣ ፵ም ላይ እንቅልፍን ጣለበት፡፡ አጅግም ሳያንቀላፋ አጅግም ሳይነቃ በመንቀላፋት በማንቀላፋት መካከል ሳለ ከጎኑ አንዲት አጥንት ወሰደ ያቺን የወሰዳትን አጥንት ሙሉ አካል አድርጎ በነፍስም በሥጋም መገኛዋ አዳምን አላከለ፡፡ አስመሰለ፡፡ በተ ፈጥሮ ጠባይ ከአዳም ሳያሳንሳት በአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ መጠን ፈጠራት፡፡ ፈጠራት ሲባልም እንግዳ ፍጥረት ማስገኘት ሳይሆን ስአዳም አካል የነበረችው ሔዋን በሠልወና እንድትገለጥ አደረጋት ማለት ነው፡፡

አዳምም ከጎኑ አጥንት እርሱን መስላና ከእርሱ ተካክላ የተፈጠረችውን ፍጥረት ባያት ጊዜ

- ከአጥንቴ የተገኘች አጥንት፣
- ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት፡፡ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል አላት፡፡ ዘፍ.፪÷፳፩-፳፫፡፡

ሴት ስተባለችውም ሔዋን ብሎ ስም አወጣላት፡፡ ሔዋን- ማለትም የሕያዋን እናት ማለት ነው፡፡ ዘፍ. ፫ ÷፳፡፡

ሔዋን ስአዳም ረዳት ሆና ተፈጠረች፡፡ ረዳትነታ:-

- ልጅ በመውለድ፣
- ከፍትወት ሥጋዊትና
- ከብቸኝነት ስለምትረዳው ነው፡፡

አግዚአብሔር አዳም በመኑ ትና በመንቃት መካከል ሳለ አጥን ቱን ከጎኑ የወሰደው:-

ሀ. ተኝቶ ሳለ ወስዷት ቢሆን ምትሐት መስሎት ከየት መጣች ብኝ ብሎ በፈራት ነበር፡፡

ለ. ፈጽሞ ነቅቶ ሳለ ወስዷት ቢሆን ከአካሉ አካል ፈሥጋ ሲወሰድ ያመው ነበጠላት ነበር፡፡

ሐ. አዳም ሚሰክለ ነፍሡ ወንቃሕ (በእንቅልፍና በመንቃት መካ ከል) ሳለ ሔዋንን መፍጠሩ ጌታ በዕለተ ዓርብ ምሱን በሥጋ ሕያው በመስቀሉ ሆኖ ስለአዳምና ስለሔዋን ድንጉት መዝ ገሀን የሚስገኝ ምሳሌ ነው፡፡ ፩-፪፡ ፅጹ. ፫-፲፩፡፡



ሔዋንን የፈጠራት ከአዳም ማዕከላዊ ሰውነት ወስዶ ነው፡፡ ከፍ ብሎ ከግንባሩ፣ ዝቅ ብሎ ከእግሩ አልፈጠራትም፡፡ ይሸውም:-

- ግንባር የባል እግር የቤተሰብ ምሳሌ ነው፡፡ እርሷ በመካ ከል ካለ አካል መገኘቷ ከባሏ በታች ከቤተሰቡ በላይ መሆ ኗን ሲያሳይ፣
- አንድም ትከናነብ ሲላት ነው፡፡ ጎናችን ምን ልብስ ቢያጣ በእጃችን እንዲሸፈን ከጎን የተፈጠረች ሴትም መሸፋፈን አለ ባት ሲል ነው፡፡ ፩ቆሮ.፲፩÷፲-፲፪፡፡

ሔዋን በተፈጠረችበት በኤልዳ በመላእክት እየተጠበቀች ሰማንያ ቀናት ቆየች በሰማንያኛውም ቀን ለአዳም የተደረገው ሥርዓት ሁሉ ሳይጓደል ተፈጽሞላት በመላእክት ታጅባ ወደ ገነት ገባች፡ አዳምና ሔዋን የሕፃናት፣ ገነት የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናቸው፡፡ ወንዶች ሕፃናት በአዳም አምሳል በተወለዱ በአርባ ቀናቸው፣ ሴቶች ሕጭናት በተወለዱ በሰማንያ ቀናቸው ወደ ቤተክርስቲያን ተወስደው ክርስትና ይነሣሉ፡፡

ልውል አግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን በመላእክቱ አሳጅቦ በታላቅ ክብር ወደ ገነት ካገባቸውም በኋላ "ገነትን ጠብ ቃት ተገክባክባት" ብሎ አስረክቦው፡፡ ዘፍ.፪÷፲፭፡፡ አዳም እንዲጠ ብቃት በተሰጠችው ገነት ሦስት ዓይነት ዕፀዋት ነበሩባት፡፡ እነዚህም:-

- ብላ ያለው፣
- አትብላ ያለው ዕፀ በለስ፣
- ብላም አትብላም ያላለው ዕፀ ሕይወት ናቸው፡፡ዘፍ.፪÷፱-፲፯፡፡



አዳም አትብላ የተባለው ዕፀ በለስ:-

፩. አዳም ስአግዚአብሔር ያለው ፍቅር የሚገለጥባት፣ ዮሐ.፲፭÷፲፭፣ ፩ዮሐ.፫÷፲፬

፪. ፍጡርነቱ የሚታወቅበት፣

፫. ነፃ ፈቃዱ የሚገለጥባት ናት፡፡ ዘፍ.፪÷፲፮፡፡

አዳምና ሔዋን በሕገ አግዚአብሔር ጸንተው በገነት ሺሳት ዓመት ከኖሩ በኋላ በሰባተኛው ዓመት በምክረ ከይሲ ተታለው የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ በመተላለፋቸው ከገነት ተባረሩ፡፡ የተባ ረሩትም በሠርክ ሰዓት ሲሆን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ጌታችን በከፈለው ካሣ በሠርክ በዕለተ ዓርብ ከነልጆ ልጆቻቸው ተመልሰው ወደ ገነት ገብተዋል፡፡



# የመጨረሻ ፍጥረት



ሰዕል አራት:- አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ
(በጊደላሱስ ያዩረሰባቸውን ፈተናና ውድቀት የሚያሳይ)

**መመሪያ I. የሚከተሉትን ዐነገሮች ትክክል የሆነውን አውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት ብለህ ጻፍ (ፊ)።**

፩. አጻም በመጀመሪያ በመፈጠሩ በሰውነት ባሕርይ ከሉዋን ይበልጣል።

፪. "መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮችንም የአሳት ነበልባል የሚያደርግ" የሚለው ቃለ እግዚአብሔር መላእክት ከነፋስና ከአሳት መፈጠራቸውን ያስረዳል።

፫. ዕፀ በለስ የእግዚአብሔር ፈጣሪነት የአጻም ፍጡርነት ይታወት ዘንድ የተሰጠች ዕፅ ናት።

፬. የዓርብ ፍጥረታት አጻም በተፈጠረበት ዕለት በመፈጠራቸው ኩሉ ሙሱ ፍጥረታት ይበልጣሉ።

፭. እግዚአብሔር የሚታየውንም የማይታየውንም ዓለም ያስገኘው በስድስት ቀናት ውስጥ ብቻ ነው።

፮. ሳጥናኤል የተፈጠረው ከመላእክት ሁሉ በፊት ነው።

፯. ዕፅዋት፣ አዝርዕትና አትክልት የተፈጠሩት በዕለተ ሰኞ ነው።

፰. ፀሐይ የጻድቃን ምሳሌ ስትሆን ጨረቃ ደግሞ የኀጥአን ምሳሌ ናት።

፱. ሴሎች ፍጥረታት በሐልዮና በንቢብ ሲፈጠሩ አጻም ግን የተፈጠረው በገቢር ነው።

**መመሪያ II. በሦሰ ረድፍ ያሉትን ሐረጉች በሦስ ረድፍ ካሉት ሐረጉች ጋር አዛምድ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. የመጀመሪያው ፍጥረት | ሀ. የፀሐይ፣ ጨረቃና፣ ከዋክብት መመላለሻ |
| ፪. ሌሮር፣ ራማ፣ ኤረር | ለ. በውኃ የሚኖሩ እንስሳት |
| ፫. የጠፈር ጥቅም | ሐ. አራቱ ባሕርያተ ሥጋ |
| ፬. በጫፋቸው የሚያደሩ ዕፅዋት | ሠ. ጥረው ግረው ራሳቸውን የሚረዱ ሰዎች ምሳሌ |
| ፭. የሐሙስ ፍጥረታት | ረ. የመላእክት ከተሞች |



**መመሪያ III. በሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

፩. ሥላሴ ለቅዱሳን በፈለጉት መልክ የሚታዩት፣ የሚገለጡት በየትኛው ሰማይ ሆነው ነው?
ሀ. በሰማያዊት ኢየሩሳሌም
ለ. በሰማይ ውዱድ
ሐ. በመንበረ ስብሐት
መ. በጽርሐ አርያም

፪. ለመናብርት አለቃ ሆኖ የተሰየመው መልአክ
ሀ. ቅዱስ ገብርኤል
ለ. ቅዱስ ራጉኤል
ሐ. ቅዱስ ሩፋኤል
መ. ቅዱስ ሚካኤል

፫. ለክህደተ ሳጥናኤል ዋና ምክንያት የሚሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ዕፀ በለስን በመብላቱ
ለ. በተፈጠረበት ቦታ አለመገኘቱ
ሐ. መላእክትን እኔ ፈጠርኪችሁ በማለቱ
መ. እግዚአብሔርን በመሳደቡ

፬. በፊልሳማ የሠደ ሕዝብ ብርሃን አዮ የሚለው ጥቅስ የሚገኘው የት ነው?
ሀ. መዝ. ፻፫፥፪ሸ
ለ. ዩሐ. ፩፥፬
ሐ. ኤር. ፮፥፱
መ. ኢሳ. ፱፥፪

፭. ስው ወደ ላይ ማየቱ ምንን ያመለክታል?
ሀ. ብዙ ሳማያት መኖራቸውን
ለ. ሁሉ ለእርሱ የተሰጠው መሆኑን
ሐ. ትሃግሌ ያለው ፍጥረት መሆኑን
መ. ሁሉንም

፮. ሃምኖና ሦስት ስሞች የትኞቹ ናቸው?
ሀ. ጻባር፣ ሃምኖር፣ መሬት
ለ. መሬት፣ ሲኦል፣ ገነት
ሐ. መሬት፣ ውኃ፣ ኧርዝ
መ. ሳንጅ፣ ኧርዝ፣ ወርልድ

፯. መዓዝነ ዕለት ስንት ናቸው?
ሀ. ስድስት
ለ. ሰባት
ሐ. አሥር
መ. ሦስት

፰. ንጹር መላእክት፣ ይመደባሉ?
ሀ. ንጹሐ ነፍስ
ተሠጥሞ፣ ከሢነ አሳት ከየትኛው ማዕረግ
ሐ. ንጹሐ ሥጋ
ለ. ንጹሐ ልቡና
መ. ሁሉም



፱. ለእግዚአብሔርና ለሰው በፍቅር በትሕትና የሚገዙ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙና የጻድቃን ምሳሌ የሆኑት፡-
ሀ. በልብ የሚኖሩ እንስሳት
ለ. በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳት
ሐ. ሰው የሚበላቸውና ለሰው የሚገዙ እንስሳት
መ. በክንፋቸው የሚበሩ እንስሳት

**መመሪያ IV. የሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ (ሽ)።**

፩. በኦሪት ዘፍጥረት ፩፥፳፮ ላይ ስለሰው ልጅ አፈጣጠር "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው" ተብሏል። በኦሪት ዘፍጥረት ፪፥፲፮-፳፩ ላይ ደግሞ በስምንተኛው ቀን ሔዋን ከአዳም ጎን በተወሰደ አጥንት እንደተፈጠረች ይተርካል። ሁለቱ እንዴት ሊስማሙ ይችላሉ? ከሊቃውንቱ ጠይቃችሁ በጽሑፍ አቅርቡ።

፪. መላእክት ሔዋንን ወደ ገነት ሲያስገቧት ለአዳም የተደረገውን ሥርዓት ሁሉ ፊጽመውሳታል። ይህ ምንን ያስረዳል?

፫. የአጻምና የሔዋን የጎጎት ኑሮ፣ ከገነት ለመውጣት ያበቋቸው ምክንያቶች እንዲሁም ያገኙት እንዲሁም ከመምህራችሁ ጋር ተወያይባቸው።

፬. ከስድስቱ ዕለት ፍጥረታት መካከል
- እስከ ዕለተ ምጽአት የሚቆዩት
- ከዚያም በኋላ ጎልፈት የሰለባቸው የትኞቹ ናቸው? አንተስ?

፭. እግዚአብሔር ከዕለተ አሑድ እስከ ዕለተ ዓርብ ድረስ ስፈጠረው ፍጥረት ሁሉ የመኖሪያ ሥርዓት ሠርቷል። ሁሉም ፍጥረት በተሠራለት ሥርዓት ጸንቶ ይኖራል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ሰውስ ካልሆነ ስምን?

፮. እግዚአብሔር በዕለት ውስጥ ባሱት ሃያ አራት ሰዓታት ሥራ ሠርቶላቸዋል። ይህ ምንን ያሳያል?

፯. አጻምና ሔዋን ሳይፈጠሩ አንተ በገነት ብትኖርና የጸደቃችሁን ፈተና ቢተርብልህ የምትመልሰው ምን ይመስልሃል?



# ምዕራፍ አራት

## ፬ ቀዳሚት ሰንበት

### ፬፩ ትርጉም

ቀዳሚት ሰንበት ዕለተ ሳብዕ ትባሳለች። ሰባተኛው ዕለት ማለት ነው። ሰባተኛዋ ዕለት ቀዳሚት ሰንበት ናት። ሰንበት ማለትም ዕረፍት ማለት ነው።

### ፬፪ የቀዳሚት ሰንበት ታሪክ

በዚህች ዕለት ልዑል እግዚአብሔር ሊፈጥረው ያሰበውን የወደደውን ሃያ ሁለቱን ሥነ ፍጥረት ፈጥሮ አከና ውኖ አረፈባት። ዘፍ. ፪ ÷ ፪።

ዕለተ ሳብዕ ፍጥረት ከላልተፈጠረባት የሥራ ፍታት፣ ዕለተ ጽርዓት፣ ጥቅም የለሽ ዕለት ተብላ አትናቅም አትቃሰልም፣ አታንስምም። እግዚአብሔር አክብሮ ዐርፎባታልና። የክብሯንም መጠን የምንረዳው እግዚአብሔር እንዳረፈባት እንጻከሰራት ስናጤን፣ ሕዝበ እግዚአብሔር ለተባሱት ለአሥራ ሬሉል ዘሥጋ ዐሠርቱ ትእዛዛት ሲሰጥ የሰንበትን ቀን አክብሩ በመባሳና ይህችንም ዕለት የናቁ ሰምች በሞት እንዲቀጡ መደረጉን በመመልከት ነው። ዘጸ÷ ፴፤ ዘጉ.ፐ፩ ÷፵ ፱-፵ ፮። በሌሎች ዕለታት የተገኙት ፍጥረታት ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲሰጡ በቀዳሚት ሰንበት የተገኘው ዕረፍትም ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲ ይጠቅማል። ልዑል እግዚአብሔርም ለሰው ልጅ ጥቅም ያዘጋጃቸውን ፍጥረታት እንደባረካቸው ሁሉ ቀዳሚት ሰንበትንም ባረከት ቀደሰት። ዘፍጥ.፪ ÷ ፫። ጌታችን ሐሮም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም እንዲል።

በመሆኑም እግዚአብሔር ባርኮ የቀደሳትን ዕለት ግክበር ይገባል። እንዲሁም "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስቡ ተባሏል። እንዲሁም "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው
- አንተ ባለቤትህ፣ ዘጸአ. ፳- ፰። በዕለተ ሰንበት፡-
- ወንድ/ ቤት ልጅህ፣

- ሱሌህ ገሪድህ (ሠራተኛህ)፤
- ከብትህም ዕረፍት ተብሏል።

"ዕረፍት" ያለው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የፍጥረቱን አቅም ያውቃል። በፍጥረቱ ሕይወት ውስጥ ያለው ውጣ ውረድ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የፈቀደውን መልካሙን ሥራ ይሠራ ዘንድ ተፈጥሯል። ኤፌ.፪ ÷ ፲። የተፈቀደለትን ሥራ ያልሠራ ፦የማይሠራ ሰው ደግሞ ይበላ ዘንድ አልተፈቀደለትም፤ ከዚህ ዓለም ገንዘብ፤ ከጸጋ እግዚአብሔር የተራቆተ ይሆናል። የትሩፋት ሥራ ምችንም ሰመሥራት አይችልም። ፪ተሰ.፫ ÷ ፮-፲፫፤ ምሳ.፳፫ ÷ ፭።

ይህን ሁሉ ውጤት የሚያስገኝለት ሥራውን ሰመሥራት አንድ ሰው ጤንነቱ ሲጠበቅ፣ ጉልበቱ የተሟላና አእምሮው የተረጋጋ መሆን ይኖርበታል። እነዚህን ከሚያያዝባቸው መንገዶች መካከል ታላቁ ዕረፍት ማድረግ ነው። ሰባተኛዋ ዕለት ተባርካ የተሰጠቸው ፍጥረቱ እግዚአብሔርን በማመን ሥርዓት ሃይማኖቱን እንዲፈጽምባት፣ ከሥጋ ድካሙ እንዲያርፍባት አእምሮውን እንዲያድስባት ነው። ዕረፍት ሲባልም እንደ አይሁድ ሥርዓት ሳይንቀሳቀሱ መዋል ሳይሆን ለነፍስ ዕረፍት፣ ሰሥጋም በረከት ሲያስጡ የሚችሉ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በመፈጸም የሚከበር ነው። ለእብነትም በዕስተ ሰንበት፦

- ቃሰ እግዚአብሔር መማር፤
- ንስሐ ገብቶ ቅዱስ ቁርባን መቀበል፤
- የተጣላ ማስታረቅ፤
- ያዘነን የተከዘን ማሪጋጋት፣ ማጽናናት፤
- በተሰያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ፤
- በማቴ.፳፭÷፴፭-፴፮ ላይ የተጠቀሱት ምሣሪራት ይፈጸምባቸዋል።

በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሰንበትን ማክበር ከእግዚአብሔር ዘንድ የማያልቅ ዘላለማዊ በረከትን ያስገኛል። ኢሳ. ፶፮ ÷ ፩-፰።



ሰባተኛዋ ዕለት "ቀዳሚት ሰንበት" መባሏ በሐዲስ ኪዳን የመጀመሪያዋ ዕለት ዕለተ እሑድ ሰንበት ተብላ በመጠራቷ ነው። ይህች ዕለት (እሑድ) ሰንበት ሆና መከበሯም በሐዲስ ኪዳን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታላላቅ ሥራዎች በሰሠሩባት ነው። ለአብነትም..

- በብሉይ ኪዳን፦ ዓለም የተፈጠረባት፣ ቀዳምያት በኵራ፣ የሚሰበሰብባት፣
- በሐዲስ ኪዳን፦ ጌታችን የተወለደባት፣ ትንሣኤውን የገ ጠባት፣ ለሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠባት ናት.

በሐዋርያትም ዘመን በዕለተ እሑድ ይሰበሰቡባት፣ ምጽዋ ይሰበስቡባት ነበር። ይህች ዕለተ ሰንበተ ክርስቲያን፣ የጌታ ቀን ትባላለች። ራእ. ፩ ÷ ፲።

አርቶዶክሳዊቂት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ሁሉቱን ቀናት ቀዳሚት ሰንበትና ሰንበተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ቀን አድርጋ ታከብራቸዋለች። ይህም ሥራን ባለመውደድ ዕረፍትን ለማጣዘት ሳይሆን በታሰ መጻሕፍት የተገለጠ ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር ለአሥራኤል ዘሥጋ ሰንበትን እንዲያከብሩ "ሰንበታቴንም ጠብቁ እኔ እግዚአብሔር እምላካችሁ ነኝ፣ በማለት በብዙ መደብ የሰ ጠው ትእዛዝ ቀዳሚት ሰንበትንና ሰንበተ ክርስቲያንን አንድ ናከብር የሚያመለክት ነው። ዘሌዋ.፲፱ ÷ ፫፣ ፳፭÷ ፪። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቀዳሚት ሰንበትን እንደ አርሱ ፈቃድ ሳይሆን በራሳቸው መጠበብ ያከብሩ የነበሩ አይሁድ በተሰበ ሰበቡት "ሰበንበት መልካም ሥራ ማሰት ለሥጋና ለነፍስ በረከት ሊያሰጡ የሚችሉ ተግባራትን ሲፈጽሙባቸው እንደሚገባ ሲገ ልጥ ተሸራሰች ገን አሳሰም። ማቴ. ፲፪ ÷ ፲፪።

በአሁኑ ዘመን ሰንበትና ሲሱች በኅላት እንዲሻሩ ስለማይደክመ ሳዎች በመጽሐፍ ቅዱስ "አንድ ሆነው በሌሳቸው በየሕዝባቸው ነ የእግዚአብሔርን በኅላት ከምድር እንሻር አሉ።" ተብሎ ተነግሮባቸዋል። መዝ. ፍ ፫ ÷ ፮።



## የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ ጡ።

፩. የቀዳሚት ሰንበት ጥቅም ምንድን ነው?

፪. ቀዳሚት ሰንበትን ስለማክበር አስመልክቶ ቤተክርስቲያን የምታስተ ምረውን ትምህርት ከመምህራን ጠይቃችሁ ተወያዩበት።

፫. ቀዳሚት ሰንበትንና ሰንበተ ክርስቲያንን በዓል አድርጎ ማክበር በአንድ ሀገር ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብላችሁ ታምናላችሁ? በመረጃ አስደግፋችሁ ተወያዩበት።

፬. አንድ ምእመን ቀዳሚት ሰንበትና ሰንበተ ክርስቲያንን በምን ዓይነት መልኩ ማክበር አለበት?

፭. ከዚህ በፊት ሰንበትን የምታከብረው በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር?



# ምዕራፍ አምስት

## ፭. ሃያው ዓለማት

ከአላት፣ ከነፋስ፣ ከውኃና ከመሬት የተፈጠሩ ሃያ ዓለማት አሉ። እነዚህም፦

ሀ. **ዓለማተ አሳት**፦ የአላት ግብር፣ ጠባይ ከሆኑት (ብርሃን፣ ውሪ የትና ይብሰት) የተፈጠሩ ናቸው። እነዚህም በቁጥር ዘጠኝ ናቸው። ሰባቱ ሰማያት፣ ምጽንዓተ ሰሜይ ገሃነመ እሳት የሚባሱት ናቸው።

ለ. **ዓለማተ ነፋስ**፦ ነፋስ የመሳበት በነፋስ የጸና የረጋ ዓለም ማለት ነው። ዓለማተ ነፋስ ሁለት ናቸው። ሐኖስን የተሸከመው ባቢል የተባለው የረጋ ነፋስ፣ ይህን ዓለም የተሸከመው የም ድር ንጣፍ፣ ንዝንዝ የሆነው ነፋስ ናቸው።

ሐ. **ዓለማተ ማይ**፦ የውኃ ዓለም፣ ከውኃ የተፈጠረ፣ ውኃ የመሳ በት ዓለም ነው። ዓለማተ ማይ አራት ናቸው። እነዚህም ሐናስ፣ ጠራር፣ ውቅያኖስ፣ ከምድር በታች ያለው ውኃ ናቸው።

መ. **ዓለማተ መሬት**፦ የመሬት አካል የሆኑ ከመሬት (ከአፈር) የተፈጠሩ ናቸው። በቁጥር አምስት ሲሆኑ አስከ ጎልፈተ ዓለም ድረስ የተሰያዩ አገልግሎቶችን ለሰው ልጆች ያበረክታሉ። እነዚህም፦

፩. ምንኛናርስት ዓለም፦ ከአዳም ወድቀት በኋላ ለሰው ልጅ መኖሪያነት የተሰጠች ናት።

፪. ብሔረ ብፁዓን፦ የመሬት አካል ናት። ራሳቸውን ከዚህ ዓለም ግብር ለጠበቁ በፈቃደ እግዚአብሔር ለጸኑ ብፁዓን እግዚአብሔር ያዘጋጃት ምድር ናት። እግዚአብሔር ባወ ቀው ይህችን ምድር በጎየአን ከመታወቅ መኖሪያም ከመ ሆን ሰውጅታል። ብሔረ ብፁዓን ከንቢረ ጎጢአት በስተ ቀር የጽድቅ ሥራዎች የሚሠ ራባትና በውስጧም ያሉ ብፁዓን በቅዱስ ኃብዞ እንደሚኖሩ ገድሰ ቅዱስ ዞሲማስ ያስረዳል።

ሯ. ብሔረ ሕያዋን፡- ለሕያው እግዚአብሔር የተገዙ፣ የቀኑ ከዚህ ዓለም ግብር የራቁ የተጠበቁ ቅዱሳን የሚኖሩባት ናት። ሔኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ልዑል እግዚአብሔር ከሚኖርበት ዓለም ወደ ብሔረ ሕያዋን አሳረገው። ነቢዩ ኤልያስም ለእግዚአብሔር በመቅናቱ ምድራዊውን ንጉሥና ንግሥት ሳያፍር ሕገ እግዚአብሔርን በማስተማሩ እግዚአብሔር በሕይወተ ሥጋ እንዳለ ወደ ብሔረ ሕያዋን ወስዶታል ዘፍ.፭ ÷፳፬ ፤ ፪ኛነ.፪ ÷ ፲፩።

ፀ. ገነት፡- ዓለመ ጻድቃን፣ አጻምና ሔዋን የነበሩባት እግዚአብሔር በዕሰተ ሠሰስ በቀጻማይ ሰዓተ ሌሊት ያዘጋጃት፣ ያበሻሻት የዕረፍትና የሕይወት የተድላ የደስታ ቦታ ናት።

እግዚአብሔር ብሩህ ብሩሁን መሬት በምሥራቅ ክኄዛ ወዲህ ጠቅልሎ ገነትን ተከለ። በዚህችም ገነት ዕፀ ሕይወትን አስገኘ። ዕፀ ሕይወትም በፍሬ የተመሳች ናት። ፍሬ ሰማኖራትም ጊዜ አይፈጅባትም። ፍሬዋን ለቅመው ቢጎርሱ እርሱን እላምጠው ሳይውጡ ሌላ ፍሬ ትተካለች። መዓዛዋ ጣዕሟ ልብን የሚመስጥ ከመሆኑ የተነሣ ያሰሕመም ነፍስን ከሥጋ ይለያል።

በዚህች በገነት ከዕፀ ሕይወት በተጨማሪ ማየ ሕይወት፣ አራቱ አፍላጋትና ዕፀ በለስ ተክሰጣታል። ማየ ሕይወትም ከዕፀ ሕይወት ሥር የምትፈልቅና ከውተት ሰባት እጅ የምትነጣ ከማር ይልቅ የምትጣፍጥ የሕይወት ውኃ ናት።

አራቱ አፍላጋት፡- በገነት መከከል ካሱት ዕፅዋት ሥር የሚፈልቁ ገነትን በአራቱ ማዕዘን ተመሳትለው የሚያጠጡ ሲሆኑ እነርሱም ግዮን፣ ኤፈሶን፣ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ይባላሉ።

❖ ዕፀ በለስ፡- በገነት በሰተምዕራብ የተተከለች የሕግ ምልክት የሆነች ዕፅ ናት። አጻምና ሔዋን ከነልጆቻቸው ለዚህች ዓለም ስታይና መከራ የተጻረጉትም የሕግ ምልክት ከሆነችው ዕፀ በለስ በሰተው ነው።

❖ ገነት፡- የመሬት አህል ሰትሆን እግዚአብሔር የሰወራት በቀናች ሃይማኖት ጸንተው ምግባር ትሩፋት የሠሩ ቅዱሳን አስበ ዕለተ



ምጽአት ድረስ በአካለ ነፍስ የጽድቅ ዋጋቸውን እየተቀበሉ የሚኖሩባት ጊዜያዊ የጻድቃን፣ የቅዱሳን መኖሪያ ናት። ሰሰ ልዕልናዋ ግን ከሰማይ እንደሆነች ይነገርላታል።

ይ. ሲዖል፡- ድቅድቅ ጨለማ የመላባት ከምድር በታች የሆነች መከከነ ጎጥአን ናት። ጎጥአን እስከ ዕሰተ ምጽአት ድረስ በአካሰ ነፍስ መከራን እየተቀበሉ የሚቆዩት በሰሲዖል ነው።

አምስቱ ዓለማተ መሬት የሚባሱት በብርሃነ መጠን ይበላ ሰጣሉ። ሲዖል ድቅድቅ ጨለማ ናት። ከሰሲዖል ይሠቹ የምንኖርባት ዓለም ትበራሰች። ከምንኖርባት ዓለም ደግሞ ብሔረ ብፁዓን፣ ከብ ሔረ ብፁዓን ብሔረ ሕያዋን፣ ከብሔረ ሕያዋን ደግሞ ገነት ትበራለች።

መመሪያ I. <u>የሚከተሰትን ዐነርኖች ትክክል የሆነውን አውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማስት መልስ ሽ።</u>

ፅ. ዓለማተ ማይ ውኃ የመላበት ዓለም ነው።
ፀ. የምንኖርበት ዓለም ከአጻም ውድቀት በኋላ ሰሰው ልጅ መኖሪያነት የተሰጠች ናት።
ፈ. ዕፀ በለስ በመሬት የተተከለች የሕግ ምልክት የሆነች ዕፅ ናት።

መመሪያ II. <u>በ"ሰ" ሪድፍ ያሰትን በ"ሦ" ሪድፍ ካሱት ሐረጉች ጋር አዛምድ።</u>

| ሢ | ሷ |
|---|---|
| ፅ. ዓለማተ አላት | ሀ. ሔኖክ |
| ፀ. ዓለማተ ነፍስ | ለ. ሐኖስ |
| ፈ. ብሔረ ሕያዋን | ሐ. ዓለመ ጻድቃን |
| ፀ. ገነት | መ. የምድር ጻርቻ |
| ፉ. አራቱ አፍላጋት | ሠ. ምጽንዓተ ሰማይ |
| ጀ. ዓለማተ ማይ | ረ. ግዮን፣ ኤፈሶን፣ ጤግርስ፣ ኤፍራጥስ |



መመሪያ III. <u>ለሚከተሰት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ።</u>

ፅ. ብሔረ ብፁዓንና ብሔረ ሕያዋን የሚባሱት ዓለማተ መሬት አንድነታቸውና ልዩነታቸው ምንድን ነው?
ፀ. ገነት በተባለችው ዓለመ መሬት ስለሱት ዕፅዋት ተወያዩ።
ፈ. ስለ አራቱ ዓለማተ ማይ ከመምህራን በመጠየቅ ሰፉ ያለ ማብራሪያ አቅርቡ።
ፉ. እናንተ በገነት ብትኖሩ የየትኛውን ዕፅ ፍሬ ትመገባሳችሁ?

መመሪያ IV. <u>የሚከተሰትን ስሞች ምን እንደሆኑ ግለራሪያ ስጡ።</u>

ፅ. ባቢል
ፀ. ናዜብ
ፈ. ምጽንዓተ ሰማይ
ፉ. ግዮን



# ምዕራፍ ስድስት

## ፯. ሰውና ሥነ ፍጥረት

ልዑል እግዚአብሔር በአምሳሳዊ ጥበቡና ሥልጣኑ ያስገኛቸው ፍጥረታት በሙሱ በቁጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሰለው ልጅ ጥቅም ይሰጣሱ። የተፈጠሩበት ዓለማም የእግዚአብሔርን ህልውና ከመግለጥ በተጨማሪ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍሳጎት የሚባሱት ምግብ፣ ልብ ስና መጠሰያ የሚገኙት ከፍጥረቱ ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱም በኩል የሰው ልጅ የሥነፍጥረቱን የተፈጥሮ ሥርዓት፣ ህልውና ተመልክቶ ፈጣሪውን ያውቃል ያመሰግናል። የሰው ልጅ ሕይወት ትንሽ ከሚባሰው ፍጥረት ጀምሮ እስከ ትልቁ፣ ከሚታየው፣ ከማይታየው፣ ከሚጻሰሰውና ከማይጻሰሰው ፍጥረት ጋር የተያያዘ ነው።

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሱ ፈጥሮ ካከናወነ፣ ክባረከ በኋላ በሩክ ፍጥረት አጻምን በሁሱ ላይ ገዢ አደረገው። አደራ ሰጠው። ይህም ማስት በራሱ ገንዘብ ላይ ሾመው አሠሰጠነው። አጻም በፍጥረቱ ላይ መሾመ ሊጠቀምባቸው፣ ሊገዝንሰባቸው ብቻ ሳይሆን ሲጠብቃቸው ሲንከባከባቸውም ጭምር ነው። ይገባውም እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበሻሻትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው ባስው ቃል ይታወቃል። ዘፍ. ፪ ÷ ፲፭

ይህ ዐረፍተ ነገር የሚያስረዳን ነገር አሰ። ሰው በሥነ ፍጥረት ጠበቅና የመንከባከብ መብት የተሰጠውን ያህል የማበደት፣ የመዘንበሳበትም ግዴታ እንዳሰበት ነው። ያበጀውና ይጠብቀው ዘንድ ልዩ በምድራዊ ሕይወቱ የተሰጠውን ሥነ ፍጥረት ማጥፋት የሰውን ልጅ በምድራዊ ሕይወቱ ሰተሰያዩ ችግሮች ከመዳረጉም በላይ የእግዚአብሔርን አደራ ሳለመጠበቁ፣ መክሊቱን ሳሰማትረፉ በነፍሱ ያስከያቱዋል። ምነንያቱም የእግዚአብሔርን ህልውና የሚጋልጡ መገናኛዎች የሆኑ፣ የሚያመሰግኑና የሚያስመለኝ ሥነ ፍጥረትን አጥፍልና።

በሥነ ፍጥረቱ ላይ ሙሴ መብትና ሥልጣን ያለው አስገኚያ
ቸው ልዑል እግዚአብሔር በመሆኑ በእደራነት ሰሰው ልጅ የተሰጠ
ውን ዓለም ሥነ ፍጥረቱን ተንከባክቦ እየጠበቀ ከመጠቀም ውጪ
ማጥፋት የሚያስጠይቅ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

ሰው ጋሚአት ሲሠለጥንበት ከፈጣሪው ሲርቅ ጥበሩ ጠባዩ
ይቀየራል። ዓመሱ ይከፋል። ክፋቱንም በዙሪያው ባሉ ሥነ ፍጥረት
ላይ ይፈጽማል። ያለርኀራኄ ዕፀዋቱን ይጨፈጭፋል፣ እንስሳቱን አራ
ዊቱን ይገድላል። እግዚአብሔር መጠለያና ምግብ ይሆናቸው ዘንድ
የፈጠረለቸውን ዕፀዋት ስለሚያቃጥልባቸው አብረው ከመቃጠል የተ
ረፋት ለስደት ይዳረጋሉ። ክላይ እንደተገለጠው ሰው በጭካኔ ተነሣስቶ
ፍጥረቱን ባጠፋ ቁጥር ራሱም ወደየባለ ችግር እያመራ ይሄዳል።

ከጋጢአት ርቀው የኖሀ ልቡናን ገንዘብ ያደረጉ ቅዱሳን ክሰው
አልፈው ለመሳው ፍጥረት ያዝናሉ ይራራሉ። ለትንሿ ፍጥረት ያስባሉ።
በአራቱ "የወንድምህ አህያ ወይም በሬው በመንገድ ወድቆ ብታይ
ከአርሱ ጋር ሆነህ እነሣሣው እንጂ ቸል አትበለው በመንገድ ብታይ
በዛፍ ወይም በመሬት ላይ እናቲቱ በሚጨቆችዋ ላይ ተኝታ ሳለች
የወፍ ልጅ ብታገኝ እናቲቱን ከሚጨቆችዋ ጋር አትውሰድ። ነገር
ግን መልክህም ይሆንልህ ዘንድ እናቲቱን ስደድ ሚጨቆችዋንም ለአንተ
ውሰድ" ተብሎ የተነገረው ሰው ለእግዚአብሔር ፍጥረት ምን ያህል
ርኀሩኀና አዛኝ መሆን እንዳለበት ያሳያል። ዘዳ ፳ ፥ ፬ ና ፮፤
ዘጸ. ኛ ፫ ፥ ፬-፭። "ጻድቅ ሰው ለእንስሳው ነፍስ ይራራል" የተባለው
ጻድቃን የእግዚአብሔርን ፍጥረት በመጠበቅ ረገድ ያላቸውን ርኀራኄ
ያሳያል። ምሳሌ ፲፪ ÷ ፲።

በሀገራችንና ክገጠር አስክ ከተማ ባሉት አዋቢያዎች የምናያ
ቸው ማራኪና አስደሳች ዕፀዋት እንዲሁ የተገኙ ሳይሆን ቀደምት አባቶ
ቻችን ሥነ ፍጥረትን መንክባክብ የሰው ልጅ አደራና ግዳጅ መሆኑን
በመገንዘባቸው ሁተከሉዋቸው ናቸው።

በሀገራችንና በመሳው ዓለም በመስፋፋት ላይ ያለውን ደርቅና
በረሃማነት ለመከላከል እግዚአብሔር የተለያዩ ገብረ ቀለም ዘዴዎች
ዕበዋትና እንስሳት አስኒጠ የፈጠራትን ዓለም በዘመናዊው አውተ
ታግዞ መንከባከብና ለማጠጠም ትውልድ የተማገለ ፍጥረትን
ማበተሳሰፍ ይኖበል።



እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ካከናወነን በኋላ "ያ
መልክም እንደሆነ አየ። ዘፍ.፩ ÷ ፲። ይህን መልክም የሆነውን ፍጥ
ረት በጸጋ ይኀሣ ዘንድ የተሾመው ሰው በተፈጠረበት ወቅት ደግሞ
"እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ።" እነሆም እጅግ መልክም ሆኖ
መፈጠሩ ያለበት ኃሳፊነት ክባድ መሆኑን ያስረዳል። ይህ እጅግ መል
ክም ሆኖ የተፈጠረው ሰው መልክም የሆነው የእግዚአብሔር ክሃሲ
ነት ጥበብና ፈቃድ የተገለጠባቸውን ሥነ ፍጥረት ማበጀቱና መጠ
በቁ መልክም የሆነችውን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመቃደል
ያበቃዋል።

### የማስተሰሰትን ጥያቄዎች መልስ ጠ።

፩. ሥነ ፍጥረት ሰለው ልጅ ክማይበረክቱት መንፈላዊና ሥጋዊ
ጥቅሞች መካከል በዓይነት አምስቱን ይዘርዝሩ።
፪. የቤተክርስቲያን አበው ሥነ ፍጥረትን በመንክባክብ ሂደት ያበረከ
ቱትን አስተዋጽዎ ዘርዝሩ።



# ምዕራፍ ሰባት

## ፯. በሥነ ፍጥረት ትምህርት ሰምን እናምናለን?

### ፯.፩ የሥነ ፍጥረት መጻሕፍት መለኮታዊ መጻሕፍት ስለሆኑ

አምስቱ ብሔረ አሪትን የጻፋቸው ሙሴ እንደሆነ እናም
ናለን። እርሱን በመንፈሱ ቃኝቶ ያጻፈ ደግሞ እግዚአብሔር ነው።
ስለዚህ የሥራው ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር እንደሆነ እናም
ናለን። እንዲህ እንድናምን የሚያስንድጀንም ስለሙሴና ስለመጻሕ
ፍቱ ጌታችን በዘመነ ሥጋዌው የሰጠው ምስክርነት ነው። ለእስ
ረጂም የተወሰኑትን እንመለከታለን።

ሀ. አይሁድ ጌታችንን ስለፍቹ ከጠየቁት በኋላ "ሁሉቱ አንድ ሥጋ
ናቸው እንጂ ወደፊት ሁለት አይደሱም።" በማለት በዘፍጥ
ረት ላይ በሙሴ አድሮ ያስጸፈውን አስተምሮአቸዋል። በኋላም
የጌታችን ትምህርት ከሙሴ ትምህርት ይጋጫል ለማለት
"እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈታት
ስለምን አዘዘ?" ባሱት ጊዜ "ሙሴስ ስለልባቸሁ ጥንካሬ
ሚስቶቻቸሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላቸሁ እንጂ ክጥንት ግን
እንዲህ አልነበረም።" በማለት የሙሴ ትምህርት ከእርሱ
ትምህርት ጋር አንድ መሆኑን አስረግጠላቸዋል። ዘፍ.፪ ÷ ፳
ማቴ.፲፱ ÷ ፮-፱።

ለ. ስለመጻሕፍቱም በግልጽ ሲናገር እንዲህ ብሎአል። "እኔ
በአብ ዘንድ የምክሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚክሳችሁ አለ አር
ሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑ
እኔን ደግሞ ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለእኔ ጽሮአልና። መጻ
ሕፍቱን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?" በማ
ለት የእግዚአብሔርን ሥራ ለማመን የሙሴ መጻሕፍት ዋና
ምቹ አስረጂዎች እንደሆኑ ገልጿል። ዘማቴ.፭ ÷ ፲፯ ላይም
"... ክሰረገ (ከሙሴ መጻሕፍት ሕግጋትን እንዴት የሙሣ
ወይም እንዲት ነጥብ ክቹ አንልሳም ሁሉ አስኒፈጸም ድረስ።



በማለት የመጻሕፍቱ ባለቤት አስረግጧል። መጻሕ ፍቱ
ዘላለማውያን ሆነው የሚኖሩት ባሰቢታቸው አርሱ ዘላለ ማዊ
ስለሆነ ነው።

ሐ. ሙሴ የሠራው ሁሉ ከእርሱ ከእግዚአብሔር የተሰጠና
ለጊሳው ለዘመነ ሥጋዊ አምሳል መርገፍ መሆኑንም ሲናገር
"ሙሴም በምድረ በዳ የነሐሱን እባብ እንደሰቀለ ÷ እንዲሁ
በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት ኤንዲኖረው አንጂ
እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።" ብሎአል።
ዮሐ.፫ ÷ ፲፬። እነዚህ ሁሉ የሚያስረዱት ሙሴ ከእግዚአብ
ሔር የተላከ መሆኑንና መጻሕፍቱም የሳኪው የእግዚአብ
ሔር መሆናቸውን ነው። የሙሴን መጻሕፍት ከእግዚአብ
ሔር ናቸው ብሎ የሚያምን ሰው በአሪት ዘፍጥረት የተጻ
ፈውን "ሥነ ፍጥረትን እንዲያምን መጻሕፍቱ ይሰገድ
ጹታል።

### ፯.፪ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስለሆኑ

የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ከአንቀጸ ሃይማኖት ጀምረው
በትምህርታቸው በቅጻሌያቸው (የፍጡር መኖር ከፈጣሪ እንደ
ሆነ) አስተምረዋል። ለዚህም ከመጀመሪያው ከኢትዮ ጉባኤ ብን
ጀምር የመጀመሪያው አጉቶጽ "ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብ
ሔር አብ አጋዝ ኩሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢ
ያስተርኢ።" ዓለምን ሁሉ በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና
የማይታየውን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር
እናምናለን፤ . . . " የቅዱስ ባስልዮስና የቅዱስ ጎርጎርዮስ ቅዳሴ
ያትም ይህን አምልኣውና አስፍተው ይገልጡታል። ስለዚህ
ይህ የሊቃውንት ትምህርትም የሐዋርያት ትምህርት ነው።
የሐዋርያት ትምህርትም የሐዋርያት ትምህርት ነው።
ሰንኳን ያስእርሱ አልሆነም።" የሚል መሆኑ በቅዱሳት መጻሕ
ፍት ተመዝግቦአልና። ዮሐ.፭ ÷ ፫፣ ቆላ፩ ÷ ፲፫-፲፮።

ይህ የቤተክርስቲያን ትምህርት ክጌታ ወደ ሐዋርያት
ክሐዋርያትም ወደ ሊቃውንት ክሊቃውንትም ወደ መምህራን
እየተላለፈ እኛ አስካለንበት ኅለመለወጥ ጸንቶ ይኖራል።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር መሆኑን አውቀን በሥነ ፍጥረት ፍጹም እናምናለን።

## ፯.፫ ያለ ሥነ ፍጥረት ክርስትናን ማመን ስለማይቻል

ቤተክርስቲያን ሞት የኃጢአት ውጤት እንደሆነ ታምናለች ታስተምራለችም። "ኃጢአትም ሞትን ትወልዳለች።" እንዲል። አንድ ሰው ሥነ ፍጥረትን ካላመነ ሞት የኃጢአት ዉጤት መሆኑን ሊያምን አይችልም። ሞት ከአዳም በፊት ነበረ፤ የኃጢአት ውጤትም አይደለም። ካለ ደግሞ ወልደ እግዚአብሔር ለምን ሰው ሆነ? የሚለውን ሊያውቀውና ሊረዳው አይችልም። ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ ይህ ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው።" ዋኃለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤ ሁሉን ከእንሩ በታች አስገዝቷልና። ፩ኛቆሮ.፲፭ ፥፳፮ የሚለውን የሐዋርያት ትምህርት ሊቀበልና ሊያምንበት ስለማይችል ክርስትናን ሕይወት ያላጣዋል። ይህም ያለ ሥነ ፍጥረት እምነትና ትምህርት ክርስትናን መቀበል አለመቻሉን ነው የሚያስረዳው።

## ፯.፬ የሥነ ፍጥረት ትምህርት ለክርስትና ትምህርት መሠረት ስለሆነ

አንድ ሰው ሥነ ፍጥረትንና የሥነ ፍጥረት አስረጂ የሆኑ የሙሴ መጻሕፍትን ካልተቀበለ የጌታን ትምህርት እንዴት ሊቀበል ይችላል? ሙሴ የጌታችን ምስክር ሆኖ እንደመጣ ጌታችንስ አስተምሯልና። ዮሐ. ፭ ፥፵፮።

በክርስትና የምንገባር ትምህርትን እንኪን ያለ ሥነ ፍጥረት ማስተማር አይቻልም። ምክንያቱም ቃለ እግዚአብሔር መመሪያችን ሲሆን የሚችለው፦

ሀ. እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው። ስለዚህ ጠባቂያችን መጋቢያችንና መሪያችን ፊታውራሪያችን ነው።

ለ. ሥነ ፍጥረት አርግጥ ነው፤ የሥነ ፍጥረት መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ኃላፍነት ሊኖረን ብቻ ነው። አሰባ ማል (አንድ ነው) የሚል እምነት ሊኖረን ብቻ ነው። አሰባ ለዚያ ማንን ፈርተን (ፈጣሪ ከሌለ) ቃለ እግዚአብሔርን



እንጠብቃለን? ለምንስ ምግባር ይኖረናል? በክርስትና ትምህርት እናራምዳለን ለሚል መጀመሪያ የገጽ በሥነ ፍጥረት ማመን ይጠበቅብናል።

### የሚከተሉትን ጥያቄ መልስ ጠ።

፩. አንድ ሰው ስለሥነ ፍጥረት ባይማር ምን ይጎድለዋል? ቢማርስ ትርፉ ምንድን ነው?

፪. በአካባቢህ ወዳሉ ጥቃትን ነፍሳት /ጉንዳን፣ ንብ፣ ቢራቢሮ/ ሂድና በማስተዋል ተመልከት። ምን ተማርህ?



## ማኅበረ ቅዱሳን ማን ነው?

- ታሪክ፦ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የክፍተኛ ትምህርት ተጅማት በነበረ የቤተ ክርስቲያኒቱ ፀጸኞ ተመሠረተ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ርቀ የነበረውን ትውልድ ቀርቦ ቤተክርስቲያኒቱን ስጎዳያገለግልና ስንዳንገ በማጽደረግ ክፍተኛ ስስዋጽኦ ሲያበረክት ቀጽቷል፤ ስዚህም በማበርከት ላጽ ጸሸፀ። በ፲፱፻፹፰ "ማኅበረ ቅዱሳን" የሚለውን ሰያሜ ስግኘት ስገልግሎቱን በማጠናከር የክፍተኛ ትምህርት ተጅማት ተማሪዎችን ከማስተማርና ከማስመሪቅ በተጨማሪ ሰፊ ስገልግሎት በማበርከት ላጽ ጸሸፀ።
- ስያሜ፦ "ማኅበረ ቅዱሳን" ስገዚአብሔር ያክበራቸው የነበሩት፣ ቅሰዋርያት፣ የጸጽጋት ስስጠፉት የቅዱሳን ገጸባ፣ ትሩፋትና ስማጸጽኑት የሚዘክርበት በመሆኑ ይህን ሰያሜውን ስገኘ።
- ዓሳማ፦ ትምህርተ ወንጌልን በተስያዩ ወንገጸች ማጸደስ፣ ስባላቱ ቤተ ክርስቲያንንም ሆነ "ማኅበረስቡን በስመቀታቸው፣ በገንዘባቸውና በጉስቡታቸው ስንዳያገለግሉ ማስቻል።
- አስራሳኒነት፦ በክፍተኛ ትምህርት ተጅማት ወጣቶችን ከሚነጥቁት
  - ወጣት የቤተክርስቲያንን ትምህርት ተምሮ ተውሬነን የሚያስተሳስፍበትን ወንገጸ በዘዋቀስ፣
  - ክተመረቀ በኃላ ተበተነው ስንዳጸዋቀሩና ቤተክርስቲያንን ስንዳያገለግሎ ሰማስቻል የሚሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።
- አቋም፦ በማንኛውም የፖስቲካ ስንቅስቃሴ ውስጥ ምንም ዓይነት ጣወቃ ንዛነት የስውም።
- አሰሳታ፦ በበተክርስቲያናችን ማሠወዐመኛዎች ሠወጥነው የመጠና በስንገለገሉት ላጽ ያሉ ስባቶችና ወንጸሚሞች ስንጸዘውም ጸቃመዘሄመራት፣
  - በክፍተኛ ትምህርት ተጅማት ስጥቢያ ስሱት የስ/ት/ቤቶች መርሐ ገበር የሚማረ ተማሪዎች፣
  - ከተመረቀ በኃላ የስገበት ት/ቤት ልና ዘደም የሰበካ ጉባኤ ስባላት በመሆን ስገልገሉት ስየደጸጭ ያሱት፣
  - ሰማኅበረ ዓለማ ተገበረዊነት በገንዘባቸው በስመቀታቸውና በጉስቡታቸው የሚረዱ ምዕመናን ናቸው።
- አባልነት፦ ከላጽ ስባላት በሚስ ሥር የተዘረዘረትን ያሟሉ
- መዋቅር፦ በሊትዮጵያ አርተጽክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በስ/ት/ቤቶች ማጸደራ ወሰን ሲያ ሥር ሆኖ መንፈሳዊ ስገልገሎቱን ጸደጀማል። በአህጉር ስብክትም ንውላን ማዕከላት

የስገልገሎት ዘርፎች፦

ሀ. የትምህርት ክፍሎ
ለ. የጽዝሙራና ሥነ ጥበባት ክፍሎ
ሐ. የሙያ ስገልገሎትና ተራጆች ክፍሎ
መ. የጥናትና ምርምር ክፍሎ
ሠ. የኮምኒኬሽን ክፍሎ
ረ. የሕጻብ ክፍሎ
ሰ. የመረጃና ወጠግባት ክፍሎ
ሸ. የማኅጸና ልቅጆ ክፍሎ
ቀ. የጥቅመት ዝግጅት ማዕከተበስሪሃ ክፍሎ
በ. የጎጥሞት ተጅማት ስስተጸጸር